## ወደ ምዕራፍ አሥራ አራት መግቢያ

አቶ መሐሪና ሌሎች ወንጌላውያን በደቡብ ኢትዮጵያ የሕክምና አገልግሎትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና መጫወታቸውን ራሳቸው አቶ መሐሪ ይናገራሉ። የምዕራባውያንን /ዘመናዊ/ መድኃኒት በኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን ከሶዶ ሆስፒታል የሚከፋፈለውን ወደ ቡልቂ ኤስ አይ ኤም ክሊኒክና ባኮ ሲያዳርሱ እነዚያ ወንጌላውያንም በጊዜው በሽታ ሁሉ የራሱ የሆነ መንፈሳዊ መነሻነት አለው በሚለው ባህላዊ እምነት ከተጠመዱትና በባሕላዊ ጠንቋዮች ሊድን ይችላል ብለው ከሚሉት ጋር ይጋፈጡና ይከራከሩ ነበር።

እስከ 1966 ዓ.ም አብዮታዊ ለውጥ ድረስ እጅግ በርካታ ቁጥር ያለው የደቡብ ኢትዮጵያ ወንዶች ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን በየዓመቱ በሙግት ያባክናሉ። ፖሊስ ጣቢያና እሥር ቤት በየቦታው የሚገኝ ነበር። በወቅቱ የአማራ አገዛዝ የበላይነት እንደነበረ ሆኖ ባሕላዊ ፍርድንና ዳኝነትን እንዳለ አጥፍተውት ነበር።

ነገር ግን የሕግ አደባባዮች የሕዝብ መገናኛ ማዕከላት ነበሩ። ይህም ማለት ለምሳሌ እንደነ አቶ መሐሪ ያሉ ወንጌላውያን በእጅጉ በሚቃወሙአቸው ሰዎች መካከል እየተገኙ ወንጌልን ያስተምሩ ዘንድ እግዚአብሔር ብዙ አጋጣሚዎችን አዘጋጅቶላቸዋል። ይህንን የእውነትን ቃል ለማስተላለፍ ወንጌላውያኑ ይደርስባቸው የነበረውን ሥቃይ በደስታ ተቀብለውታል። በጋሞ ጐፋና በተቀሩት የአገሪቱ ክልሎች ብዙ ምእመናን በደረሰባቸው ኢ-ሰብአዊ ሥቃይና መሠረታዊ ሕክምና አጥተው ለሞት ተዳርገዋል።

በቤተሰቦቻቸው አቅራቢያ የታሠሩ ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ምግብና ልብስ ያለችግር ይቀርብላቸዋል። በክፍለ ሀገሩ ወህኒ ቤት የሚታሠሩት ግን በቅርብ የሚደርስላቸው ነገር ባለመኖሩ ሥቃያቸው እጅግ የከፋ ነበር።

ነገር ግን ወንጌላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ብቁነት በሚገባ በማረጋገጥ በከሳሾቻቸው ፊት ቃሉን በሙላት እየሰጣቸው በብቃት መንፈሳዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ችለዋል።



# የበለጠ ችግር በጐፋ ውስጥ

## ምዕራፍ አሥራ አራት

ከስምንት ወር በኋላ በ1951 ዓ.ም ሚስተር ማክሊላን በቡልቂ የኤስ አይ ኤም ጣቢያ ውስጥ ቤቶችን ለመገንባት ተመለሰ። በጣም ታምሜ ስለነበረ ደጋግሜ በሕክምና እንዲረዳኝ ጠየቅኩት። ወቅቱ ክረምት ስለነበረ ወደ ቡልቂ ምንም መኪና ለመግባት አይችልም ነበር። የአይሮኘላን ማረፊያና መነሻ የሚሆን ቦታ በባኮ መንግሥት አዘጋጅቶ ስለ ነበረ ከአዲስ አበባ ባኮ አስፈላጊውን አቅርቦት በአየር ማጓጓዝ ይቻል ነበር። በክረምቱ ወቅት በቡልቂ የነበሩ ሚስዮናውያን ገንዘባቸውን ሲጨርሱ፣ ሚስተር ማክሊላን ወደ እኔ መጥቶ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሃሳብ እንዳካፍለው ጠየቀኝ። ቀኑን ሙሉ ሳስስና ስፈልግ ውዬ ከቡልቂ ወደ ባኮ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር በእግር ተጉዞ ገንዘብ ሊያመጣላቸው የሚችለውን ወንጌላዊ አገኘሁላቸው። ገንዘቡ ሲደርሳቸው ሚስዮናውያኑ በቡልቂ የጀመሩትን የቤቶች ሥራ ግንባታ ለመቀጠል ችለዋል።

በተመሳሳይ ጊዜም እኔ መድኃኒት አግኝቼ ለስምንት ወር ሙሉ መርፌ ለመወጋት ችያለሁ። ይሁን እንጂ፣ የተሻለኝ ነገር አልነበረም። በአካባቢውም ተዘዋውሬ እንዳልሰብክ አቅም አጣሁኝ፣ ስለዚህም ተመልሼ ወደ ወላይታ ሆስፒታል ለመሄድ ወሰንኩኝ። ሄጄም በወላይታ ሶዶ ሆስፒታል አራት ወር ተኛሁ። ነገር ግን ጤናዬ አልተመለሰኝምና እዚያ ተኝቼ ለመቀጠል አልፈለግኩም።

አንድ ቀን ዶክተር ባርሎው ወደ እኔ መጥተው፣ «መሐሪ» አሉኝ። «አቤት፣ ምን ፈለጉ» አልኳቸው።

«ለምን እዚህ ተኝተህ ትውላለህ? ተነሣና ነቃ ብለህ ለመሥራት ሞክር» አሉኝ።

እኔም፣ «ይኸማ ጥሩ ማበረታቻ ነው» አልኩና ተነሥቼ እየተንቀሳቀስኩ አነስተኛ ሥራ ለመሥራት ሞከርኩ። ወዲያው ግን ሕመም ተሰማኝና ደከመኝ።

ዶክተሩም «ተመልከት፣ ተገቢውን ዕረፍት ካላገኘህ በፍጹም ሊሻልህ አይችልም። ግማሽ ዕረፍት አግኝተህ ልሥራ ካልክ ላንተ ጥሩ አይሆንም።» አሉኝ።

ዶክተር ባርሎው የሚሉኝን እገነዘባለሁ፣ ዳሩ ግን እኔ ስለብዙ ነገሮች እጨነቅ ነበር።

ከጐፋ ባለቤቴ ደብዳቤ ጻፈችልኝ። በምናርሰው መሬት ምክንያት ከፍተኛ ችግር እንደደረሰባት ነበር የጻፈችልኝ። የመሬቱ ባለቤት ኪራዩን ጨምሮብን ስለነበረ ማረስ ወደማንቀጥልበት ደረጃ ደርሰናል የሚል ሲሆን፣ ተጨማሪውን ግብር ካልከፈልነውም የእርሻ ሰብላችንን እንደሚወስድብን ገለጸልን። እህላችንን ከወሰደብን ደግሞ ለሚቀጥለው ዓመት የምንበላውን እናጣለን። ስለዚህም ከፍተኛ ስጋትና ጭንቀት ውስጥ ገባሁ።

ወደ ዶክተር ባርሎው ሄጄም፣ «ወደ ጐፋ መመለስ እፈልጋለሁ። ቤተሰቦቼ በብዙ ችግር ላይ ነው ያሉት። ምን ይሻለኛል?» አልኳቸው።

እርሳቸውም፣ «በደረትህ ውስጥ ያለብህ በሽታ አልተወህም» አሉኝና አስፈላጊውን መድኃኒት ሰጡኝ። «ለሁለት ዓመት ሙሉ መድኃኒት ሳታቋርጥ ብትወስድና ብዙ ዕረፍት ብትወስድ፣ እንዲሁም ከባድ ሥራ ባትሠራ ምናልባት ይሻልሃል» አሉኝ።

እኔም ባለቤቴም ተመሳሳይ በሽታ እንደያዛት ነገርኳቸው። እርሳቸው አራት መቶ ፍሬዎችን ለእኔ አራት መቶ ፍሬዎችን ደግሞ ለባለቤቴ እንድወስድላት ሰጡኝ። መድኃኒቶቹን ተቀብዬ ወደ ጐፋ ተመለስኩኝ። በጣም ከመድከሜ የተነሣ ከውጪ ሚስዮናውያን መካከል የተወሰኑት የአይሮኘላን ቲኬት ገዝተው ሰጡኝና በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሶዶ ለቡልቂ ወደሚቀርበው ሳውላ ወደሚባለው ስፍራ በአውሮኘላን በረርኩኝ።

## የበለጠ ችግር በጐፋ ውስጥ

ወደ ጐፋ ከተመለስኩኝ በኋላ ምንም ሥራ ልሠራ አልቻልኩም። በ1952 ዓ.ም ለአምስት ወር ሙሉ ከፍተኛ ችግር ደረሰብኝ። ባለሥልጣኖች የነበሩት የተወሰኑ ክርስቲያኖችን አሠሩአቸው። ባለቤቴም ጠንካራ ክርስቲያን ነበረችና እርሷንም ወስደው አሠሯት። እኔ በአልጋ ላይ ተወስኜ በመቅረቴ ለጊዜው አላሠሩኝም። ነገር ግን ሰዎች፣ «በዚህ አካባቢ እየዞረ የሚሰብከው እርሱ ነውና እርሱ መታሠር አለበት» ይሉ ነበር።

አንድ ቀን ሁለት ቄሶች አንድ ፖሊስ ይዘው ወደ ቤቴ መጡ። «

«ተነሥ! ብድግ በል! ተነሥ!» አሉኝ።»



«ለምን ፈለጋችሁኝ? ምንድን ነው ነገሩ?» እያልኩኝ ተከራከርኳቸው።

«ተፈልገሃል» አሉኝ።

«ማን ነው የፈለገኝ? ለምንድን ነው የተፈለግኩት?» ብዬ ጠየቅኳቸው።

«ለምትጠየቀው ጥያቄ መልስ እንድትሰጥ በፖሊስ ጣቢያ ተፈልገሃል» አሉኝ።

እሺ ብዬ በመስማማት ልብሴን ለበስኩና በከተማ ወዳለው ፖሊስ ጣቢያ በዝግታ አዘገምኩኝ።

ከባለሥልጣኖች አንዱ የሆኑት፣ «መሐሪ» ብለው ተጣሩ።

«አቤት፣ አለሁኝ» አልኳቸው።

«አንተ ሠራተኛ ነህ ወይስ ሰባኪ ነህ?» አሉኝ።

ጥያቄው ቀጥተኛ ነበር። በዚያ በግልጽ አሳብ ላይ መከራከርና ጊዜ ማጥፋት አይገባንም።

ሰዳኛው ወንጌላዊ መሆኔን በነገርኳቸው ጊዜ፣ አንድ የመጨረሻ ጥያቄ ብቻ እጠይቅሀሰሁ አሉና፣ «ከዛሬ ጀምሮ መስበክ ታቆማለህ ወይስ አታቆምም?» አሉኝ።

እርስዎም ይንገሩኝ፣ «አንድ ሰው መተንፈስ ያቆማል? ሰእኔ መስበክ ማለት እንደ መተንፈስ ማለት ነው። ለእኔ ስብከት ሥራ ሳይሆን ሳላቋርጥ የማደርገው ቀጣይ ክንውን ነው። አንድ ሰው መተንፈስ ካቆመ ይሞታል፣ እኔም እስክሞት ድረስ ስብከቴን ማቆም አልችልም» አልኳቸው።

«ይህ የመጨረሻ መልስህ ነው?» አሉኝ።

«ሌላ መልስ ልሰጥ አልችልም» አልኳቸው።

«እንግዲያውስ አንድ ነገር ልንገርህ፣ ስብከትህን ካላቆምክ ወደ ወህኒ ትጣላለህ» አሉኝ።

«ሌላ ምርጫ የለኝም። የማውቀው አንድ ነገር ቢኖር ስብከቴን ማቆም አልችልም። ለምን ሰበክህ ብለው ወደ እሥር ቤት የሚያስገቡኝ ከሆነ ያ የእርስዎ ውሳኔ ነው» አልኳቸው።

በ1952 ዓ.ም በየካቲት ወር የመጀመሪያ ቀን ፀጉሬን ላጭተው ወደ ትልቁ ወህኒ ቤት አስገቡኝ። በእርግጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ

የሚጸልዩልን ወገኖች እንዳሉ አውቅ ነበር:: በዚያን ጊዜ እየተሠቃየን ማገልገላችን ለብዙዎች ከፍተኛ ብርታትን ሰጥቷቸዋል:: እኔ በምኖርበት አካባቢ ሦስት የጸሎት ቤቶች /ማኅበራት/ ነበሩ:: እነርሱም አይከና፣ አላ እና ባጋ በመባል ይታወቃሉ:: ያኔ እኔ በባጋ እሰብክ ነበር:: በተጨማሪም ከዚያ የማኅበር መሪዎችንና ሦስት ወጣቶችን ይዘው አሥረዋል:: ከአይከና ቤተ ክርስቲያን ደግሞ መሪዎች የነበሩት ሁሉም ታሥረዋል:: ሲኩ እንደ ዬዊሻ ጠንካራ መሪ ነበር:: ከአላ ማኅበር ደግሞ አብዛኛዎቹ መሪዎች ታሥረዋል:: በተለይም ታመነው እና ጳውሎስ ጌቱሮ የሚባሉት ታዋቂ መሪዎች ነበሩ:: ጳውሎስ የእኔ ተማሪ የነበረ ሲሆን፣ ትጉሕ ወንጌላዊ ሆኗል:: ሁላችንም በአንድ እሥር ቤት የታሠርን ስለሆነ እርስ በርሳችን በእጅጉ እንጽናና ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስን ለመማማርና ለማስተማርም የቻልንበት ጊዜ ነበር::

ታዲያ፣ የሁላችንንም ፀጉር ላጭተው ወደ ትልቁ ወህኒ ቤት አስገቡን:: እኛም በእሥር ቤት ውስጥ ከተረጋጋን በኋላ የጸሎት ፕሮግራም ጀመርን:: አንድ ቀን እኔ እየጸለይኩ ሳለ ከዘበኞች አንዱ ብቻውን መጣና፣ «ጫማህን አድርግ! ስማ፣ ጸሎት አቁም! ጫማ አድርግ ነው የምልህ:: ትሰማኛለህ? አትታዘዙም? አቁም ነው የምልህ» አለኝ:: ለእርሱ ጩኸት ትኩረት ሳልሰጥ መጸለዬን ቀጠልኩ:: አሁን ጩኸቱን አቁሞ ጸሎቴን እስክጨርስ ጸጥ ብሎ ቆመ::

«ቆይ ጠብቅ! ነገ ምን እንደሚከተልህ ታያለህ:: አንተን በመቃወም ክስ እመሠርትብሃለሁ:: በየሄድህበት ቦታ ሁሉ ችግር እንደምትፈጥር እያየሁ ነው:: በዚሁ በትልቁ እሥር ቤት ውስጥ በችግር ፈጣሪዎች ላይ ምን ማድረግ እንዳለብን እናውቃለን» አለ::

ወደ ሁላችንም አፍጥጦ እየተመለከተ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብሎ ቆመ:: «እንዳትሰብክ ተነግሮህ ነበር:: ለአገሪቱ ሕግ የማትታዘዝ ስለሆንክ በተደጋጋሚ ታሠርክ:: አሁን ደግሞ በእሥር ቤት ትሰብክ ጀመር? ልንገርህ? አንተ ችግር የምትፈጥር ነህ:: ከእንደ አንተ ዓይነት ሰዎች ጋር እንዴት መደራደር እንደሚቻል ቆይና ታያለህ» አለኝ::

የእርሱ ሁኔታ ምንም አላስፈራኝም፣ እንዲሁም ሌሎች ስለሚነዙት ሁሉ ምን ያደርጉኝ ይሆን የሚል ጭንቀት አልነበረኝም:: ታምሜ በአልጋ ላይ በነበርኩ ጊዜ ወስደው እንዳሠሩኝ ታስታውሳላችሁ::

አሁንም ገና እየታመምኩ ነው አምጥተው በዚህ በትልቁ እሥር ቤት ያስገቡኝ::



ዘበኛውም እኔን ለመክሰስ ማመልከቻውን ለሃምሳ አለቃው አቀረበ፣ በክሱ ማመልከቻ ያቀርበው ሃሳብ ማታ ይጮሁብኝ የነበረውን ቃል ብቻ ደጋግሞ ገልጾታል:: የሃምሳ አለቃውም አስጠሩኝና ወደ ቢሮአቸው ስገባ:-

«ለምንድን ነው በእሥር ቤት ውስጥ የምትሰብከው?» አሉኝ::

«እኔ አልሰበክሁም» አልኳቸው::

«አልሰበክህም? ኸ? ታዲያ ምን ታደርግ ነበር?»

«እኔ እጸልይ ነበር::»

«እንግዲያስ፣ ከዛሬ ጀምሮ በእሥር ቤት መጸለይ ማቆም አለብህ:: እሥር ቤት የጸሎት ስፍራ አይደለም ገባህ?» አሉኝ::

«መጸለይማ አላቆምም:: ለምንስ አቆማለሁ? እንዳልጸልይስ የሚያቆመኝ ማን ነው? በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ በእሥር ቤት ውስጥ መጸለይ ከሕግ ውጪ ነው የሚል አንቀጽ አለ?» አልኩኝ::

«እና መጸለይ አታቆምም? በል ቆይ መጸለይን ሳታቆም ስትቀር እናያለን! ኸ? በል ጫማህን አውልቅ!» አሉኝ::

ጫማዬን ካወለቁ በኋላ እግሬን በእግር ብረት አሠሩኝ:: እጅግ አጥብቀው ያሠሩኝ ስለሆነ በምንቀሳቀስበት ጊዜ እግሮቼን በጣም ያመኝ ነበር:: እኚህ ሰው የሃምሳ አለቃ ዓለማየሁ ለጥቂት ሳምንቶች በእግር ብረት ታሥሬ እንድቆይ አደረጉ:: ይሁን እንጂ እርምጃው በእርሳቸውና በሌሎቹም ዘንድ ምንም ለውጥ እንዳላመጣሁ ተመለከቱ:: ከዚያ በኋላ የእግር ብረቱ ከተፈታልኝ በኋላ በሃምሳ አለቃው ቤት ውስጥ ለየት ያለ ሥራ እንድሠራ ተደረገ:: እዚያም ኮርቻና የብርድ ልብስ እንዲሁም ሌሎች የተቀደዱ ልብሶችን ጨምሬ እሰፋ ነበር:: ሥራ መሥራት ጥሩ ነውና እኔም በዚያ በስፌት ሥራዬ ደስተኛ ሆንኩ:: ሌሎች ብዙ እሥረኞች የሚሠሩት ግን ውጪ ነበር::

አሁን ከወላይታ ሶዶ ከተመለስኩ አምስት ወር ሆኖኛል:: ጨርሶ ለመዳን ሁለት ዓመት እንደሚወስድብኝ ዶክተር ባርሎው ነግረውኛል:: የነበረብኝ ሳል ኃይለኛ ስለነበር ነበር የሃምሳ አለቃው ራርተውልኝ በቤታቸው ቀለል ያለ ሥራ እንድሠራ ያደረጉኝ:: ወዲያውም ያልተጠበቀ ፍጻሜ ደረሰ:: ከታሠርን ከጥቂት ሳምንት በኋላ በከባድ ወንጀል የታሠሩትን ክስ ለመመልከት ተንቀሳቃሽ ፍርድ ቤት ወደ ቡልቂ ደረሰ::

## የሥነ መለኮት መስቀልኛ ጥያቄ

በእሥር ቤቱ ውስጥ ከአሪ ጐሳ የሆነ ዚዶ የሚባል ሰው ክርስቲያን በመሆኑ ከእኛ ጋር ታሥሮ ነበር:: ቅጣቱን ለማክበድ ወታደሮቹ እግሩን በእግር ብረት አሠሩት:: ሰውየውም በክፍሉ ውስጥ ብቻ እየዳኸ ይንቀሳቀስ ጀመር:: ተንቀሳቃሹ ፍርድ ቤት በደረሰ ጊዜ ዚዶ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ሰድቧል የሚል ክስ ቀርቦበት ነበር:: ከቄሶቹ የደረሰበት ክስ የኦርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን የሚጻረር ትምህርት አስተምሯል የሚል ነበር:: በዚህም ምክንያት ቄሱ መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ ይጠራዋል:: ለዚህም ነበር ቄሱ ለፍርድ እንዲቀርብ ያስደረገኝ::

በመጨረሻም ስሜ ተጠራና ለጥያቄ ቀረብኩኝ::

«አንተ ወንጌላዊ ነህ? አንተ ነህ በየገጠሩ እየተዘዋወርክ ችግር የምትፈጥረው?» አሉና  ዳኛው ጠየቁኝ::

«ይህንን የሞኝ ወሬ ትቼ ወደ ቤቴ ተመልሼ እርሻዬን ማረስ አሰብኝ በልና ክሱ ይነሣልሃል:: ትስማማለህ?» አሉኝ::

«አይሆንም፣ ስብከቴን ማቆም አልችልም» አልኩኝ::

ከዚህም የተነሣ አንድ ዓመት እንድታሰር ተፈረደብኝ:: ወዲያውም ይግባኝ ጠየቅኩኝ:: ይግባኙ በደረሳቸው ጊዜ ፍርዱን ለውጠው ጉፋን ትቼ ወደ ቁጫ እንድመለስ ነገሩኝ::

እኔም ዳግመኛ ይግባኝ ጠየቅኩና ኢትዮጵያ አገሬ ናት፣ በፈለግኩበት ቦታ የመኖር መብቴ ይጠበቅልኝ:: ዳኛውም እሺ ይግባኝህ ወደ አዲስ አበባ ይላካል አሉኝ:: የይግባኙ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ በዋስ ተለቀቅኩኝ::

ወዲያውኑ ዚዶን መስቀልኛ ጥያቄ የጠየቀው ቄስ በፍርድ ቤቱ ተገኘ:: ቄሱም ችግር የሚፈጥር ሰው ስለሆነ በዋስ መለቀቅ የለበትም ሲል ለማግባባት ሞከረ:: እንደገና ለመስቀለኛ ጥያቄ ተጠራሁኝ::

«አንተ ወንጌላዊ ነህ?» አሉኝ::

እኔም፣ «አዎን፣ ወንጌላዊ ነኝ» አልኩኝ::

«ምንድን ነው የምትሰብከው?» ሲሉኝ፣



የምሰብከው ምን እንደሆነ በአጭሩ ነገርኳቸው፣ «በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉም ይድናሉ:: የማያምኑትም ይፈረድባቸዋል::»

«እግዚአብሔር ማን ነው?» አሉና ጠየቁኝ::

«እግዚአብሔር አባት፣ ልጁና መንፈስ ቅዱስ ነው::»

ቄሱ መለሰና፣ «ስለ ሥላሴ ምሥጢር የምታውቀው ቀላል መልስ ይኸው ነው? ሌላስ አታውቅም?» አለኝ::

«ስለ ወንጌል ትርጉም በዝርዝር አስረድቼሃለሁ:: እግዚአብሔር አባት፣ ልጅና መንፈስ ቅዱስ እንደሆነም ተናግሬአለሁ:: ከዚህ የበለጠ ምን ለማወቅ ትፈልጋለህ?»

«እንደ ጠበቅኩትም:- ስለ አባቶቻችን ሃይማኖት ምንም የምታውቀው ነገር የለም:: ነገር ግን ወንጌላዊ ነኝ ትላለህ:: ለመሆኑ ምን እየሰበክ ያለህ ይመስልሃል?» አለኝ

እኔም፣ «ወንጌል ማለት ምን እንደሆነ አውቃለሁ:: ወንጌልን ሰምተው የሚቀበሉም እንደሚድኑ አውቃለሁ:: የምትሰሙኝ ሰዎች ሁላችሁም ብቸኛ አዳኝ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ያስፈልጋችኋል» አልኳቸው::

ፍርድ ቤቱም ወደ ቄሱ በመዞር ምን ሃሳብ እንዳለው ጠየቀው::

ቄሱም፣ «ሰዎቹ፣ በተለይም ይህ ሰው ሁከት የሚፈጥር ነው:: ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ሁሉም በየገጠሩ እየዞሩ ችግር መፍጠራቸውን እናቆማለን ብለው እስኪስማሙ ድረስ መታሠር አለባቸው» ብሎ አሳቡን ሰጠ::

የቄሱም ምላሽ በጣም አስቆጣኝ::

«ሰዎችን ባትፈራ እንኳን እግዚአብሔርን ልትፈራ ይገባሃል:: እግዚአብሔር እንደሚፈርድ ታውቃለህ:: የምትለውም ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ልብህ ያውቃል» አልኩት::

ቄሱም በዚህ አነጋገሬ በጣም ተቆጣ:: «አሁንስ እየሰደብከኝ ነው:: እንዳልኩትም ችግር ለመፍጠር ነው የተወለድከው» አለኝ::

ዳኛውም በእግር ብረት እንድታሠር አዘዙ:: እንደገናም በእግር ብረት ታሠርኩ::

በቅርብ ጊዜ ክርስቲያን የሆነ ፖሊስ በፍርድ ቤት ቆሞ የሚባለውን ሁሉ ያዳምጥ ነበር። ወደ እኔ ቀረበና፣ «ለምን እንደዚህ ትናገራቸዋለህ? ለመስማማት ካልቻላችሁ ዝም ማለት አትችልም? ለራስህ እኮ ችግር እያመጣህ ነው። ዝም ካልክ ምናልባት ምሕረት አድርገው ሊፈቱህ ይችላሉ» አለኝ።

«አንድ ነገር ለመናገር ከፈለግኩኝ በዓለም ውስጥ ዝም የሚያሰኘኝ ምክንያት የለም።» ብዬ በጽሞና መለስኩለት።

ሁሉም የምናገረውን እንዲሰማኝ እፈልጋለሁ። ፖሊሱ ወደ እኔ ቀርቦ እያነጋገረኝ መሆኑን ያውቁ ስለነበር ስለ ውሳኔዬ እንዳስብበት እንዳነጋገረኝ ያዩት ነበር።

«እኔ የሰዎች እሥረኛ ነኝ እንጂ፣ የእግዚአብሔር እሥረኛ አይደለሁም። ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ያስፈታኛል። ስለዚህ ወደ ትልቁ እሥር ቤት መግባት አያስፈራኝም።» አልኩኝ።

«ዳኛውም በትልቁ እሥር ቤት መታሠር ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን በአንድ ቦታ ተወስነህ ብቻህን ትቀራለህ» አሉኝ።

እኔም፣ «አመሰግናለሁ፣ ክርስቲያኖች ብቻቸውን መሆናቸው በጣም ጥሩ ነው። ምክንያቱም በጸጥታ ሳይረበሹ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ይችላሉ። እኔ ለእግዚአብሔር ክብር ብቻዬን መሆኔ ምንም አይደለም። ምን ጊዜም እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው። ከሰዎች ጋር ከምሆን ብቻዬን ስሆን የበለጠ እጸልያለሁ» አልኳቸው።

## በሥቃይ ማደግ

ስለ መልሴ ምን እንዳሰቡ አላውቅም። ሌላ ተጨማሪ ቃል አልተናገሩም። በእግር ብረት እንደታሠርኩ ሰባት ወር ወደ ታሠርኩበት ትልቁ ወህኒ ቤት ወስደው አስገቡኝ።

በዚያች ምሽት አቶ ሻንካ የሚባል ክርስቲያን ሰው መጥቶ ጐበኘ ኝና፣ «የማቴዎስ አባት፣ እዚህ ነህ?» አለኝ። «አዎን፣ እዚህ ነኝ። እግዚአብሔር ይመስገንና ደህና ነኝ። አንተስ እንደምን ነህ?» አልኩት።

ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላም፣ «ዛሬ ሽልማት ተቀብያለሁ። ለምተሀል?» አልኩት።



«ኧረ ምንም አልሰማሁም። የምን ሽልማት ነው የተቀበልከው? ሁላችንም ቀን በየእርሻችን ስንሠራ ነው የዋልነው። ለመሆኑ ማን መጥቶ ነበር? እስቲ ንገረኝ» አለኝ።

«ያ አጭር ቄስ እዚህ የሚሠራውን ታውቅ የለም? እርሱ ሊጐበኘኝ መጣና ሽልማት ሰጥቶኝ ተመለሰ» አልኩት።

አቶ ሻንካም በግርምት ጸጥ ብሎ ደቂቃ አሳለፈና፣ «የምን ሽልማት ነው የሰጠህ?» አለኝ።

እኔም ሁሉንም ነገርኩት።

እርሱም፣ «ሞኝ ነህ! በእግር ብረት መታሠር ለአንተ ሽልማት ነው? ምናልባት አብደሃል» አለኝ። በፍጹም አላበድኩም። አሁን ብሠቃይም የኋላ ኋላ ሽልማቴን አገኛለሁ። መሠቃየትና ሽልማት አብረው የሚሄዱና የማይነጣጠሉ ናቸው። ለመሠቃየቴ ምክንያት የሆነኝ እርሱ ነው፣ ውጤቱ ግን ሽልማት ማግኘት ይሆናል።»

አቶ ሻንካ ወደ ቤት ተመልሶ የደረሰብኝን ሁሉ ለተቀሩት ክርስቲያኖች ሲነግራቸው፣ ሁሉም አዘኑ። እኔ ግን ለምን እንዳላዘንኩ ምንም አልገባቸውም ነበር። በሥቃይና በሽልማት መካከል ያለው ግን ኅነት አልገባቸውም።

ያ ግን አያስደንቅም፤ ብዙ ክርስቲያኖችም ይህንን ማለትም በመሠቃየትና በሽልማት መካከል ያለውን ልዩነት ስለማያውቁ ሥቃይን ይፈራሉ።

ከጐጃም የመጣው ወታደር መንግሥቱ የሚባለውና ባለፈው ጊዜ ስታሠር በእግር ብረት ያሠረኝ ወደ እሥር ቤት መጣ።

«አሁንም ይህንን ከንቱ ወሬህን አላቆምክም?» አለኝ።

«ምን ማለትህ ነው? ምን ስሕተት ሠራሁ?» አልኩት።

«ነፃ መውጣት ሲገባህ፣ ይኸው በእግር ብረት ታሥረሃል። ለምንድን ነው በየአካባቢው እየተዘዋወርክ ሰዎችን የምትሰድበው? ይህ የወንጌላዊ ሥራ አይደለም።»

«እንዴ፣ ታዲያ ምን ስሕተት ሠራሁ? ማንንም አልሰደብኩም። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ማስተማር ደግሞ ስድብ አይደለም።»

«ወዲያውም በል ጫማህን አውልቅና ስጠኝ» አለኝ። በዚያን ወቅት እኔ አሮጌ ሸራ ጫማ አድርጌ ነበር።

«የእኔን ጫማ ማድረግ ፈለግክ እንዴ?» አልኩት:: ጫማዬን የሚያስወልቀኝ ሊያስረኝ ሳይሆን ለራሱ ሊያደርግ ነው ባልኩት ጊዜ በጣም ተቆጣ:: ወዲያውም ጫማዬን ይዞ ሄደ::

በመጨረሻ ግን የሃምሳ አለቃ አለማየሁ ወታደሩ ጫማዬን ስለወሰደብኝ ገሥጸውና እንዲመልስልኝ አደረገ:: «ይህ ሰው ታሟል:: ጫማውን መውሰድህ ስሕተት ነው:: መልስለት::»

«እኔም ጫማዬን በጣም ስለምፈልገው የሃምሳ አለቃው ሲረዳኝ በጣም ደስ አለኝ::

## ተጨማሪ የእሥራት ጊዜ በጨንቻ

በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ለሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጽሑፍ ማመልከቻ ለመላክ እሞክር ነበር:: እነርሱም ወረቀቱን የክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ ወደ ሆነው ጨንቻ ወስደዋል:: በመጨረሻም አንዳንዶቻችን ወደ ጨንቻ እንድንሄድ ተጠራን:: ባለሥልጣኖቹም ከቡልቂ ወደ ጨንቻ በእግር አንድ መቶ ኪ.ሎ ሜትር ያህል እንድንጓዝ አደረጉን:: እዚያ ከመድረሴ በፊት እግሮቼ ከቁርጭምጪሚቴ ጀምሮ እስከ ጉልበቴ ድረስ አበጡብኝ:: በተጨማሪም ተረከዜ አበጠ:: ከቡልቂ ወደ ጨንቻ በእግር ለመጓዝ በአጠቃላይ አምስት ቀን ፈጀብን::

ወደ ጋሞ እንደደረስን የጋሞ ማኅበር መሪዎች አንድ በቅሎና ሁለት የሚረዱኝን ሰዎች ሰጡኝ:: ስማቸውም ዮሐንስና እርጌ ይባሉ ነበር:: ሁለቱም ወጣቶች በበቅሎ ላይ እየረዱኝ ወደ ክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ ጨንቻ ደረስን::

በፍርድ ቤት ተጠርቼ ለምጠየቀው ጥያቄ መልስ ከመስጠቴ በፊት በጨንቻ እሥራ አንድ ቀን ቆይቻለሁ:: ይህም የሆነው በሐምሌ ወር **1952** ዓ.ም ነበር:: ያ ፍርድ ቤትም ጉዳያችን በሶዶ እንዲሰማ ቀጠሮ ሰጠን:: የቀጠሮው ቀን የሚዘገይ ስለነበረም ወደ ቡልቂ እንድንመለስ ተደረገ:: ጊዜ ደርሶ ወደ ወላይታ ሶዶ የተወሰድነው ግን በፖሊስ ላንድሮቨር መኪና ነበር::

ሶዶን ዳግመኛ ለመጐብኘት በመብቃቴም በጣም ደስ አለኝ:: ወደ ሆስፒታል ሄጄም መድኃኒት እንድገዛ ተፈቀደልኝ:: ሌላ ተጨማሪ የሚዋጥ ኪኒንም አገኘሁ:: በወላይታ የነበሩ ክርስቲያኖችም ባዩኝ ጊዜ በጣም ተደነቁ:: በጋሞ ጐፋ ስለነበረው ስደት ብዙ ይሰሙ ስለነበር እኔንም ሞቷል የሚል ግምት ነበራቸው::



በወላይታ የሚገኙ ክርስቲያኖችም የጋለ አቀባበል በማድረግ ለባ ብር አዋጥተው ለምግብ ወጪያችን ሰጡን:: በጐፋ ለሚኖሩ አንዳንድ ወንጌላውያንም ገንዘብ ይከፍሉ ነበር:: ወደ ጐፋ ለመመለስ በተዘጋጀን ጊዜ ከቦንጋ ወደ ጨንቻ ተዛውሮ የነበረው ሚስዮናዊ ለመሄድ ተነሥቶ ነበር:: ያን ጊዜ በሳምባ ነቀርሳ በጣም እየተሠቃየሁ ስለነበር ያ ሚስዮናዊ በቅሎ ሊያቀርብለኝ ፈለገ:: አብረውኝ የነበሩት ክርስቲያኖች ሊቆዩ አልፈለጉምና ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ዕቃቸውን ሁሉ ይዘው ተንቀሳቀሱ:: በገንዘባቸውም ወደ ጐፋ ሲመለሱ ሸጠው ትርፍ ለማግኘ ት የብርድ ልብስ ገዝተዋል:: እኔም በበቅሎ እንደምከተላቸው በማመን ከኋላ ትተውኝ ሄዱ:: ሚስዮናዊው ወዳጄም በቅሎ ቢያፈላልግ ወደ ጐፋ ለመላክ ፈቃደኛ የሚሆኑ ሰዎችን ለማግኘት አልቻለም፣ ስለዚህም ተመልሼ በእግሬ ለመጓዝ ተገደድኩ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ሙሉ ጤና አይሰማኝም ነበርና ጉዞው ሦስት ቀን ወሰደብኝ::

## እሥር ቤትና የሳምባ ነቀርሳ

በእሥር ቤት የተቀበልኩት /የደረሰብኝ/ ምቾት አልባ አያያዝ ለእኔ ጥሩ ሳይሆንልኝ አልቀረም:: ምክንያቱም የያዘኝ የሳምባ በሽታ ቀስ በቀስ እየጠፋልኝ በመሄዱ ጥንካሬ እያገኘሁ በጐፋ የወንጌል ሥራዬን ለማከናወን በቃሁ:: እሥር ቤቱ ለእኔ ሆስፒታል ሆነልኝ:: የምፈልገውንም ዕረፍት ያገኘሁበትና ከበሽታዬም የተፈወስኩበት ስፍራ ነው::

የእሥር ቤቱ ብርድ ለእኔ መድኃኒት እንዲሆንልኝ እግዚአብሔር አደረገ:: የሰጡኝን ክኒኖች በየዕለቱ እየወሰድኩኝ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወርኩ ወንጌልን እሰብክ ነበር::

በስደቱ ወቅት እፍርሰውብን የነበረውን ጸሎት ቤት መልሰን ለመሥራት ልዩ ጥረት አደረግን:: በዚያውም ላይ ወንጌል ባልተሰበከባቸው አካባቢዎች እየሄድን መስበካችንን ቀጠልን::

በጐፋ የተቀናጀ የመጀመሪያ ስደት የተጀመረው በ1947 ዓ.ም ላይ ነበር:: አስቀድሞ ማስፈራሪያ ይደርስብን የነበረው ከግለሰቦች ሲሆን፣ ያም ከመንግሥት ባለሥልጣኖች የተቀናጀ ትእዛዝ ደርሶአቸው አልነበረም:: ነገር ግን፣ «በየትም ቦታ እየተዘዋወራችሁ መስበክ አይፈቀድላችሁም» ተብሎ ተነገረን:: «ሰዎችን ማጥመቅም ክልክል ነው» ተባልን:: «ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ማለትም /እሁድ/ ሰዎችን እየሰበሰባችሁ መዘመር፣መጸለይና መስበክ አትችሉም:: ፊደል

ለማስተማርም አይፈቀድላችሁም:: ጸሎት ቤቶችም ከሕግ ውጪ የተሠሩ በመሆናቸው መዘጋት አለባቸው» ተባለ::

ብዙ ክርስቲያኖች በተለይም እያንዳንዱን ማኅበር የሚያስተዳድሩ ኃላፊዎች እየተያዙ ታሠሩ:: እኔንም ለማሠር ሞክረው የነበረ ቢሆንም፣ ያን ጊዜ መያዝ ለእኔ የተሻለ አይሆንም ነበር::

የነበረን አማራጭ ወደ አዲስ አበባ ሄደን የፈቃድ ወረቀት ማምጣት ብቻ እንደሆነ ሽማግሌዎቹ ወሰኑ::

ስለዚህም እኔና ሌሎች ሁለት ሰዎች ወደ አዲስ አበባ ተላክን:: ከአራት ወር ቀጠሮና ማመልከቻ በኋላ ወደ ክፍለ ሀገሩ ባለሥልጣኖች ትእዛዝ እናስተላልፋለን አሉን:: እነርሱም በክፍለ ሀገር ያሉት ባለሥልጣኖች ሕገወጥ ነው ብለው ያገዱንን ሁሉ ለማድረግ ወይንም ለማምለክና ለማስተማር እንደምንችል አረጋገጡልን::

ይህንን ጥሩ ዜና በእሥር ቤት ለነበሩት ወገኖቻችን ለመንገር ደስ እያለን በዚያ በክረምቱ አደገኛ ጉዞ አደረግን::

ስለ ጉዞአችን አንሥቼ እግዚአብሔር በብዙ በተለያዩ መንገዶች እንደ ረዳን ነግሬአቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ስደቱ አልቆመልንም::

ከዚያ በኋላ በሁለት የተለያዩ ጊዜያቶች ባስኬቶ በሚባል ቦታ ታሥሬአለሁ:: የዚያ አካባቢ ሰዎች ወንጌልን አጥብቀው የሚቃወሙበት ምክንያት በጊዜው የነበሩ የአማራ ባለሥልጣኖች ክርስቲያኖችን ማሳደድ ስለሚያስደስታቸው ነው:: በመጀመሪያ የታሠርኩት እህል ለመሸመት ወደ ባስኬቶ በሄድኩኝ ጊዜ ነበር:: የታሠርኩበትም ምክንያት ለመስበክ የሄድኩ አድርገው ነው:: እጄን ወደ ኋላ በጠፍር ቀፍድደው አሠሩኝ:: ልክ አህያ እንደሚነዱ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ወደ ጐፋ በጅራፍ እየገረፉኝና በዱላ እየመቱኝ ነዱኝ:: ለሁለተኛ ጊዜ የታሠርኩትም ወደ ደሜ ለመስበክ በሄድን ጊዜ ነበር:: ያኔ ለአንድ ምሽት ብቻ አቆይተው ለቀቀውኛል::



# ወደ ምዕራፍ አሥራ አምስት መግቢያ

*አቶ መሐሪ ከቦታ ወደ ቦታ በሚዘዋወሩበት በተለያዩ ጊዜያት አገልግሎታቸውን እንደገና በስፋት እንደ ጀመሩ ይገመታል:: ከመሐሪ አገልግሎት በፊት የወላይታ ወንጌላውያን በደቡባዊ ምዕራብ ጐፋ ይሠሩ /ያገለግሉ/ ነበር:: ቀስ በቀስ ደግሞ በዚያው በደቡባዊና በምዕራባዊ ክፍል በአሪ ጐሳ መካከል አገልግሎታቸውን ያሰፉ ነበር:: በዚያ የኢትዮጵያ ክልል ወንጌልን ለማስፋፋት የሄዱ የመጀመሪያዎቹ የወላይታ ወንጌላውያን ናቸው::*

*አቶ መሐሪ ወደ ኋላ እንደሚያስታውሱት በእነዚያ ዓመታት ውስጥ አራት ነገሮች በአዕምሮአቸው ውስጥ ጐልተው ታይተዋቸው ነበር:: እነርሱም፣ ሀ) የመሬት ስርጭት፣ ለ) ወንጌላውያንን ማሠልጠን፣ ሐ) ጠንቋዮችን መዋጋት፣ መ) የእጅ ባለሙያዎች የነበሩትን ከኅብረተሰቡ ማዋሃድ የሚሉት ነበሩ:: እነዚህ ነጥቦች እያንዳንዳቸው ማኅበራዊ ጉዳዮች በመሆናቸው ወንጌላውያን ትኩረት ሰጥተውባቸው ለውጥ ለማምጣት አስፈላጊውን አስተዋጽኦ አድርገዋል::*

*ከ1968 እስከ 1969 ዓ.ም ድረስ የመሬት ስርጭት ጉዳይ ጉልህ ሚና አልነበረውም:: በወቅቱ አቶ መሐሪና ጓደኞቻቸው ነገሩን በዝምታ ለማዳመጥ መረጡ:: ነገር ግን እርግጠኞችና መሻሻል የማይታይባቸው ነበሩ::*

*አቶ መሐሪ በጐፋ በሚያገለግሉበት ወቅት በኤስ ኣይ ኤም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሦስት ዓመት አሳልፈዋል:: በቡልቂ የተማሩትን የእነስተኛ ጊዜ ትምህርት ራሳቸው አልጠቀሱትም:: መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር የማያቋርጥ ተግባር እንደሆነ ያውቁ ነበር:: የመገሠጽንና የመቆጣትንም አስፈላጊነት የበለጠ ያውቃሉ:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜያቸው ወጣት ወንጌላውያንን ለማበረታታት እንዴት ይቆጡአቸውና ይገሥጹአቸው እንደነበር ይገልጻሉ::*

*አቶ መሐሪ በልጅነታቸው ጊዜ ከጠንቋይ ጋር ግንኙነት ነበራቸው፣ ነገር ግን በአሪ ጐሳዎች መሃል በነበሩ ጊዜ ግን በግልጽ ፊት ለፊት ይጋፈጡአቸው ነበር:: ያካበቱት ልምድ የሚያገልሏቸው አልነበረም:: ነገር ግን በጐፋ በነበሩበት ዓመት ውስጥ በተደጋጋሚ የተፈጸሙ ናቸው::*

*በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ወንጌላውያን በሚያገለግሉባቸው ቦታዎች በሰዎች መካከል የነበረውን ልዩነት ለማጥበብ ብዙ ታግለዋል:: ፊት ለፊት መጋፈጥ የሚከብድ ቢሆንም፣ የሚፈለግ ነበር:: በውጤቱም አስደናቂ ነገሮችን ለማከናወን ችለዋል::*

# ሩቅ ደቡብ

## ምዕራፍ አሥራ አምስት

እግዚአብሔር ወንጌልን እንድሰብክ ከቁጫ ወደ ጐፋ አውራጃ እንደመራኝ ሁሉ፣ በመጨሻም ሩቅ ወደ ሐመር ባኮ አውራጃ ሄጄ እንድሰብክ መራኝ። በአሪ ጐሳዎች መካከል ይሠራ ከነበረው ወንጌላዊ ጋር ሄጄ እንድሠራም መራኝ።

ወደ ባኮ ለመጀመሪያ ከሚስዮናውያን መድኃኒት ለመግዛት የሄድኩት በ1948 ዓ.ም ላይ ነበር። ያኔ ወንድሜ ዳንኤል አብሮኝ ሄዷል። ወደዚያ ለመድረስ ሦስት ቀን ለመመለስም ሦስት ቀን ነበር የወሰደብን። የመጀመሪያውን ሌሊት ግራሻንጋማ በሚባል ቦታ አደርን። ሁለተኛውን ሌሊት ደግሞ አሪ አይዳ በሚባል ስፍራ ያደርን ሲሆን፣ ሦስተኛውን ሌሊት በባኮ በሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮን ጣቢያ ደርሰን አደርን። በዚያን ጊዜ አቶ አምቦሌ የሚባል ከወላይታ የመጣ ወንጌላዊ ከሚስዮናውያኑ ጋር ይሠራ ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በፊት በሳምባ ነቀርሳ ታምሜ በነበረ ጊዜ በጐፋ አውራጃ ውስጥ ጉያ በሚባለው ቦታ ሆኜ ለጌታ ቃል ኪዳን ገብቼ ነበር።

በመንደሩ አቅራቢያ በሚገኘው ጋራ አናት ላይ ተቀምጬ በአዕምሮዬ ውስጥ መሎ በሚባለው አቅጣጫ ሠላሳ ጸሎት ቤቶችን አየሁኝ። ያን ጊዜ በዚያ አካባቢ የጸሎት ቤቶች በችግር ይመሠረቱ ነበር።

እግዚአብሔር ከዚያ በሽታ እንዲፈውሰኝና ወደዚያ አካባቢ ሄጄ እነዚያ ሠላሳ ማኅበራት እንዲመሠረቱ ለመርዳት እንድችል ጸለይኩኝ።

ልክ በዚያን ወቅት ሚስተር ዲክ ማክሌላን የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናዊ በቡልቂ ነበርና ወደ እርሱ ካስጠራኝ በኋላ፦ «አቶ መሐሪ፣ ምን ብናደርግ ይሻላል? ከወላይታ የመጡ ወንጌላውያን ብሪ፣ ባንገ፣ ዳንኤል፣ ዴንጐ እና ከበደ የተባሉት ወደ አሪ ጐሳ አካባቢ ወንጌልን ለመስበክ ሄደዋል። ዘለቀ ግዛው የሚባለው ሰው ደግሞ እያስፈራራቸው ነው። ዳንኤል ከመደብደቡም በላይ፣ ሁሉም ልብሶቻቸውን ተገፍፈው ተወስደውባቸዋል። በአሪ ጐሳ ውስጥ ወንጌልን ለመስማት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ። ነገር ግን ወንጌላውያኑ ሁሉም ተባረሩ። ምን ብናደርግ የሚሻል ይመስልሃል?» አለኝ።



«የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፣ እኔ ወደ አሪ እሄዳለሁ» አልኩት። «እንዴት ይቻልሃል? ዶክተሩ ለሁለት ዓመት ረዥም መንገድ መጓዝ እንደሌለብህ ነግሮሃል። በቅርቡም በእሥር ቤት ስለነበርክ የሳምባ ነቀርሳህ አልዳነልህም። አሁንም በሽታው በሳምባህ ላይ አለ። ያ ቦታ ደግሞ ለመሥራት በጣም አስቸጋሪ ነው። እንዴትስ ሆነህ እዚያ ሄደህ ለመስበክ ትችላለህ?» አለኝ።

እኔም፣ «የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ እሄዳለሁ፣ እርሱ ጤና ይሰጠኛል፤ የሚፈለገውንም ብርታት እርሱ ይሰጠኛል። ስለ ጤናዬ ብዙም አልጨነቅም» አልኩኝ።

የጐፋ ሽማግሌዎች መማክርት ተሰብስበው ነበር። ሚስዮናዊው ሚስተር ዲክ ማክሌላን ወደ መማክርት ስብሰባ ሄጄ ዘለቀ ግዛው የሚባል የመሬት ከበርቴ ወንጌላውያንን እያሳደደ እንዳለ አካባቢውንም ለቅቀው እንዲሄዱ እንዳዘዛቸው ንገራቸው የሚል ሃሳብ አቀረበልኝ።

«ወደዚያ እንድትሄድ ከጠየቁህም፣ ለእኔ የነገርከኝን አሳብህን ንገራቸው።»

ወደተባለው የመማክርት ስብሰባ ሄጄ ስነግራቸው፣ በጉዳዩ ላይ ተወያዩበት። በብዙ አካባቢዎች ከመንግሥት ባለሥልጣኖች የበለጠ የመሬት ከበርቴዎች ችግር የሚፈጥሩ ናቸው። መጨረሻ የሌለውን ማስፈራራታቸውን ለመቋቋምና ወደ አንድ ውሳኔ ለመድረስ ቀላል አልነበረም።

«ወደ አሪ አካባቢ ሄደህ አራቱ ወንጌላውያን ይሠሩ በነበሩበት ቦታ ለመስበክ ትፈልጋለህ?» ብለው ጠየቁኝ።

ለመሄድ ፈቃደኛ መሆኔን በገለጽኩላቸው ጊዜ፣ ስለ ጤንነቴ ጠየቁኝ። ትንሽ እስክጠነክር ድረስም እንድቆይ መከሩኝ።

«እኔም ከቀን ወደ ቀን እግዚአብሔር ያጠነክረኛል። ወደዚያ እንድሄድም እግዚአብሔር ፈልጐኝ ከሆነ አሁን እሄዳለሁ» አልኳቸው።

### ወደ ደቡባዊ ምዕራብ መዛወር

ወደ ውብሐመር ከመሄዴ በፊት ዳንጎ ሳና የሚባል ሌላ ወንጌላዊ እዚያ ሄዶ እየሰበከ ነበር። እርሱም ለሕዝቡ፣ «መሬትን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። የመሬት ከበርቴዎች ባርያዎች አትሁኑ» እያለ አላስፈላጊ ቅስቀሳ በማድረግ ችግር ፈጥሮ ነበር።

እነዚያ የመሬት ከበርቴዎች ገበሬዎቹን /ጭሰኞቻቸውን/ ግብር ማስከፈል ብቻ ሳይሆን በየሳምንቱ ሰኞና ማክሰኞ እርሻቸውን እንዲያርሱላቸው ከማስገደዳቸውም በላይ በየዓመት በዓሉ ስጦታ እንዲያቀርቡላቸወም ይጠይቃሉ::

የመሬት ከበርቴዎቹ ዳንጐ ሳናን አላሠሩትም፣ ዳንኤልን ግን ደብድበውታል:: ስለዚህም ያንን አካባቢ ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ መሥራት ጀምሯል::

እኔም ወደ ውብሐመር በሄድኩኝ ጊዜ አስቀድመው በሄዱት ወንጌላውያን በሁለት ቦታ ማኅበር /ቤተ ክርስቲያን/ ተመሥርቶ ነበር:: አንዱ ማኅበር ኦልዳማር በሚባል ቦታ የተመሠረተ ሲሆን፣ ሁለተኛ ውም ዚማታር በሚባል ቦታ ተመሥርቷል:: በጐፋ ሰብኩ ዓመት እንደ መኖሬ በዚያ አካባቢ የነበሩት የመሬት ባለሀብቶች ጨካኞች ናቸው ማለት ለእኔ አዲስ አልነበረም:: በብዙ መንገድ በጐፋ ከመሥራት ይልቅ በአሪ መሥራት የበለጠ አደገኛ ነበር::

ሌላው በዚያ አካባቢ ለአገልግሎቴ አስቸጋሪ የሆነብኝ የቋንቋ ችግር ሲሆን፣ በማስተምርበትና በምሰብክበት ቦታ ሁሉ አስተርጓሚ ይገኝ አቆም ነበር:: በወላይታ፣ በጐፋና በቁጫ የቋንቋ ልዩነት ችግር አልፈጠረብኝም:: ነገር ግን ወደ አሪ በምሄድበት ጊዜ አስተርጓሚና[2] መሪ እንደሚያስፈልገኝ ለሽማግሌዎቹ መማክርት ነግሬአለሁ::

የተባለውን ሰው ለማግኘት ለሽማግሌዎቹ ቀላል ባይሆንም፣ በመጨረሻ ግን ዚዶ የሚባለውን ሰው አገኙልኝ:: ይህ ሰው በአሪ ውስጥ ከመጀመሪያ ክርስቲያኖች አንዱ ቢሆንም፣ እኔ አስቀድሜ እርሱን የተገናኘሁት በቡልቂ እሥር ቤት ውስጥ ሆነን ነበር:: የአሪ ቋንቋ ለዚዶ የእናቱ ቋንቋ በመሆኑ ለእኔ ብቁ አስተርጓሚ መሆን ይችላል ብዬ ብቀበልም፣ ከእነዚያ መጨረሻ የሌለውን ችግር ከሚፈጥሩ የመሬት ባላባቶች ጠብ መካከል የገባ መሆኑን ስደርስበት ጭንቀት ውስጥ ገባሁኝ:: እኔም በእንደዚህ ዓይነት አላስፈላጊ ጠብ ውስጥ ሁልጊዜ ተሳታፊ የምትሆን ከሆነ ወደ ፍርድ ቤት ስለምትጠራ የእኔ መሪና አስተርጓሚ ልትሆን አትችልም ብዬው ነበር:: እርሱም ለጊዜው ሙግቱን አቁሞ ሊረዳኝ ወሰነና ረዳኝ:: የዚያን ሽማግሌ እርዳታ ማግኘት ለእኔ ትልቅ ደስታ ነበር::

ወደ አሪ ተጉዘን በሰላም ከደረስን በኋላ አቶ ዚዶ እኔ ለመስበክ በምፈልግበት አካባቢ አብሮኝ እየተዘዋወረ በማስተርጐም ይረዳኝ ነበር::



ባላምባራስ ሐሸታ የሚባሉ ሲረዱን ደስተኛ እንደሆኑ ገልጸው በአሪ አካባቢ በፈለግንበት እየተዘዋወርን ወንጌልን እንድንሰብክ ፈቀዱልን:: ይተባበሩንም ዘንድ እግዚአብሔር ቅን ልብ ሰጥቷቸዋል::

ብዙም ሳንቆይ ሰዎች፣ «እንዴት እናምናለን ? በመሬታችን ላይ ሁል ጊዜ ችግር አለብን:: ይህ ተንኮለኛና ጨካኝ የመሬት ባላባት መሬቱን ለቅቀን እንድንወጣ ነግሮናል:: እንዴትስ ያለማነውን መሬት ጥለን ሄደን ሌላ ጫካ እንደገና ማልማት እንችላለን? እንዴትስ ባልታረሰ መሬት ዘር መዝራት እንችላለን? ይህን መሬት ለቅቀን ከወጣን ለቤተሰቦቻችን ምን እንመግባለን?» አሉኝ::

አቶ ደስታ ጽጌ በዘመኑ የታወቁ የመሬት ባላባትና ሳያቋርጡ ችግር የፈጠሩብን ሰው ናቸው:: ወንድማቸው ሰለሞን ደግሞ ትንሽ ነገሮችን ማገናዘብ የሚችል በመሆኑ መልካም ምክር ይሰጠን ነበር:: አቶ አስፋው የሚባለው ሰው ደግሞ መልካም ሰው ነበር:: ቤአ የሚባለው ሰው ደግሞ ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር::

## የመሬት ስምምነትና ድርድር

የመሬት ከበርቴው የአቶ ደስታ ጽጌ ወንድም አቶ ሰለሞን ጽጌ በወቅቱ የፓርላማ አባል ነበሩ:: ወደ አቶ ሰለሞን ሄጄ በአካባቢው መሬት ተከራይቼ ለመኖር እንድችል አስፈቅዳለሁ ብዬ ለክርስቲያኖቹ አማከርኳቸው:: ደግሞም ወደ ጐፋ ሄጄ ቤተሰቤን ጐብኝቼ ለመመለስ እፈልግ ነበር:: ወደ ቤተሰቦቼ ስሄድ በአሪ ያሉት የአካባቢው ሰዎች ሥራዬን አጠናቅቄ የሄድኩ መሰላቸው እንጂ ወደ አሪ ተመልሼ የምመጣ አልመሰላቸውም ነበር:: በሰላም እንድመለስ ጸልዩልኝ ቶሎ እመለሳለሁ ብዬ አረጋገጥኩላቸው::

ከአንድ የአካባቢው ባለሥልጣን ለአቶ ሰለሞን ጽጌ የመተዋወቂያ ደብዳቤ ወሰድኩኝ:: ነገር ግን ወደ አዲስ አበባ መሄዳቸውን አወቅኩኝ:: ሌላ አባይነህ ንጉሤ የሚባል የሚመራኝን ሰው አገኘሁና ወደ ሌላ የአካባቢው ሹም ወሰደኝ፣ እርሱም ቀረጥ ሰብሳቢ የነበረ ታደሰ አረጋ ይባላል:: እነዚህ ሰዎች የአካባቢ ሰዎች ሲሆኑ ተሰሚነት የነበራቸውና የሚከበሩ ናቸው:: ነገር ግን የመንግሥት ተቀጣሪዎች ስለሆኑ የሚጠሉ ነበሩ::

ይህ አባይነህ የሚባለው ሰው ከእኔ ጋር ለመሄድ ደስተኛ አልነበረም:: ተነሥ እንሂድ ብዬ አደፋፈርኩት::

«ጋሼ የምርህን ነው?» አለኝ፣ በልመና ዓይኖቹ አትኩሮ እየተመለከተኝ::

«እንዴ ለምን? የምሬን ነው እንጂ:: እዚህ አካባቢ አንቁም፣ እንሂድ» አልኩት::

በመጨረሻ ግን ትዕግሥት በማጣቱ ይቅርታ ጠየቅኩት::

«አቶ ሰለሞን ወዲያው ከተናገርነው በኋላ ወደ እኛ ዞሮ ለጥቂት ቀናት እሥር ቤት ያስገባናል:: እሳት በመቀስቀስ እኛው ለራሳችን ችግር እናመጣለን:: እንግዲህ ምን ብናደርግለት ይሻላል? ወደ ቤቱ ባዶ እጃችንን ሄደን መገናኘት እንችላለን? ባዶ እጃችንን ከሄድን ወደ ቤቱ የሚያስገባን ይመስልሃል? ባዶ እጃችንማ ከሄድን እንደሰደብነው ይቆጥርና ምክንያት አድርጎ ሊደበድበን ይችላል» ስለው አባይነህ፣ «ጋሼ ጊዜያችንን በከንቱ እያባከንን ነው» አለኝ::

የአባይነህን ግትርነት እረዳለት ጀመር:: «ለምን እንደምትጨነቅ እየገባኝ ነው:: ቢሆንም እግዚአብሔር እንድንሄድ ከፈለገ ሄደን የምንገናኘውን ሰው ልብ እግዚአብሔር ራሱ ሊያዘጋጅ ይችላል:: ምንም አንፍራ፣ የእግዚአብሔርንም ጥበቃ አንጠራጠር:: ተነሥ መንገዱን አሳየኝና እንሂድ» አልኩት::

አባይነህ ለመሄዱ የጓጓ ልብ ባይኖረውም ትከሻውን አነቃነቀና ጉዞአችንን ጀመርን:: እንደማየው ከሆነ እዚያ ስንደርስ ምን እንደሚጠብቀን ስለማያውቅ ልቡ እየፈራ ነበር:: እኔ ግን ከልቤ ጸለይኩኝ፣ «ጌታ ሆይ፣ ዛሬ ልዩ ጥበቃ አድርግልን:: ይህ ጉዞአችን አባይነህ ያንተን እንክብካቤ እንዳይጠራጠር ትምህርት የሚሰጠው ይሁን» አልኩኝ::

ረዥም መንገድ ከተጓዝን በኋላ፣ በይካ ወደሚባለው ትንሽ ከተማ ደረስን:: በመጀመሪያ ዳር ዳሩን ብንሄድም፣ በመጨረሻ ምርጫ አልነበረንምና በከተማው ውስጥ ዘልቀን ገባን:: የአቶ ሰለሞንን መኖር ለመጠየቅ ወሰንን:: ስንጠይቅም ወደ አዲስ አበባ መሄዳቸው ተነገረን:: ከዚያም መንገዳችንን ወደ ቀረጥ ሰብሳቢው ቤት አደረግን::

አባይነህ በግልጽ ፍርሃት ቢሰማውም ይከተለኝ ነበር:: ወደ በሩ እንደ ደረስን ወደ ውስጥ ተጣራን:: በግቢው ውስጥ ሰዎች ነበሩና ወደ ውስጥ እንድንገባ ጋበዙንና ገባን:: ወደ መቀመጫ /በርጩማ/ አመለከቱንና ተቀመጥን:: በእኛ አካባቢ ወደ ቤት ሲገባ የሁሉንም ሰው



እጅ መጨበጥ ባህላችን ነው፣ እኛ በደረስን ጊዜ ግን ሰዎች ምግባቸውን ለመብላት እጆቻቸውን ታጥበው ነበርና መጨባበጡ አስፈላጊ አልነበረም::

በመንገድ ስንሄድ እኔ ለራሴ፣ «ለምን እንደ መጣንና ምን እንደምንፈልግ ብንነግራቸው ይሻላል:: ምናልባት ቢቆጣንና ቢደበድበን እንኳን ሁሉ ለመልካም እንደሆነ እናውቃለንና ያረካናል::»

የቀረጥ ሰብሳቢው ባለቤት የተቆላ እህል /በቆሎ/ አመጣችና ከፊታችን አስቀመጠችልን::

አመሰገንኳትና:: «እባክሽን፣ ከመብላታችን አስቀድሜ ብጸልይ ቅር ይልሻል? አስቀድሜ ስለ ምግቡ እግዚአብሔርን ሳላመሰግን አልበላም አልኳት::»

ሴትየዋም ወደ ባሏ ተመለከተችና፣ «መልካም ነው፣ ጥሩ ባህል ነው፣ በሉ ጸልዩ» አለችን::

«ጌታ ሆይ፣ ይህንን ምግብ ባርከህ ቀድስልን፣ እንድንደሰትበት ስለሰጠኸን ስለ እያንዳንዱ ነገር በጣም እናመሰግንሃለን:: ይህንን ቀን በሰላም እንድናሳልፍ እርዳን:: በኢየሱስ ክርስቶስ ስም:: አሜን!»

ሴትየዋም ባልዋን፣ «ምን ታስባለህ? በዚህ አካባቢ የሚጸልዩና የሚሰብኩ ሰዎች ሁሉም ታሥረዋል፣ ከአካባቢያችንም እየተባረሩ እየወጡ ነው:: እነዚህ ሁለቱ ሰዎች እዚህ ምን ይሠራሉ? ለምን አልታሠሩም?» አለች::

ባሏ መልስ እስኪሰጣት ድረስ እኛ በፈገግታ የተሰጠንን ቆሎ እንመገብ ነበር::

«አይሆንም፣ እነዚህን የምናሥርበት ምክንያት የለንም:: ይህ ሰው ለብዙ ጊዜ የታሠረ ነገር ግን ተስፋ የማይቆርጥ ነው:: ተስፋ የሚያስቆርጥ አንዳች ምክንያት የለም» አላት::

የተሰጠንን እህል እየተመገብንና ቡናም እየጠጣን የወዳጅነት ጨዋታ ቀጠልን፣ ቀልድና ጨዋታም እያቀላቀልን አሳለፍን::

ቡናው አክትሞ ጀበናውና ሲኒዎቹ ከተነሡ በኋላ ታፈሰ ወደ እኔ ዞሮ፣ «ከየት ነው የመጣኸው?» አለኝ::

እኔም፣ «ከቡልቂ አካባቢ» አልኩት::

የመጣሁበት ትክክለኛ ቦታ የት እንደሆነም ጠየቀኝ:: እኔም የመጣንበትን መንደር /ቀበሌ/ እና የለፈርንበትን የመሬት ባላባት ስም ጠቀስኩለት:: ከመሬት ከበርቴውም ለአቶ ሰለሞን ጽጌ ደብዳቤ ይገና እንደ መጣሁ ነገርኩት::

«ታዲያ እዚህ ለምን መጣህ?» አለኝ::

ከዚህ በፊት ባጋ በሚባል አካባቢ አስተምር ነበር:: እዚያም ብዙ ሰዎች ተምረዋል:: እዚህ አካባቢ ያሉት ሰዎችም መማር ስለሚፈልጉ ላስተምራቸው ነው የመጣሁት አልኩት::

እርሱም፣ «ምናልባት አታውቅም እንጂ፣ እኔ በዚህ አካባቢ የቀረጥ ሰብሳቢ ነኝ» ሲለኝ፣ «ነው እንዴ?» አልኩት:: ድምፄንም በማጉላት መደነቄን ገለጽኩለት:: «እንግዲህ እንተዋወቅ:: እኔ መሐሪ እባላለሁ:: ከተቀመጥኩበት ብድግ አልኩና ጐንበስ ብዬም ቀኝ እጁን በሁለት እጆቼ ጨብጬኩትና የሞቀ ሰላምታ ሰጠሁት:: ሰላም ለእናንተና ለመላው ቤተሰብህ ይሁን ብዬ ሰላምታዬን አቀረብኩለት::»

እርሱም ከእኔ ጋር በመገናኘቱ የተሰማውን ደስታ ከገለጸልኝ በኋላ፣ ለማስተማር ብዙ ሰዎች እንደማገኝ ተስፋው መሆኑን ነገረኝ:: በሁኔታው የወዳጅነት ስሜት ነበረው፣ ስለተገናኘንም ደስተኛ እንደሆነ ነግሮናል:: አሁን ወደ ቢሮው እንደሚሄድም ከነገረን በኋላ በተመቻችሁ ጊዜም ኑና ጐብኙኝ አለን::

## የሥልጠና ልምምድ

ስለነበረን ቃለ መጠይቅ ከልቤ በጣም ደስ አለኝ:: አባይነህና እኔ በኮረብታው ቦታ ወደሚገኘውና ኦልዳሜሪ ወደሚባለው መንደር ለመሄድ ወሰንን:: አንድ የምናውቀውን ሰው ተገናኘንና ውይይት ስንጀምር ሰውየው፣ «ስለተገናኘን ደስ ብሎኛል:: ጥሩ ቀን እንደሚሆንላችሁ ተስፋዬ ነው» አለን ገና ስንገናኝ::

አሁን አባይነህና እኔ እንደገና በሃሳብ በየግላችን ሆነናል:: «እውነት ነው! እግዚአብሔር ዛሬም ከእኛ ጋር ነው:: ይህንን በደንብ አምናለሁ:: ይህ ሁሉ ሕልም ይመስለናል:: እንዴት ሊሆን ይችላል?» አልኩኝ::

«እንዴት ሆነ?» አለና አባይነህ በጥርጣሬ ጠየቀ::

«በጥንት ጊዜ ለአንድ ባለሥልጣን ስጦታ ካላቀረብንለት አያናግረንም:: እንዲያውም ወደ ቤት ግቡ እንኳን አይሉንም:: ዛሬ ግን ይህ ሰው ወዳጅ ሆኖልን እቤቱ ገብተን አብረነው ቡና ጠጥተናል::



የቀድሞ ሰዎች ግን አንድ ነገር ይዘንላቸው ካልሄድን በፍጹም አያነጋግሩንም ነበር:: ወደ ውጪ ጐትተው በዱላ ይደበድቡን ነበር:: ዛሬ ወደዚህ ሰው /ባለሥልጣን/ ቤት በገባን ጊዜ በማንኛውም ደቂቃ ተነሥቶ የሚደበድበን መስሎኝ ጡንቻዎቼ ተኰማትረው ነበር:: ይህ መቼም ተአምር ነው:: በእውነት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነበር:: ዛሬ ረድቶናል» ብዬ አስረዳሁት::

ጸሎቴ ተመልሶልኛል:: ይህ ልምምድ አባይነህን የሚያበረታታው ነበር፣ በእምነቱም በጣም ጠንካራ እንዲሆን ረድቶታል::

በመንገዳችን እየተነጋገርን ተጉዘን ወደ ቤታችን ማታ ደረስን:: ስለ ውሎአችንና ስለ ነበረን ሁኔታ አንሥተን እንጫወት ጀመር:: እግዚአብሔር እንዴት እንደ ረዳንና ከቀረጥ ሰብሳቢው ቤት ስለ ነበረን ውይይት ሁሉ ስናስብ በጣም እንደነቅ ነበር::

ይህ እንግዲህ ባልድማር በሚባለው ቦታ ለሁለት ዓመት ቆይታችን ትርፋማ የነበረ ጅምራችን ሲሆን፣ በመጨረሻም በዚያ አካባቢ ሁለት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ተችሏል:: ቤተሰቤን ወደ አሪ አካባቢ ለማዛወር ሁኔታው የተመቸ ባለመሆኑ በዚያው በጐፋ ውስጥ ባጋ በሚባል ቦታ እንዲቆዩ አደረግሁ::

ሁልጊዜ ስለ ወጣት ጓደኛዬ አባይነህ አስብ ነበር:: በእምነቱ እያደገ መሆኑንም አስተውል ነበር:: እንደ ሌሎቹ የአካባቢው ሰዎች አባይነህም ሁለት ሚስቶች ነበሩት:: አንዷ ወጣትና ቆንጆ ስትሆን፣ የመጀመሪያው ሚስቱ ግን ቁንጅና የሌላትና ወጣትም ያልነበረች ናት::

«ምን ይሻላል? ይህን ሁኔታ በምን መልኩ ማስተካከል እችላለሁ?» እያልኩኝ ያላደገውን ጢሜን መፈተግ ጀመርኩ:: «አባይነህ በእምነቱ እያደገ በመሆኑ አንድ ቀን ለመጠመቅ መጠየቁ አይቀርም:: ለመጠመቅ የሚፈልገው ከወጣቷ ሚስቱ ጋር ቢሆንም ምንድን ነው የማደርገው?»

በጉዳዩ ላይ እያሰብኩበትና እየጸለይኩበት ብቆይም ጥያቄውን ራሱ እስኪያነሣ ዝም ለማለት ወሰንኩኝ::

እውነትም አንድ ቀን አባይነህ ወደ እኔ መጣ:: በእግዚአብሔር ጊዜ ውስጥ እኔም እንዳንተ ወንጌላዊ ለመሆን እፈልጋለሁ:: ይህንን ወንጌል ለሌሎች ሰዎች ማካፈል እፈልጋለሁ:: ወደ አዲስ አካባቢ ሄጄም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች መናገር እፈልጋለሁ አለኝ::

«በጣም ጥሩ ነው:: ይህንን ካንተ በመስማቴ በጣም ደስ ብሎኛል::»

ለማበረታታትና በቅን አሳቡ ላይ እንቅፋት እንዳላኖርበት በጣም እጠነቀቅ ነበር። እንግዲያውስ አዲስ ኪዳን ከፍተን እንማር ብዬ አሳቤን አቀረብኩለት። ያስተማርኩት እያንዳንዱ ነጥብ ለእርሱ አዲስና እንግዳም ሆነበት። እኔ የተማርኳቸውን አንዳንድ ትምህርቶችም አስተማርኩት።

አባይነህ በጊዜው በቀለም ትምህርት ቤት ተምሮ እስከ ሦስተኛ ክፍል የደረሰ ቢሆንም፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም አያውቅም ነበር። ያቀረብኩለት እያንዳንዱ ነጥብ ለእርሱ ምሥጢር ሆነበት። በእርግጥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያምናል፣ በሕይወቱም ውስጥ ብዙ ለውጦችን በማየቱ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነም ተረድቷል። ነገር ግን የተለወጠው ሕይወቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ብዙ አልተረዳም ነበር።

አንድ ቀን ስንወያይ፣ «አሁን አንተ ወንጌላዊ ለመሆን ትፈልጋለህ?» አልኩት።

ምንም ሳይናገር ራሱን አነቃነቀ። ምናልባት ምን እንደምናገረው የተጠራጠረ ይመስላል።

«በየአካባቢው እየተዘዋወርክ ወንጌል ለሕዝብ ለመስበክ /ለማስተላለፍ/ ትፈልጋለህ? ያ መልካም ነው ያንን በመስማቴ ደስ ይለኛል። ይሁን እንጂ በሕይወትህ ለሌሎች እንቅፋት የሚሆን አንድ ነገር አለ። ይህ እንቅፋት የሆነው ነገርህ ደግሞ ሰዎች የምታስተምረውን እውነት እንዳይከተሉ ያደርጋቸዋል አልኩት»።

«እሺ፣ እስቲ ንገረኝ ምንድን ነው እንቅፋት የሆነው?» አለኝ።

እኔም በክርስቲያኖች መካከል ሁለት ሚስት ያለውን ሰው ማጥመቅ በማንኛውም ቦታ የተለመደ አይደለም። ለመጠመቅ ከፈለግክም ከአንድ ሚስት ጋር መኖር ይገባሃል። ከአንድ ሚስትህ ጋር ሆነህ ከተጠመክም በኋላ የጌታን እራት ማለትም /ቅዱስ ቁርባን/ እንድትወስድ ይፈቀድልሃል። ምናልባት ከዚያ በኋላም ጌታ በዚህ አካባቢ ጠንካራ ወንጌላዊ እንድትሆን ሊያደርግህ ይችላል።» አልኩት።

እርሱም በጥሞና ያዳምጠኝ ነበር፣ በፊቱ ላይም አንዳች ቅሬታና የመከፋት ምልክት አይታይበትም ነበር።



«በአሁኑ ጊዜ አንተ ሁለት ሚስቶች አሉህ። ሁለት ሚስቶች እስካሉህም ድረስ ለመጠመቅና የጌታን እራት /ቅዱስ ቁርባን/ ልትወስድ /ልትካፈል/ አትችልም» አልኩት።

ለተወሰኑ ደቂቃዎች አንዳች ቃል አልተናገረም። እኔ ግን፣ «ለምን? ማን ነው ያለው?» እያለ ይጠይቀኛል ብዬ እጠብቅ ነበር።

«እሺ አንዷን ወደ አባቷ /ቤተሰቧ/ ብለድስ?» አለኝ።

በዚህ መልሱ በጣም ተደነቅኩኝ። «ይህማ መልካም አሳብ ነው። ግን የትኛዋን ነው ወደ አባቷ ለመመለስ የምትፈልገው?» አልኩት።

እርሱም፣ «ከመጀመሪያ ሚስቴ ጋር ለመጠመቅ እፈልጋለሁ። ሁለተኛ ዋንና ወጣቷን ወደ አባቷ እሰድዳታለሁ» አለኝ። «አባቷም ሌላ ባል ሊፈልግላት ይቀልለዋል። ምክንያቱም ገና ወጣትና ቆንጆ ነች።» ይህን የሚናገረው ምናልባት እኔን ለማስደሰት ይሆን? ብዬ እትኩሬ እመለከተው ነበር።

«በእውነት አንተ ሁለተኛዋን ሚስትህን ወደ አባቷ መልሼ እሰዳታለሁ ነው የምትለኝ?»

«ትክክል! ሁለተኛዋን ሚስቴን ወደ አባቷ እሰዳታለሁ ምንም ችግር የለም።»

«እውነትህን ነው?» አልኩት።

«አዎን፣ እውነቴን ነው» አለኝ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሁለተኛ ሚስቱን ወደ አባቷ መልሶ እንደሚወስዳት ነገራት። ለዘመዶቹና ለወዳጆቹ ሁሉ ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር እንደሚጠመቅም አስታወቃቸው።

በመጨረሻም ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር በመጠመቅ በአካባቢው ጥሩ የወንጌል አስተማሪ ሊሆን ችሏል።

ያን ጊዜ ባለቤቴ ዮሐንስ የሚባለውን ልጃችንን ወለደች። በዚህም ምክንያት ወደ ቤቴ ተመልሼ ለተወሰነ ጊዜ ከእርስዋ ጋር ለመሆን ወሰንኩኝ። እኔ በምሄድበት ጊዜ ለአባይነህ ጓደኛ ረዳት አገልጋይ ያስፈልገው ነበር። ኤጃት የሚባል ሰው ለአባይነህ ቤት ቅርብ የሆነው እኔ እስክመለስ ድረስ አባይነህን ይረዳው ነበር።

## አባይነህ ብቻውን ሆነ

ወደ አሪ በተመለስኩኝ ጊዜ የጐፋ ሽማግሌዎች ቦርድ ዚማተር ወደሚባለው ቦታ ሄጄ እንድሰብክ ወሰኑ:: ይህም ማለት አባይነህን ለብቻው ትቼው መለየት ማለት ነው:: ትልቁ ችግሩ ምን እንደሆነ ስለማውቅ ከመሬት ከበርቴዎች ጋር ስላለው ባሕርይ አጥብቄ አጠይቀው ነበር::

«ራስህን ከፖለቲካ የለየህ ሁን፣ ያንተ ሥራ ወንጌልን ማስተማርና ሰላምን መከተል ነው:: መጀመሪያ በቀረጥ ሰብሳቢው ቤት በነበርን ጊዜ ያልነውን አስታውስ:: እኛም ስናስተምር ደስ እንደሚለውና የአካባቢው ሕዝብ ቢማር እንደሚደሰት የነገረንን አስታውስ:: ወንጌልን በማስተማር ላይ ጊዜ የምንወስድ ከሆነ ከመሬት ባላባቶች ጋር አላስፈላጊ ጠብ ውስጥ የምንሳተፍበት መንገድ አይኖርም:: የእኛ ተግባር ማስተማር ብቻ መሆን አለበት::» እርሱም መሬት እንዲኖረው የሚፈልግ መሆኑን ስለማውቅ ዕውቀት ከቀሰምክ በኋላ ሌሎች እንደሚያደርጉት አንተም መሬት ለመግዛት ትችላለህ:: ታዲያ ከመሬት ባላባቶች ጋር መጣላትህን አቁም:: እንደዚያ ዓይነት ጥል ለወንጌል ሥራ መሰናክል ይሆናል፣ የግል መንፈሳዊ ሕይወታችንን እንደሚጐዳም እወቅ:: የወንጌል መልእክት የሚተላለፈው በፍቅር እንጂ በጥላቻ አይደለም:: ታውቃለህ? እኔ እዚህ ቦታ የመጣሁት ከመሬት ከበርቴዎች ጋር ለመጣላት ወይም በማንኛውም መንገድ ሥልጣናቸውን ለመቃወም አይደለም:: ከዚህ ቀደም እንደነገርኩህ የእኔ ዓላማ የሕዝቡን ማኅበራዊ ኑሮ ለመለወጥ አይደለም፣ ነገር ግን ከእያንዳንዱ ሰው ጋር በሰላም ለመሥራት ነው:: የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በሰላም ውስጥ ነው:: እኔ የምሰብከው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ብቻ መሆን አለበት:: ሰዎች ከሰይጣን ባርነት ነፃ ሊወጡ የሚችሉት በእርሱ ሲያምኑ ብቻ መሆኑንም እነግራቸዋለሁ:: እንደምታውቀው እኔ የማስተላልፈው መልእክት ይሄ ብቻ ነው:: የክርስቶስ መንግሥትና መልእክቱም ይኸው ነው:: እኔ እንደምረዳው ከሆነ ሌሎች ሥጋዊ ነገሮች የወንጌልን ያህል አስፈላጊ ባለመሆናቸው ከወንጌል መልእክት ጋር መቀላቀል የለባቸውም:: በወንጌል መልእክት ላይ ሌላ ከጨመርን መንፈሳዊውን መልእክታችንን አበላሸነው ማለት ነው::



«እኔ ወደዚህ አካባቢ የመጣሁት ወንጌልን ለማስተማር ነው:: አንተም ተመሳሳይ ተግባር ማከናወን አለብህ:: እኔ ሰዎች በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ እንደሚድኑ አሰብካለሁ:: ከመጽሐፍ ቅዱስም የተማርኩት ይህንን ነው:: ከዚህም የተነሣ ከመሬት ከበርቴዎች ጋር ንብረታቸውን ስለማስተዳደር ጉዳይ እጆቼን ስለማላስገባ ምንም ችግር የለኝም:: ከእነርሱም ጋር የሚያጨቃጭቀኝ አንዳች ምክንያት የለም:: አንተም ሰባኪና አስተማሪ እስከሆንክ ድረስ፣ እንደ እኔ ተመሳሳይ ሥራ መሥራት አለብህ:: በዚህ አካባቢ ከመሬት ባላባቶች ጋር አለመጣላትህ ለአንተና ለጌታ ሥራ የሚበጅ ይሆናል» ብዬ መከርኩት::

አባይነህ ለአያሌ ዓመታት በዚያ አካባቢ ሽማግሌና ወንጌላዊ ሆኖ አገልግሏል:: እኔም ከጐኑ ሆኜ በዚህ አገልግሎት በመሳተፌና በመርዳቴም እጅግ ደስ ይለኛል::

## ከጠንቋዮች ጋር መጋጨት

በደቡባዊ ኢትዮጵያ በብዙ ጐሳዎች መካከል እንደነበሩ ሁሉ፣ በአሪ ሕዝብ መካከልም ብዙ ጠንቋዮች ነበሩ:: እነርሱም በሰዎችና በመናፍስት መካከል የሚያማልዱ ነበሩ:: ጠንቋዮች ወደ መናፍስት ለመቅረብ ይችላሉ ብለው ሰዎች ስለሚገምቱ ራሳቸውን ከሰዎች አርቀው ይታያሉ:: ብዙውን ጊዜ የጠንቋዮች ቤቶች የሚሠሩት ወጣ ባለ /ገለልተኛ/ ቦታ አካባቢ ነው:: በአካባቢያቸው የሚገኙትን ዛፎች ደፍሮ የሚነካ አልነበረም::

በጠንቋዩ መሬት ላይ ዛፍ የሚቆርጥ ሁሉ መጥፎ ዕድል ይገጥመዋል ተብሎ ይገመታል:: ከእነርሱ ጋር ጉዳይ ከሌላቸው በስተቀር ወደ ጠንቋዮቹ ለመቅረብ ወይም በመሬታቸው ላይ እንኳን እንደ ልብ መራመድን ሰዎች አጥብቀው ይፈሩ ነበር::

በተለይም በዚህ አካባቢ አንድ ጠንቋይ በአነስተኛ ኮረብታ ላይ ትልቅ ቤት ነበረው:: በዚያ ኮረብታ ዙሪያ ያለ መሬት በሰይጣን መንፈስ ለእርሱ እንደተሰጠው አድርጐ ያውጅ ነበር:: ሰዎች ሁሉም ከብቶቻቸው ወደ እርሱ መሬት ሄደው ሣር እንዳይግጡ ይከላከሉ ነበር:: በተጨማሪም ዛፍ ከእርሱ መሬት አይቆርጡም፣ ሣርም አያጭዱም ነበር:: ኮረብታው እንዳለ የእርሱ ርስት እንደሆነ ይቆጠር ነበር:: ለእርሻ በጣም ለም ቢሆንም ማንም ሄዶ ለማረስ አይደፍርም ነበር:: የቀረጥ ሰብሳቢው ታፈሰ ይርጋ አንድ አሳብ መጣለት:: ከዚህ ጠንቋይ ከመንግሥት ትእዛዝ ውጪ እጥፍ ቀረጥ ለመቀበልና ወደ

ኪሱ ለማስገባት አሰበ። በግሉ ግን ሕይወቱን ለማዳን ቀጭን ዘንግ የሚያክል እንጨት እንኳን ከዛፎቹ መካከል ለመቁረጥ ይፈራል። ታዲያ ክርስቲያኖች ደግሞ ጠንቋይን እንደማይፈሩ በሚገባ ያውቃል።

አንድ ቀን አንዳንድ ክርስቲያኖችን በአንድ ላይ ጠርቶ፣ «በእግዚአብሔር ታምናላችሁ?» በማለት ጠየቃቸው፣ እነርሱም ራሳቸውን ነቀነቁ። የቀረጥ ሰብሳቢዎች ትእዛዝ ሲሰጡ እንዲ ጥያቄ ሲያቀርቡ አይታዩም ነበር። ደስ የሚለው ግን የመጨረሻ ውይይታቸው ነበር።

«እናንተ የጠንቋዮችን መናፍስት አትፈሩም አይደለም?» አለ። «ትክክል ነው፣ አንፈራም።»

«ደግሞም ለሚቀጥለው ዓመት የምታርሱትን አዲስ መሬት ትፈልጉ የለም?» አለ።

አሁን አድማጮቹ ሁሉ ጥያቄው እየጣማቸው መጣ።

«እኔ አሁን ለሚቀጥለው ዓመት የምታርሉትን አዲስ መሬት ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ። ቢላዋችሁን ስላችሁ እሳት ልቀቁበትና ጫካውን መመንጠርና እርሻችሁን አሁኑኑ መጀመር አለባችሁ። ማንም ሕጋዊ እርምጃ የሚወስድባችሁ ቢመጣ እኔ አለሁላችሁ። ማንም በአካላችሁ ላይ ክፉ ነገር እንዳያደርስባችሁ እኔ እታደጋችኋለሁ። እነዚያ ክርስቲያን ያልሆኑት ሁሉም የፈለጉትን ያህል ቢቆጡ እናንተን አይነኳችሁም። በእውነት ጠንቋዩን ካልፈራችሁት በኮረብታው ዙሪያ ያለውን የጫካ መሬት ሁሉንም ማልማት ትችላላችሁ። ነገር ግን የጠንቋዩ የግል ንብረት የሆነውን ግቢውን ብቻ አትንኩበት።»

ክርስቲያኖቹም በዚህ አባባሉ በጣም ተደሰቱና ተነሣሡ። ክርስቲያን ያልሆኑት ደግሞ በጣም ፈርተው ደነገጡ። እነርሱ የጠበቁት ክርስቲያኖቹ በጠንቋዩ አካባቢ ያለውን መሬት ማረስ ሲጀምሩ እየተቀሰፉ የሚሞቱና ከብቶቻቸውም ሁሉ የሚያልቁባቸው አድርገው ነበር። ይህ ሳይሆን በቀረ ጊዜ አንዳንዶቹ ሄደው የጠንቋዮቹን ባለሥልጣኖች ይጠይቋቸው ነበር። አንዳንዶቹም ምን ነው የመናፍስት ፍርድ ዘገየሳ ይሉ ነበር። ግን ተስፋ አልቆረጡምና ትንሽ ቆይቶ ይመጣል ይባባሉ ነበር። የጠንቋዩንም መናፍስት ከቁጣው ለማብረድ መሥዋዕት ያቀርቡላቸው ነበር።



ለመቁረጥ ከባድ ከሆኑት ከትላልቅ ዛፎች በስተቀር መሬቱ በሚገባ ተመነጠረ። የኮረብታው ዙሪያ ተመንጥሮ አለቀና ቁጥቋጦው ሁሉ ተቃጠለ። ማረስ በሚቻለው ቦታ ሰዎች በሬዎቻቸውን ጠምደው ማረስ ጀመሩ። በበሬ ለማረስ የማይመችውን ቀጥ ያለውን መሬት ደግሞ መደቅደቂያ አበጅተው መሬቱን በእጃቸው መደቅደቅ ጀመሩ።

ክርስቲያኖች ሁሉም አዲስ መሬት አግኝተው ማረስ በመቻላቸው በጣም ደስ አላቸው። ቀረጥ ሰብሳቢውም ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት እንደሚችል ስለሚያውቅ በጣም ተደስቷል። የመንግሥት ባለሥልጣኖች ራሳቸው ጫካ የነበረው መሬት መልማቱን ሲሰሙ በጣም ደስ አላቸው።

የቀረጥ ሰብሳቢው በስውር የጠንቋይ መንፈስ ኃይል እንዲሰበር ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል። ሰዎች በጠንቋይ የማመናቸው ሁኔታ እየቀነሰ መጣ። ለሌላ ለውጥም ግልጽ እየሆኑና ራሳቸውን እያዘጋጁም መጡ። ብዙዎች ወንጌል ቢሰሙም ያመኑት ግን ጥቂቶች ነበሩ።

እኔም ደግሞ በጣም ደስ አለኝ። በኅብረተሰቡ መካከል ወንጌል እንደ ተሰበከ ብዙ ለውጦችም መታየት ጀመሩ።

ጠንቋዮች የሚያደርጉት ድርጊት ወደ እነርሱ ለሚሄዱት ሰዎች ሁሉም የልብ ሰላም ሊሰጣቸው አልቻለም። ጠንቋዮቹም ሰዎች ወንጌልን ለመስማት እንዳይዘጋጁ በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ ይከላከሉ ነበር። የወንጌል ብርሃን በአካባቢው መብራት ሲጀምር የጨለማ ሥራ ሁሉ ተጠርጎ ተወገደ።

እኔም ዚማተር የሚባለውን ቦታ ለቅቄ የሁለት ሰዓት መንገድ ወደ ሆነው ቦይካ ወደተባለው ስፍራ ሥራዬን /አገልግሎቴን/ ለመጀመር ሄድኩኝ።

በዚያ ቦይካ በሚባለው አካባቢ በጣም ታዋቂ የሆነ ቤጃ የሚባል ሰው ነበር። እኔ እዚያ ከመድረሴ በፊት ይህ ሰው ይጠነቁል ስለነበረ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ እየሄዱ ያማክሩት ነበር። እንዲያውም በዚያ አካባቢ ዝነኛ የሆነ ጠንቋይ ነበር። እኛም ለእርሱ ወንጌልን ስንመሰክርለት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አመነና መሬቱን ቆርሶ ሰጥቶኝ እዚያ እስካለሁ ድረስ በመሬቱ እያረስኩ እንድቆይ ፈቀደልኝ።

በቦይካ በቆየሁ ጊዜ ከጐፋ አብሮኝ የሚሠራውን አንድ ሰው አምጥቼ ነበር። ስሙም ካሳ ዌጋ ይባላል። ከጐፋ የሽማግሌዎች

መማክርት አስፈቅጄ ስላመጣሁት ለእርሱ ገንዘብ ለመክፈልም ተስማምተውልኛል:: ለተወሰነ ጊዜም ከእኔ ጋር ሠርቷል:: የሰውዬውን መነሻ አውቅ ነበርና ያመጣሁትም በጣም ልዩ ለሆነ ዓላማ /አገልግሎት/ ቢሆንም የእኔ ዓላማ ግቡን ከመምታቱ በፊት ምን ያህል ችግር እንደሚከሠት ምንም አሳብ አልነበረኝም:: ነገር ግን አብሮኝ ይሠራል፣ ይረዳኛልም በማለት በጣም ተደስቼ ነበር::

## ባለእጆችም ክርስቲያን ሆኑ

በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ጥንታዊ የሆነ ሰይጣናዊ መጥፎ ባህሎች ነበሯቸው:: በኅብረተሰቡም ውስጥ ቀጥቃጮች፣ አናጢዎች፣ ቆዳ ፋቂዎችና ሸክላ ሠሪዎች ነበሩ:: በአራሽ ኅብረተሰብ መካከል የእነዚህ ሰዎች መኖር በጣም አስፈላጊ ነበር:: ነገር ግን በሙያቸው ከማክበር ይልቅ ሲያዋርዷቸው ይታያሉ:: እነዚህ ሰዎች ከአካባቢው እንዳይሄዱባቸው ኅብረተሰቡ በብዙ መንገዶች ይከላከል ነበር::

ከራሳቸው ማለትም ከባለእጅ ቤተሰብ /ወገን/ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ወገን እንዲያገቡ አይፈቀድላቸውም:: ብዙውን ጊዜ የሚተዳደሩት በእርሻ ሳይሆን በሙያቸው ነው:: እነዚያን ሸክላ ሠሪዎች ፉጋ ብለው የሚጠሯቸው ሲሆን፣ ፉጋዎች ደግሞ የቡዳ ዓይን አላቸው ተብሎ ይታመን ነበር:: ፉጋዎች ወደ ሌሎች ሰዎች ቤት በነጻነት እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም:: እነርሱ ያዘጋጁትንም ምግብ ማንም አይመገብም:: ሌሎች ሰዎች እንደሚሸጡና እንደሚገዙ ተመሳሳይ ዕድል አይሰጣቸውም:: ሲሞቱም ለየት ባለ ቦታ ከመንገድ ዳር ይቀበራሉ:: ከሌላው ኅብረተሰብ ቀብር ጋር የመስተካከል መብት አልነበራቸውም:: እንዲያውም በዚያን ዘመን ሰዎች «የሸክላ ሠሪ ሞት ከውሻ ሞት አይበልጥም» ይሉ ነበር::

ዓይኖቻቸው የሰይጣን /የቡዳ/ ዓይን ነው ተብሎም ይታመን ነበር:: አንድ ፉጋ ወደ አንድ ሕፃን ከተመለከተ ሕፃኑ ወዲያው ታሞ ይሞታል ተብሎም ይታመን ነበር:: የተዘጋጀውን ምግብ ከተመለከተ ያንን ምግብ የበላ ሰው ወዲያው ይታመማል ይባላል:: ከዚህም የተነሣ ወደ ማንም ሰው ቤት እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም:: አንድ ዕቃ ሠርተው ካመጡ በተወሰነ ርቀት ላይ ሆነው ይጣሩና ያስረክባሉ እንጂ ደፍረው ወደመጡበት ቤት አይጠጉም:: ሸክላውን ያሠራቸውም ሰው ከቤቱ ወጥቶ ይገናኛቸውና ተገቢውን ሂሳብ ክፍሎ ዕቃውን ይረከባል እንጂ ወደ ቤቱ እንዲገቡ በፍጹም አይጋብዛቸውም:: አንድ ሸክላ



ሠርተው ሲያጠናቅቁ የሚከፈላቸው በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን እህል ነበር:: ከዚህም የተነሣ ምግባቸውን ከኅብረተሰቡ የሚያገኙ ጥገኞች ለመሆን ችለዋል::

ምንም እንኳን እነዚህ ሕዝቦች በኅብረተሰቡ ውስጥ የራሳቸው የሙያ ባለቤቶች ቢሆኑም፣ በሌላ ሥራ የሚያግዛቸው የለም:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሕዝቦች በኅብረተሰቡ ዘንድ ሲገለሉ የማይቻሉና በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: ለምሳሌ፣ እንስራ፣ ማሰሮ፣ የሸክላ ድስት በእነርሱ ይሠራሉ:: እነዚህን ዕቃዎች ኅብረተሰቡ በግድ የሚፈልጋቸው ናቸው:: ፋቂዎች ተብለው የሚጠሩ ቆዳን ፍቀው ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ ተፈላጊ ሙያ ያላቸው ናቸው:: ቀጥቃጮች የሚባሉት ደግሞ ለኅብረተሰቡ የሚያስፈልገውን የእርሻ መሣሪያ ሠርተው የሚያቀርቡ ናቸው:: ያለእነዚህ የእጅ ባለሙያዎች ኅብረተሰቡ ሥራውን ለማከናወን አይችልም::

በዚያ አካባቢ ወንጌልን መስበክ በጀመርን ጊዜ እነዚያን የእጅ ባለሙያዎችን የመለየትና የማግለል ባህል መልካም እንዳልሆነ ለሕዝቡ እናስተምር ነበር:: እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው እኩል አድርጎ ፈጥሯል:: የሁሉም ሰው ሥራ ደግሞ በእኩልነት ቢታይ መልካም ነው:: እነዚህ የእጅ ባለሙያዎች ለኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ሕይወት ጠቃሚዎች እንጂ ጐጂዎች /አደገኞች/ አይደሉም:: እንደ ማንኛውም ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው መቀበል ያስፈልጋቸዋል:: በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ከሆኑም ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ናቸው:: ወደየቤታችን እንዲገቡ መፍቀድ አለብን:: አብረናቸው መመገብ አለብን፣ አብረውን እንዲበሉም መጋበዝ አለብን::

ይህንን ስብከቴን የማያምኑት ሰዎች በሰሙ ጊዜ ፊታቸው በቁጣ ተለዋወጠ፣ ለኅብረተሰቡም ውርደት እንደሆነ ተረጎሙት:: እነዚህን የእጅ ሙያተኞች ከኅብረተሰቡ ጋር ማስተካከል መጥፎ ዕድል የሚያመጣብን ይሆናል ይሉ ነበር:: በመጨረሻም ይህንን ባህል በሙሉ የለወጥን ቢሆንም እስከ ሕይወት ዋጋ አስከፍሎናል::

በዚህ ጅምር ላይ ነበር አንድ አንጥረኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነው:: ከኅብረተሰቡም ብዙም ተቃውሞ አልነበረም:: ቀጥሎም ሌሎች ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ከዚያ አንጥረኛ ጋር ቡና መጠጣት ጀመሩ:: የማያምኑት ሰዎች ደስተኞች ባይሆኑም፣ ጠብ

ለመፍጠር የሚያበቃ ምክንያት ስላልነበራቸው ምንም ማድረግ አልቻሉም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዚያ የፉጋው ልጅ ሞተ፣ ክርስቲያኖቹ ሬሳውን ለየት ወዳለው ቦታ ወስደው ከመቅበር ይልቅ በሰውየው ቤት አቅራቢያ ቀበሩት። መላው የገጠሩ ሕዝብ በቁጣ ከዳር እስከ ዳር ተነቃነቀ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሰውየው ልጅ በዚህ ሁኔታ እንዲቀበር አሳብ ያቀረብነው እኔና የሥራ ጓደኛዬ ካሣ ዊጋ የተባለውና ከሌሎችም ክርስቲያኖች ጋር ሆነን ነው። ይህን ሁሉ ለማድረግ የተስማማነውም ከማያምኑት ሰዎች ለሚደርስብን ቁጣና ተቃውሞ ዝቅተኛ ግምት በመስጠት ነበር።

በአካባቢው ሰዎች እምነት የፉጋው ልጅ ከወትሮው ሁኔታ ተለይቶ በአካባቢው መቀበሩ የገጠሩን ኅብረተሰብ ሕሊና እንደ መበከል ነበር የተቆጠረው። ስለሆነም ከብቶቻችን ይሞቱብናል፣ የእርሻ ሰብሎቻችንም ምርት አይሰጡም የሚል ፍርሃት ነበረባቸው።

ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ በጐፋ ነበርኩኝ። ካሣ መጥቶ በፍጥነት ወደ ጐፋ እንድመለስ ጠየቀኝ። ለእኔ ደግሞ ዓመት በዓል ስለነበር ነበር ወደ ቤተሰቤ ወደ ጐፋ የሄድኩት። ጊዜው በጋ ሲሆን የእህል አጨዳም ወቅት ነበር። እህሌን ለማጨድ ወደ ባጋ መውረድ ነበረብኝ። ካሣ መጣና የሆነውን ሁሉ ነገረኝ።

«ክርስቲያን ያልሆኑት ሁሉ በእሑድ ቀን ተሰብስበው ንብረታችንን ለመዝረፍ፣ ከብቶቻችንን ለማረድ፣ እርሻዎቻችንን ለማውደምና እኛን ከአገር ለማባረር ተስማምተዋል። ከፍተኛ ውጊያ ሊጀመር ነው፣ ተነሥና ምን ማድረግ እንደምትችል እስቲ እይ» አለኝ ካሣ።

እኔም፣ «ምን ባደርግ ይሻለኛል?» ብዬ ለራሴ አሰብኩኝ። «ቦታው ደግሞ የሙሉ ቀን ጉዞ ነው። መላው የገጠሩ ሕዝብ ከተነሣብን እኔ አንድ ሰው ምን አድርጌ ይሆን ልረዳ የምችለው?» ብዬ ተጨነቅኩ።

በዚህን ጊዜ የመንግሥት ባለሥልጣኖች እገዛ ያስፈልገናል ብለን ወሰንን። ምክንያቱም ይህ የሃይማኖት ችግር ሳይሆን ማኅበራዊ ችግር ነው። ሕግን የሚጻረር ነገር ምንም አልሠራንም። በዚህን ወቅት የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ከጐናችን ለማድረግ መቻል እንደነበረብን ተረዳን።



እኔና ካሣ ሁለታችንም የተፈጠረውን ሁኔታ በጽሑፍ ለመንግሥት ባለሥልጣኖች አስታወቅን። በዚያ አካባቢ ለነበሩት ባለሥልጣኖች ትእዛዝ አስተላልፈው ችግሩ እንዲፈታ እንዲያደርጉልን ጠየቅናቸው። ባለሥልጣኖቹም ማመልከቻችንን ተቀብለው ያፀኑ መሰሉ። በዚያን ጊዜ የጐፋ ሽማግሌዎች መማክርት ተሰብስበው ስለነበር እኔም ወደ እነርሱ ገሠገሥኩ። ምን እንደ ተፈጠረ ከነገርኳቸው በኋላ እንዲጸልዩልን ገልጸን ጉዞአችንን ቀጠልን።

እኔም ታላቅ ልጄን ይገፔ ከካሣ ጋር ሦስት ሆነን ወደ ቦይካ ተጓዝን። ወደ አካባቢው እንደ ደረስን ከመካከላችን አንድ ሰው የመሬት ከበርቴ ወደ ነበሩት ወደ አቶ ደስታ ጽጌ ሄዶ እንዲያነጋግራቸው ተስማማን። እኚያ ሰው ቀደም ሲል በክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ ችግር ያደረሱ ነበሩ።

እኔ ወደ ቤታቸው እንደ ደረስኩም የመሬት ከበርቴው አቶ ደስታ ጽጌ፣ «ደህና ነህ? ቤተሰብህ ደህና ነው? ከተያየን ብዙ ጊዜ ሆነን እኮ» አሉኝና የሞቀ ሰላምታ አቀረቡልኝ።

ሁሉ ነገር ደህና መሆኑን ነገርኳቸው። እጅ ለእጅ ከተጨባበጥን በኋላ፣ «ትንሽ ችግር አጋጥሞናል» ብዬ ስለሆነው ሁሉ በዝርዝር ነገርኳቸው።

እርሳቸው በሃዘኔታ ካዳመጡኝ በኋላ፣ «ሰዎች ሁሉ እኩል እንደሆኑ ማስተማራችሁ ከሕግ ውጪ አያደርጋችሁም፣ ማንም እንዳይነካችሁ አደርጋለሁ» ብለው አረጋገጡልኝ።

ከዚያም የአካባቢው ሹምና ዳኛ ወደሆኑት ሰው ሄድን፣ ስማቸውም አቶ አስፋው ይባላል። የአባታቸውን ስም አላስታውስም። እኔም ሰላምታ ስሰጣቸው እጃቸውን መለሱልኝና ስለ ራሴ ጤንነት በመጠየቅ የሞቀ ሰላምታ ሰጡኝ።

ከጥቂት ጊዜ በፊት ለአቶ አስፋው መጽሐፍ ቅዱስ ሰጥቻቸው በጣምም ተመስጠው መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንደሚያነቡና ብዙም ትምህርት እንዳገኙበት ነገሩኝ።

እኚህ ሹም፣ «ምንም ስሕተት እንዳልሠራችሁ አውቃለሁ። ማንም ሰው ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳያደርስባችሁ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ አሉኝ። በእናንተ በኩል ግን ምንም ፍርሃት አታሳዩአቸው።

እናንተም ደግሞ በማንኛውም መንገድ አትተንኩሱአቸው /አታናድዷቸው/» አሉኝ::

ከዚያም እንደገና ወጥተን ሄድንና ሰዎች ለቀብር ወደተሰበሰቡበት ቦታ ደረስን:: ያኔ እኔ በጣም የድካም ስሜት ነበረብኝ:: ሰዎቹም፣ ምን ነው? ምን ሆነሃል? ከየትስ መጣህ?» አሉኝ::

እኔም ከቡልቂ መምጣቴን ነገርኳቸው:: እነርሱም ከሩቅ ቦታ በአጭር ጊዜ ገስግሰን በመምጣታችን በጣም ተደነቁ::

«አሁንስ ምን ልታደርግ ነው?» ብለው ጠየቁን::

ምን እንደምናገር ሳላውቅም ሁልጊዜ ሳላቋርጥ በልቤ እጸልይም ነበር:: የገጠሩ ሕዝብ ሁሉ ክንዱን በእኛ ላይ እያነሣ መሆኑ ግልጽ ነበር:: እንዲያውም በዚያ አካባቢ የሚሰበከው የወንጌል አገልግሎት መጨረሻው የቀረበ ይመስል ነበር። የአካባቢው የመሬት ከበርቴ ወይም ባለቀሳድ የምንላቸው ሰው በቀብሩ ላይ ነበሩ:: እኔን ሲመለከቱኝ በጣም መድከሜን ተመለከቱና፣ «ተቀመጥ፣ ቡና ጠጥተህ ትሄዳለህ» አሉኝ::

ከዚያም፣ «በጣም የደከመው እንግዳ መጥቷልና በፍጥነት ቡና አፍልተሽ አምጪ» ብለው ወደ ባለቤታቸው ላኩ።

መግደርደር ሳላስፈለገኝምና «በጣም አመሰግናለሁ:: ነገር ግን በጣም እቸኩላለሁ:: አስቸኳይ የሆነ ቀጠሮ አለኝ:: እዚያው መገኘት ይገባኛል» አልኳቸው::

እርሳቸውም ፈቀዱልኝና ጉዞ ጀምረን ወደ በይካ አቅራቢያ ደረስን። ወደ አቅራበያው ጸሎት ቤት ሄደን ስንገባ የሚከተለን ችግር በግልጽ ታይቶኛል:: በአጠቃላይ ምን እንደምናደርግ ባይገባኝም ማድረግ የምችለው ነገር ቢኖር በዝምታ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመራን መጠበቅ ብቻ ነው።

ወደዚያ የደረስኩት ቅዳሜ ማታ ሲሆን፣ የአካባቢው ሰዎች ሁሉም ተመልሼ መምጣቴን ሰሙ:: የሚቀጥለው ማግስት (እሑድ ቀን) ሁኔታው እጅግ አሳሳቢ እንደሚሆን ብረዳም ምን እንደምናደርግና ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንደሚገባኝ ጌታ አላመለከተኝም።

## በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሆነው ተአምር

በማግስቱ በጠዋት ወደ ጸሎት ቤት ሄድኩኝ:: ሌሎች ምእመናንም እንዲሁ ተገኝተው ነበር:: የመጡት ሰዎች ብዙ ሳይሆኑ ጥቂቶች ነበሩ::



ቀስ በቀስ የማያምኑት ሰዎች ከጸሎት ቤቱ ውጪ መሰብሰብ ጀመሩ:: ብዙዎቹ ዱላዎቻቸውን ይዘዋል:: አንዳንዶቹ ደግሞ ጫካ የሚመነጥሩበትን ረገቭቭርም ገጀራ (ቆንጨራ) ይዘዋል።

«እንኳን ደህና መጣችሁ:: ለምን ከውጪ ትቆማላችሁ ግቡና ተቀመጡ» ብዬ እንዲገቡ ጋበዝኳቸው::

ያን ጊዜ ሁሉም ተደነቁ:: እኔ ግን እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንዳለብኝ እንዲያመለክተኝ በልቤ በቅንነት እጸልይ ነበር:: እነርሱ ደግሞ ሊያጠቁን በጣም ትንሽ ሰበብ እንደ ፈለጉ በጣም እርግጠኛ ነበርኩ። ሁኔታቸውን ስረዳ ከፍተኛ አደጋ ሳያደርሱ ወይም የተወሰኑ ሰዎችን ሳይገድሉ የሚመለሱ አይመስሉም:: በእኛ በኩል ደግሞ አንዳች አደጋ ቢያደርሱብን ምንም ለመከላከል እንደማንችል እናውቃለን:: አንድ ዱላ እንኳን በአጠገባችን አልነበረም።

«ታዲያ እንደምን ናችሁ? ስለመጣችሁ በጣም ደስ ብሎናል» አልኳቸው::

በልቤ ደግሞ እጸልይ ነበር:: «ጌታ ሆይ፣ እዚህ ቦታ አንተ የጀመርከውን ሥራ እነዚህ ሰዎች እንዳያፈርሱ ለክብርህ ብለህ አንተው ተከላከልልን» አልኩኝ።

በጸሎት ቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎችም ከበስተውጪ የተሰበሰቡት ሰዎች ወፋፍራም ዱላ እና ቆንጨራ መያዛቸውን አስተዋሉ።

ሁሉም እንደ ፈሩ አውቃለሁ:: ለእያንዳንዳቸውም ምን መናገር እንዳለብኝ ስለማላውቅ በልቤ እጸልይ ነበር:: ምንም መናገር ባለመቻሌ በጸጥታ በልቤ መጸለዬን ቀጠልኩ:: ሰዎቹም በውጪ በያሉበት ቦታ ምንም ሳይናገሩ መቀመጥ ጀመሩ:: ቀስ በቀስ ደግሞ ያልገቡት ክርስቲያኖች አንድ በአንድ እየመጡ በመግባት የጸሎት ቤቱን ሞሉት።

ከእነዚያ ከማያምኑት መካከል አንድ ሰው፣ «የመዝጊያውን እንጨት ከየት አገኘህ?» አለኝ::

በሩ በጣም ጠንካራና ሰፊ በሆነ እንጨት በልዩ ዘዴ የተሠራ ሲሆን፣ ለዚሁ ቤት በር እንዲሆን የሰጡኝም የመሬት ከበርቴው ናቸው።

«በዚህ አካባቢ አንድ ሹም (የመሬት ከበርቴ) ብቻ እንዳሉ ታውቃለህ:: በሩን የሠራሁበትን ዛፍ እርሳቸው ናቸው የሰጡኝ::»

«እናጢውም በጣም የተሳለ ፋስና መጥረቢያ ተጠቅሞ በመላጊያ ልጎ በማለስለስ ሠርቶታል» ብዬ መለስኩለት:: በሩ የተዋበ በመሆኑ

በርግደው በመስበር ደብድበውን በሩን ይዘው የሚሄዱ መስሎኝ ነበርና አሁንም ምን እንደማደርግ አልገባኝም ነበር።

ከውጪ አንድ ሰው ወደ ጸሎት ቤቱ ሰተት ብሎ ገባ:: እርሱም ከማያምኑት አንዱ ነው:: የጋለ ሰላምታ ሰጠሁትና በመቀመጫዬ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ጋበዝኩት:: ሰላምታዬን ከተቀበለ በኋላ ለመቀመጥ ፈቃደኛ አልሆነም:: ነገር ግን ወደ ኋላ ቆም በማለት የተቀመጡት ሰዎች ወደ ውጪ እንዲወጡ በአንገቱ ምልክት ይሰጣቸው ጀመር::

አብረውት የነበሩት ሁሉም በተረከዛቸው ቁጢጥ በማለት በዝግተኛ ድምፅ ይነጋገራሉ:: እኛም ከውስጥ ሆነን የእሑድ አምልኮት ሥርዓታችንን ለማካሄድ ወሰንን:: እየዘመርንና እየጸለይን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በምናጠናበት ወቅት ከውጪ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች ቀስ በቀስ እየተነሡ ሄዱ::

አሁንም ምንም ሳያደርጉን መሄዳቸው ለምን እንደሆነ ባይገባንም እፎይታ አገኘን:: ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሰላም ሰፈነልን።

ያን ጊዜ አቶ ሰለሞን ጽጌ ከአዳስ አበባ መመለሳቸውን እንደ ሰማሁ አሁንም ሌላ ችግር እንደሚከሠት አረዳ ነበር።

አቶ ሰለሞን እንደተመለሱም የፈራነው አልቀረልንም:: እነዚያ የማያምኑ (ክርስቲያኖች ያልሆኑ) ሰዎች የክርስቲያኖቹን ንብረት ይዘርፉ ጀመር።

## ሌላው ማመልከቻ

እኔ በምኖርበት በባጋ የአቶ ሰለሞን ዘመድና የእኔ ወዳጅ የነበረ የቀረጥ ሰብሳቢ ነበር:: ምናልባት ሊረዳን ይችላል ብዬ አሰብኩኝ። የሆነውን (የደረሰብንን) ሁኔታ ሁሉ በዝርዝር በመግለጽ የክርስቲያኖች ንብረት ሁሉ መዘረፉንና አቶ ሰለሞንም ሁኔታውን ለማረጋጋት የወሰዱት እርምጃ አለመኖሩን ከገለጽኩኝ በኋላ፣ ቀረጥ ሰብሳቢውን የእነዚህ ንጹሐን ሰዎች ንብረት እንዳይዘረፍና ከብቶቻቸውም እንዳይታረዱባቸው የሚል ደብዳቤ ጻፍኩለት::

በተጨማሪም ቼስትሪ በሚባል ቦታ አንድ ሰው ሦስት ከብቶቹ ተወስደውበታል፣ ሌላኛውም ሁለት ፍየሎች የተወሰዱበት ሲሆን፣ ከአንድ ቤት ደግሞ ሦስት በጎች ተዘርፈዋል።



«ይህ ሁኔታ እንዲህ ከቀጠለ፣ በክርስቲያኖችና ክርስቲያኖች ባልሆኑት ሰዎች መካከል ከፍተኛ ውጊያ ይቀሰቅሳል:: ውጊያውም ብዙ አደጋና ሞት ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑ በስተቀር የሚጠቅም ወገን አይኖርም» በማለት ገለጽኩኝ:: «ክሳችንን መቀጠል እንችላለን:: ማመልከቻችንም እስከ አዲስ አበባ ሊደርስ ይችላል::»

ይህን ከፍተኛ ጠብና ዝርፊያ ለማብረድ ዘመዱ ሰለሞን አንድ እርምጃ እንዲወስድ በማድረግ እንዲረዳን ተማጸንኩት:: በባጋ የነበረው የቀረጥ ሰብሳቢ ጥሩ ደብዳቤ ለሰለሞን ጽፎ ላከልኝ::

ይህን ደብዳቤ ለአቶ ሰለሞን እንዲሰጥልን ዘለቀ የሚባል ሰው መረጥን:: አቶ ሰለሞን ደብዳቤው ደርሶት ካነበበ በኋላ እኔን አስጠራኝ ና ወደ እርሱ ሄድኩኝ።

ያኔ አቶ ሰለሞን ልጅ ሞቶበት በለቅሶ ላይ ነበርና መልእክተኛው ሄዶ የእኔን መምጣት ነገረው:: ወዲያውም ወደ ቤት እንድገባ ተነግሮኝ ስገባ ሰውየው ከዘመዶቹ ጋር ተቀምጦ ይስተዛዘን ነበር። ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ከተቀመጥኩኝ በኋላ አቶ ሰለሞን ምልክት ሰጠኝና፣

«ዛሬ እዚህ ብዙ ሰዎች አሉ:: ስለ ደብዳቤህ ለመነጋገር አይመችም:: የሐዘኑ ሥርዓት ዕሮብ ዕለት ስለሚያበቃ፣ አንተ ሐሙስ ጠዋት ተመልሰህ ና» አለኝ::

እኔም ስለ ቀጠሮው አመስግኜው በባህላዊ መንገድ፣ «እግዚአብሔር ያጥናህ:: እግዚአብሔር ያበርታህ» ብዬው፣ «አሜን፣ አሜን» ብሎኝ ተሰናብቼ ሄድኩኝ::

በመልካም መግባባት ስለተሰነባበትን ሐሙስ ቀን በቀጠሮአችን መሠረት ስሄድ ጥሩ ቃለ መጠይቅ እንደሚያቀርብልኝ እተማመን ነበር።

ሐሙስ ዕለት ወደ ቤቱ እንደ ደረስኩ አቶ ሰለሞን፣ «እንደምን ነህ? ደህና ነህ? ሥራህስ እንዴት ነው?» ብሎ የሞቀ ሰላምታ አቀረበልኝ:: እኔም ስለ ልጁ አሟሟት ጠየቅኩት:: ስለ አዲስ አበባ የፓርላማ ተሳትፎውም ጠየቅኩት።

«በዘለቀ የላክህልኝ ደብዳቤህ ደርሶኝ በጥንቃቄ ተመልክቼዋለሁኝ:: እንደተረዳሁት ከሆነ ከወንድሜ ከደስታ ጋር ችግር እንዳለህ አያለሁ:: አሁንም እርሱ ችግር እየፈጠረብህ ነው? ወይስ የነበራችሁን ችግር አስወግዳችኋል?» አለኝ:: ስለ ራሱና ራሱ ስለፈጠረው ችግር ግን

እንዳት ለመተንፈስ አልፈለገም:: እርስ በርሳችንም ደግሞ ተነቃቅተናል። አንተ አንተ እንዳንባባል ወይም በመካከላችን መግባባት እንዳይጠፋ ሦስተኛ ሰው አስቀምጠናል።

«ደስታ ምንም ችግር አልፈጠሩብንም:: የሰው ፍጡር ሁሉ ሊሳሳት እንደሚችል አሳምረው ያውቃሉ:: እኛም የችግሩ መንሥኤ አይደለንም:: ስለ አገራችን ደኅንነት በጣም እናስባለን። በጊዜው ክርስቲያኖች ከሌላ አቅጣጫ ችግር ሊከሠትባቸው ነው:: ስለዚህም ነው እርዳኝ የምለው::»

«እኔ መቼም ሁልጊዜ ልረዳህ ፈቃደኛ እንደሆንኩ ታውቃለህ:: በአዲስ አበባ ፓርላማ ለመገኘት የቻልሁት በዚህ ሕዝብ ተመርጬና በእነርሱም ተወክዬ ነው:: ለዚህ ሕዝብ ከእኔ ውጪ ከልብ የሚያስብላቸውም የለም:: እናንተ ክርስቲያኖችም ሰዎችን ለማስተማር እንደምትፈልጉ አውቃለሁ:: ሰዎች በእኩልነት እንዲታዩ ትፈልጋላችሁ:: ችግር አልፈጠራችሁም:: ከዚህ ቀደም እንደነገርኩህ በመሬት ከበርቴውና በገበሬው መካከል ችግር አትቀስቅስ» ሲለኝ በውስጤ በጣም ደስ አለኝ:: በመልካም አቅጣጫ እየተጓዝን እንደነበረም አወቅኩኝ:: ስለ ሁኔታው ደጋግሞ ተናገረ:: ፖለቲከኛ ሆኖ የተወለደም ይመስላል::

«አንተ ወንጌላዊ እንጂ የፖለቲካ ሰው አይደለህም:: የመሬትን ስርጭት ማከናወን የፖለቲከኞች ሥራ ነው:: ያ የአንተ ችግር አይደለም:: አንተ ዝም ብለህ የእግዚአብሔርን ቃል ስበክ እንጂ በሌሎች ጉዳዮች ተሳታፊ አትሁን::»

እኔም በአሳቡ ተስማምቼ ይህ የእኔም ዓላማ መሆኑን ነገርኩት:: ምናልባት ሰዎች መሬትን ስለማከፋፈል አንሥተው ከሰሰውኝ እንደሆነ ጠየቅኩት።

«አንተ ዝም በልና ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ስበክ:: ይህ መልካም ነው:: እኔም በኅብረተሰቡ መካከል የበላይ ሆነው ለመኖር የሚፈልጉ ጠንቋዮች ሲጠፉ ማየት እፈልጋለሁ:: የእነርሱ ጥንቆላና የበላይነት ለማንም አልበጀም:: አንተ ስብከትህን ብትቀጥል ግን የሚመጣ ችግር የለም:: እኔ እዚህ እስካለሁ ድረስ በፈለግክበት መንደር እየተዘዋወርክ የመስበክ ነጻነት አለህ:: ሌሎች ሰዎች ለሥራህ መሰናክል እንዳይሆኑብህ እኔ እያለሁ ብቻ ደጋግሜ ነግሬሃለሁ:: አንተም ሆንክ ሌሎች ክርስቲያኖች ከፖለቲካ ጉዳዮች ራቁ» አለኝ።



ይህን መናገሩ እውነቱን ሲሆን፣ የነበረው ችግር ሁሉ ቆመ:: ለረዥም ጊዜያት የክርስቲያኖች ኅብረት አልተዘረፈባቸውም:: ጌታ ያንን ችግር ስላስወገደልን በጣም ደስ አለኝ:: ኅብረታቸው እንደማይዘረፍ ማረጋገጫ ሲያገኙ ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቲያኖች እምነት ለመምጣት ፈቃደኞች ሆኑ።

## የሕዝብ ሁከት

በእርግጥ ተቃውሞ የለንም ማለት አይደለም:: በዚህ ጊዜ ልጄ አድነ ከእኔ ጋር አብሮኝ ይዘዋወር ነበር:: ጣኒባል ወደሚባል ቦታ ለመስበክ ሄድን:: የአካባቢው ሰዎችም እዚያው ቆይተን እንድንሰብክ ፈቀዱልን:: «ማዳን የሚችለው ጌታ ኢየሱስ እንጂ ጠንቋዮች አይደሉም:: እርሱን ብቻ ለማምለክ ፈቃደኛ ብትሆኑና ብታምኑት ከፍርሃታችሁ ነፃ ሊያወጣችሁ ይችላል፣ ብትክዱት ደግሞ ይፈርድባችኋል። እርሱ አዳኝ ብቻ ሳይሆን ፈራጅም ነው:: እርሱን እንደ አዳኛችሁ አድርጋችሁ ከተቀበላችሁት ደግሞ አይፈርድባችሁም» አልኳቸው::

ሰዎቹም እንዲህ ዓይነት መልእክት ከዚህ በፊት ሰምተን አናውቅም አሉ። የወንጌል መልእክት በእውነትም ለሁሉም እንግዳ ነበር። በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑም ጠየቅኳቸው::

«ይህንን ትምህርት ለመስማት የሚፈልጉ ከመካከላችሁ አሉ? በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታምናላችሁ? እርሱን ለመቀበልና ለማምለክ ተዘጋጅታችኋል?» አልኳቸው:: «ይህንን ትምህርትህን ለመስማት አንፈልግም» ብለው መለሱልኝ:: እኔም መልሼ፣ «ለመስማት ካልፈለጋችሁ እሺ. እኛም ወደ ሌላ አካባቢ ሄደን ለሚሰሙን እንሰብካለን» ስላቸው።

«መስማት አንፈልግም» ብለው መለሱልኝ:: ከዚያ በኋላ በእኛ ላይ ጭካኔ ማሳየት ጀመሩ:: ሌቦች፣ ለማኞች፣ ነፍስ ገዳዮች ብለውም ሰደቡን::

ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይሰድቡን ነበር:: አንዳንዶቹም ድንጋይ አንሥተው ወርውረውብናል፤ በብዙ መንገዶች የማይመቹና የማንቀርባቸውም ነበሩ።

ያኔ ከእኔ ጋር ልጅና ሌላው ከአሪ ጎሳ የሆነ ጴጥሮስ የሚባል አብረውኝ ነበሩ። ጴጥሮስ መሪዬና አስተርጓሚዬም ነበር። እርሱም ዚ.ማተር ከሚባል ቦታ ነበር አብሮኝ የመጣው።

በአሪ ውስጥ አልኮል መጠጣትና መስከር የተለመዱና ሕዝቡን አንድ ያደረጉ ማኅበራዊ ትስስሮች ናቸው። እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ መጠጣትን ስለምንቃወም የማኅበራዊ ኑሮ ጸሮች ናቸው ይሉናል። አለመጠጣታችን በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደ መጥፎ ባህል ተወስዷል። አንድ ቀን ከምንሰብክበት ስንመለስ ሰዎች ተሰብስበው ወደሚጠጡበት ስፍራ ደረስን። «ኑ ና ጠጡ» ብለው ጋበዙን።

«እኛ አልተጠማንም ምንም ለመጠጣት አንፈልግም» ስንላቸው፣ «እንግዲያውስ ለመጠጣት ካልፈለጋችሁ ምርጫው የእናንተ ነው» አሉን። «ግን ይህ ልጅ ጴጥሮስ አስቀድሞ ከእኛ ጋር ይጠጣ ነበርና አሁን መጠጣት አለበት» አሉና የተወሰኑ ሰዎች ዘለለው አነቁት። ሌሎቹ ደግሞ በመሬት ላይ በግድ ሲያጋድሙት የተቀሩት አፉን ከፍተው የአልኮል መጠጡን ይግቱት ጀመር።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሌሎች ሰዎች ደግሞ እየረበሹን ያስጨንቁኝና ያስፈራሩኝ ነበር። ጴጥሮስ ግን በመሬት በወደቀበት ከታገላቸው በኋላ በመጨረሻ አመለጣቸውና ከፊታቸው ሸሸ። ከሰዎቹ አንዳንዶቹ ወፍራም ዱላ የያዙ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ረዥም እጀታ ያለውን የሣር ማጨጃ ቆንጨራ ይዘዋል። ዱላቸውን አዘጋጅተው ቆንጨራቸውን እያፏጩ ጴጥሮን ተከተሉት።

በዚያ ግብግብ መካከል ጴጥሮስ ተለይቶኝ ነጎደ። በልቤ ግን እግዚአብሔር እንዲታደገውና እንድንገናኝ እጸልይ ነበር። እኔን በሌላ አቅጣጫ ሲያባርሩኝ፣ እርሱንም በሌላ አቅጣጫ ያባርሩት ነበር። እርሱን አባርረው ለመያዝ ፍላጎት አልነበራቸውምና ወዲያው ተመለሱና መጠጣታቸውን ተያያዙት። ጴጥሮስም ሸሽቶ ለመደበቅ ቻለ። ብዙ የተለያዩ ሰዎችን ካጠያየቅኩኝ በኋላ በመጨረሻ የተደበቀበትን ቤት አመለከቱኝ። ለቤቱ ባለቤትም ራሴን አስተዋውቄው ጴጥሮስን እንደምፈልገው ነገርኩት።

«ሰዎች ለምን ይቆጧችኋል? የሰረቃችኋቸው ነገር አለ እንዴ አለኝ?» ሰውየው።

እኔም፣ «እኛ ሌቦች አይደለንም፣ የማንንም ንብረት አልነካንም» አልኳቸው።



በዚህን ጊዜ እነዚያ ሰዎች ዙሪያችንን ከብበው ሁኔታውን ይከታተሉ ነበር። እኛ ወንጀለኞች አለመሆናችንን ለሰውየው ገለጽን።

ወንጌልን ለመስበክ ብቻ የመጣን መሆናችንን ባስረዳነው ጊዜ ሰውየውም ለተሰበሰቡት ሰዎች፣ «እነዚህ ሰዎች ወንጀለኞች አይደሉም። እንዴት እንደ ሌባ ታባርሩአቸዋላችሁ? ይህን ልጅ (ጴጥሮስን) አሁን ተውት አትንኩት። ምን እንደሚሰብኩ እኔ ሰምቼአቸዋለሁ። ለትምህርታቸውም ትኩረት በመስጠት እያሰብኩበት» ነው አላቸው።

ሰዎቹም በገለጻው ረክተው ጴጥሮስ ከተደበቀበት እንዲወጣ ሆነ። ለሁሉም ሰላምታ ከሰጠን በኋላ ወደ ጣኒባል ተመለስን። ነገር ግን በሰዎቹ አዕምሮ የነበረው አሳብ አብረዋቸው የማይጠጡ ሰዎች የማኅበራዊ ኑሮአቸው ጸሮች እንደሆኑና ለኅብረተሰቡም መጥፎ ዕድል የሚያስከትሉ ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ውስጣቸው ደስተኛ አልነበረም።

## የሕግ ክስ

ዳግመኛ ለመተንኮስና ድንጋይ እስኪወረውሩብን ድረስ እኛም ነገር ለመፈለግ አልፈጠንንም። ነገር ግን መጥፎ ዕድለኞች ከዚህ ሊዱልን ይሉን ነበር።

እኛ ቻል ብለናቸው በነበርን ሰዓት ከጎዛ ከተማ አንድ ፖሊስ መጥቶ ተቀላቀላቸው።

«አንተ ባርኔጣ ያደረግክ ሰው! ቁም! ቁም! በሕግ አምላክ በባንዲራ አምላክ! ትሰማኛለህ? ቁም!» አለኝ። እኛም አቆምንና እስኪይዙን ጠበቅናቸው።

«እዚህ ምን ትሠራለህ? ለመሆኑ ከየት ነው የመጣኸው?» እያለ ለማወቅ ጠየቀኝ።

እኔም ወንጌላዊ መሆኔንና ከቡልቂ መምጣቴን እዚህ በአሪ ወንጌል እየሰበክሁ ያለሁ መሆኔን ነገርኩት።

«ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ መሆንህን የሚገልጽ ሕጋዊ የፍቃድ ወረቀት ይዘሃል?» ሲለኝ፣ «አዎን፣ ወረቀቱ አለኝ» አልኩት።

በዘመኑ የፍቃድ ወረቀት ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር። እንደዚያ ዓይነት ወረቀት ማግኘት የተዘጋ ነው።

«ከባለምባራስ ሐሺታ ያገኘሁትን የፍቃድ ወረቀት ይኸው በቦርሳዬ ይገኛለሁ» አልኩት።

ፖሊሱም ወረቀቱን ባነበበ ጊዜ በጣም ተደነቀ:: ከዚያም ወደሚከታተሉን ሰዎች ዘወር ብሎ ለምን እንደምትከታተሏቸውና እንደምትቃወሟቸው ንገሩኝ አለ:: በዚህ አካባቢ ሌላ ወንጀል እስካልሠሩ ድረስ የመስበክ መብት አላቸው:: ሰዎቹም ለቅቀውን ወደየቤታቸው እንዲሄዱ አዘዛቸው። እኛም መንገዳችንን እንድንቀጥል ከነገረን በኋላ ማንም ሰው የሚያጠቃን እንደማይኖርም አረጋገጠልን::

ጴጥሮስና እኔ ችግራችን ከተቃለለልን በኋላ ወደ ጣኒባል ተመለስን:: እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነልን ተንበርክከን አመስገንነው:: በዚያን ቀን ነፍሳችንን የታደጋት እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ተገነዘብን::

በእነዚያ ወራት አምቦሌ ከሚባል ወንጌላዊ ጋር በአካባቢው ለመዘዋወርና ለመስበክ ተስማማን። ወደ ደሜ ሄደን የምንሰብክበትን ስልት ተወያየን::

በተጨማሪም እግዚአብሔር ወንጌልን ለማስፋፋት የአካባቢውን ሰዎች እየጠራ መሆኑን ሳስተውል በጣም ተደሰትኩኝ:: አባይነህ ደግሞ ውብሐመር በሚባል ቦታ ሄዶ እንዲሰብክ ሁኔታዎችን አመቻቸሁለት:: ካሣ ዊጋ ደግሞ በዚማተር ቆይቶ እንዲሰብክ ካበረታታሁት በኋላ፣ ለተወሰኑ ወራቶች ወደ ጎፋ ተመለስኩኝ።

በዚያን ወቅት አማሮ በሚባል ቦታ ሰዎች ወንጌላዊ እንደሚፈልጉ ከሰማሁ በኋላ ወደዚያ ሄጄ ለመስበክ ፈቃደኛ ሆንኩ:: የሽማግሌዎች መማክርት ቦርድ እኔ ለተወሰነ ጊዜ ወደ አሪ እንድመለስና ወደ አማሮ ግን ሌሎች ወንጌላውያን ቢሄዱ እንደሚሻል ወሰኑ።

ስለዚህ እኔም ወደ ቤቴ ተመለስኩኝ:: ወደዚያ እንደተመለስኩ ሸክላ ሠሪዎችን በተመለከተ ችግር የተፈጠረ መሆኑን አስተዋልኩ።

## ሌላው የቀብር ብጥብጥ

አሁንም የአንድ ሸክላ ሠሪ (በተለምዶ የፉጋ) ልጅ ሞቶ ክርስቲያኖች ያልሆኑትን በመተው ክርስቲያኖችን ጠርተው ሁሉም ተሰባስበው የሞተውን ልጅ ቀበሩት። በአገራችን ደቦ የሚባል ባህል አለን:: ይህም ማለት የተወሰኑት የአንድ አካባቢ ሰዎች በአንድነት ሆነው ጫካ በመመንጠርና ቁጥቋጦን በማጋየት በኅብረት ይተጋገዛሉ። በዚያን አጋጣሚ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ጎራ ለይተው ስለ ደቦ



በማንሣት ረብሻ ፈጥረው ክርስቲያኖቹን በዱላ ይደበድቧቸው ጀመር:: አማኞቹም ራሳቸውን ለመከላከል ቆንጨራ ይዘዋል:: ይሁን እንጂ ሰላማዊ ሁኔታ ተፈጥሯል።

«አገራችንን አርክሰዋል:: የሸክላ ሠሪውም ልጅ ባልተለመደ ሁኔታ በመሬታችን ተቀብሯል:: ሰብላችን ይወድምብናል:: ከብቶቻችንም ታመው ይሞቱብናል:: ስለዚህ ይህንን የሚበክል ሁኔታ ማስወገድ አለብን» ተባባሉ።

ኅብረተሰቡ በሙሉ እንደገና ታወከ:: ክርስቲያኖች ያልሆኑት ሰዎች የጸሎት ቤታቸውን የሣር ክዳን በእሳት አቀጣጠሉ:: ቤቱም ወዲያው ወድሞ ወደ አመድነት ተለወጠ:: የሸክላ ሠሪዎች በጎችና ፍየሎች እየተወሰዱ (እየተዘረፉ) ታረዱ:: ቤትም እየገቡ የሚሰባበሩትን ዕቃዎች ሁሉ መሰባበር ጀመሩ:: የሸክላ ሠሪውንም ከአካባቢው አባርረው አስወጡ።

«ተመልሰህ ወደዚህ ስፈር ከመጣህ ኃላፊነቱ የራስህ ነው፣ ለሚደርስብህ ለማንኛውም ነገር ማንም አይጠየቅም» ብለው አስፈራሩት::

ወንጌላዊ ካሣም ወደ ጎፋ አምልጦ መጣ። ልክ በዚያን ጊዜ የአካባቢው ቤተ ክርስቲያናት ስብሰባ ነበር:: ምን እንደ ተፈጸመ ለማወቅና በጉዳዩ ለመጸለይ እንዲችሉ ስለ ሁኔታው ወንጌላዊው መጥቶ እንዲያስረዳ ጋበዙት::

ያን ጊዜ ከሩቅ አገር ከደቡብ ሐመር ለመጡት ሰዎች እኔንም አስተዋወቁኝ:: እዚያ ደግሞ ሰዎች መልካምን ዜና (ወንጌልን) ለመስማት እንደሚፈልጉ ሰማሁ:: ኤስ አይ ኤም ደግሞ በሐመር ጣቢያ ለመክፈት በሂደት ላይ ነበርና ለአካባቢው ሕዝብ ብዙ ወንጌላውያን ያስፈልጉ ነበር።

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት አቶ ሰለሞን ቃል ገብቶልኝ እንደነበረ አስታወስኩኝ:: ያን ጊዜ አቶ ሰለሞን በአዲስ አበባው ፓርላማ ተሰብስቦ ነበር:: ለአቶ ሰለሞን ደብዳቤ ጽፈን ወደ አዲስ አበባ ለመላክ የምንችልበትን መንገድ ተወያየን:: በዚህም ጉዳይ ላይ ከሚስተር ብሩስ አዳምስና ከጎፋ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መማክርት ጋር ሆነን ጸለይንበት:: በተጨማሪም ከወላይታ ወንጌላውያን ጋር ማመልከቻውን ለአቶ ሰለሞን አቀናብረን ለመጻፍ ስለምንችልበት ሁኔታ ተወያየን።

በሚጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ምን እንደ ተፈጸመ በዝርዝር ለመጻፍ ከተስማማን በኋላ በደብዳቤውም ላይ እኔ ፈረምኩበት::

በጊዜው የቡልቂ አውራጃ አስተዳዳሪ አቶ አሰፋው ባቤ ይባሉ ነበር:: አቶ ሰለሞን የሚወስደው ማንኛውም እርምጃ በአውራጃ አስተዳደሪው በአቶ አሰፋው በኩል እንደሚፈጸም ስለምናውቅ የማመልከቻችንን ግልባጭ ለአውራጃው አስተዳዳሪ ላክን።

አስተዳዳሪውም ግልባጩ እንደ ደረሳቸው በጣም ተቆጥተው እኔንና ካሣን አሣሠሩን:: ሦስት የታጠቁ ፖሊሶችን ወደ ኤስ አይ ኤም ግቢ ልከው ካስያዙን በኋላ በትልቁ ወህኒ ቤት ውስጥ ጨመሩን።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በቀጠሮ ጠሩኝና፣ «መሐሪ» ሲሉኝ፣ እኔም፣ «አቤት፣ ጌታዬ» አልኩኝ::

«ወደ አዲስ አበባ በተላከው ደብዳቤ ላይ ፈርመሃል?» አሉኝ::

«አዎን፣ ጌታዬ፣ ፈርሜአለሁ» አልኳቸው።

«እኔ በማስተዳድረው አውራጃ ውስጥ ተፈጸመ ብለህ እንዴት ውሸት ታሰራጫለህ?»

«ጌታዬ፣ ውሸት የለውም:: በደብዳቤው ውስጥ የተጻፈው ነገር ሁሉም እውነት ነው:: አጋንነን የጻፍነው ምንም ነገር የለም:: ሁሉ ነገር እውነት ስለመሆኑ አብሮኝ የነበረው ሰው ምስክር ነው» አልኳቸው::

የአውራጃ አስተዳዳሪውም ትልቅ ሐዘን ተሰማቸው፣ በሚቻላቸው ሁሉ በማንኛውም ነገር ሊረዱን እንደሚችሉ አረጋገጡልን።

በአካባቢው የአማራ ተወላጅ የሆኑ አቶ ምክረ የሚባሉ የመሬት ባላባት ለክርስቲያኖቹ አዲስ ጸሎት ቤት የሚሠሩበትን መሬት ቆርሰው ሰጧቸው:: ክርስቲያኖች ያልሆኑት ደግሞ በበኩላቸው መሬቱን ለመቀደስ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። ሽክላ ሠሪዎችም አላስፈላጊ ችግር እንዳይፈጥሩ ተጠይቀዋል:: በእርግጥ ብጥብጡ ለወደፊቱ የሚቀጥል ሊሆን የሚችል ቢሆንም፣ የነበረብን ችግር ተወግዶ ሁሉም ሰላምን ከማግኘቱም በላይ ሥራችንም ማደግ ጀመረ።

በዚህን ጊዜ የአሪ አካባቢ ወንጌላውያን በየጊዜው እያደጉና ብዙ ሥራ እየሠሩ በመሆናቸው እኔ ወደ ጎፋ ለመመለስ ወሰንኩ::

ከዚያ በመሄዴ በብዙ መንገድ ያሳዝነኛል:: በአሪ ሕዝብ መካከል በሁለት ዓመት ቆይታዬ ብዙ ችግሮችን የተጋፈጥን ቢሆንም፣ ብዙ



መንፈሳዊ እድገትም ለማየት ችለናል። በጎፋ ደግሞ በዚያን ጊዜ ብዙ ችግር አልነበረም፣ የሥራ ውጤታችንንም ከበፊቱ ጋር ስናስተያይ የጎላ እድገት አላየንበትም።

## ማስታወሻ

1. ኤስ አይ ኤም ጣቢያ በሚያቋቁሙባቸው ቦታዎች ሁሉ::
2. በአካባቢው የሚያገለግሉ ወንጌላውያን አስተርጓሚ የሚሹት ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራቶች ነው። በሚያስደንቅ የተፈጥሮ ዝንባሌ የአካባቢውን ቋንቋ ፈጥነው ይለምዱት ነበር።

## ወደ ምዕራፍ አሥራ ስድስት መግቢያ

*ክርስቲያን ያልሆኑት ሰዎች ጠንቋዮችን ባቡ (አባት) እያሉ ይጠሯቸዋል:: አቶ መሐሪና የሥራ ጓደኞቻቸው እነዚያን ጠንቋዮች ሳያቋርጡ እየተዋጉ ነበር። እያንዳንዱ ወንጌላዊ አስተማሪ በመሆኑ ፊደልን በማስተማር በአካባቢው ግልጽ የሆነ ተሣትፎ ነበራቸው። አንድ ሰው ፊደልን ተምሮ መጻፍና ማንበብ ሲችል በኅብረተሰቡ መካከል ከፍተኛውን ደረጃ እንደያዘ ይቆጠር ነበር። ያ ሰው ለራሱ ማሰብ ይጀምራል:: ወንጌላውያን ፊደልን ያስተምሩ ስለነበር ከዚህም የተነሣ ከኅብረተሰቡ ጋር ግንኙነት ስለሚያደርጉ ለብዙ ሰዎች ወንጌልን ለማስራጨት ችለዋል። የፊደል ማስተማሪያ ክፍሎች ቀስ በቀስ አድገው የመንደሩ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለመሆን ከመብቃታቸውም በላይ፣ እነዚያ ት/ቤቶች በኅብረተሰቡ ተቀባባይነት አድገው በመጨረሻም የመንግሥት ት/ቤቶች አካል ሆነዋል። በብዙ አካባቢዎችም ወንጌላውያን የመንግሥት ት/ቤቶች አስተዋዋቂዎች ነበሩ።*

*ብዙውን ጊዜ ሰዎች ክርስቶስን የሚቀበሉት አንድ ጊዜ ነው:: ግለሰቡ የተናቀ ባለእጅም ይሁን ወይንም ሀብታም የመሬት ከበርቴም ይሁን ለወንጌላውያን ምንም ልዩነት አያመጣም:: ነገር ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ሰምተው ክርስቶስን ለመቀበል ለተዘጋጁት ሁሉ ተገናኝ ተው ወንጌልን ለመመስከር ወንጌላውያኑ ደስተኞች ናቸው።*

*በክርስቶስ ለማመን እየፈለጉ ዛሬ ነገ እያሉ የሚዘገዩትንም ሰዎች በትዕግሥት ማስተማራቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ታሪካቸው ከተዘረዘረው ሰው ጋር አቶ መሐሪ ለምን ያህል ጊዜ እንደጸለዩና ስንት ጊዜ እንዳነጋገሯቸው አላውቅም።*

*በአያሌ ዘመን የግል አገልግሎታቸው እንዲሁም በብዙ መቶዎች ለሚቆጠሩ አብሮ አገልጋዮች ሁሉ አርኪ ውጤት ነበራቸው:: አቶ መሐሪ ብቻቸውን አልነበሩም:: ጓደኞቻቸው (የአገር ልጆች) በተመሳሳይ መንገድ ይሠሩ ነበር:: ሁሉም አገልጋዮች ከቀን ወደ ቀን፣ ከወር ወደ ወር ከሕዝቡ ጋር ትከሻ ለትከሻ ገጥመው ስለሠሩ ስኬታማ ለመሆንም በቅተዋል::*

*መለወጥ ለሚገባው ኅብረተሰብ ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ኃይል አስደናቂ ምስክር ሆናለች። ፍጹም የሆነ ነገር አልነበረም፣ ሊሆንም አይችልም:: ነገር ግን የአዳኙን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ያሳዩ ነበር::*



# ወደ ጎፋ መመለስ

## ምዕራፍ አሥራ ስድስት

በ1957 ዓ.ም ወደ ጎፋ ተመልሼ ሐመሮ በሚባል አካባቢ ለስድስት ዓመት ሠርቻለሁ:: አጠቃላይ ሥራዬ (አገልግሎቴ) መነሻው ራሻ ለማ በሚባለው ሰው ዙሪያ ያተኮረ ይሆናል።

የራሻ አባት ሀብታም ነበሩ፣ በአካባቢውም ተደማጭነት ያላቸው የመሬት ከበርቴ ነበሩ:: ራሻ ደግሞ ሀብታም ቤተሰብ ስለነበረው ብዙ ሚስቶችና ብዙ አገልጋዮች ነበሩት። ብዙዎች በድህነት በሚጎሳቆሉበት ኅብረተሰብ መካከል በቅንጦት ለመኖር የቻለ ሰው ነው። እጅግ በጣም ተደማጭነት ያለው ከመሆኑ የተነሣ በሰዎች ዘንድ የሚከበርና የሚፈራም ነበር::

እኔ በ1941 ዓ.ም በጎፋ ወደ ባጋ ሄጄ ቤተ ክርስቲያን ባቋቋምኩኝ ጊዜ ይህ ሰው በሐመር ሕዝብ መካከል ይኖር ነበር። በባጋ አካባቢ እሰብክ በነበረ ጊዜ አልፎ አልፎ ስብሰባዎቻችንን ይካፈል ነበር። በዚያን ጊዜ ይህ ሰው እጁን አነሣ:: ከዚያም፣ «በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ:: ሰይጣንን ክጃለሁ:: የቀድሞውን የኃጢአት መንገዴን ትቼ በአዲስ ሕይወት እመላለሳለሁ» አለ:: ለጥቂት ሳምንቶች እውነትም ክርስቲያን ለመምሰል ፈለገ:: ቆይቶ ግን የልቡ ምኞት ምን እንደሆነ በግልጽ ያስታውቅ ጀመር።

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን የወሰነው ውሳኔ «ከአንገት በላይ» ነበር:: ከልቡ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝና ጌታ እንደሆነ አልተቀበልም ነበር:: የእውነትን መንገድ ቢፈልግም፣ ለመቅረብና ለመታዘዝ ግን አልቻለም። የእርሱ ዓይነት ብዙ ሰዎች እንዳሉ ብናውቅም የተለየ ስሜታቸውና ቀጥተኛ ውሳኔ ለመወሰን አለመቻላቸው ብዙም አያስጨንቀንም። የሰዎችን ልብ የሚለውጠው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናውቃለን:: እጅ ማንሣትን ተከትሎ የተለወጠ ባሕርይ መታየት አለበት።

## የፊደል ትምህርትና ጠንቋዮች

የዚህ ኅብረተሰብ መኖሪያ አካባቢ ጀዊላ ሐመሮ ይባላል:: በዚያም አካባቢ የፈለገ ሁሉ እንዲማር የፊደል ት/ቤት ከፍተን ስለነበረ ብዙ የአካባቢው ልጆች እየመጡ ይማሩ ነበር:: ያን ጊዜ ሚስተር ቢል

ዋስተን የሚባሉ የውጭ አገር ሚስዮናዊ በቡልቂ ይኖሩ ነበር:: እርሳቸውም ለት/ቤታችን መጽሐፎችንና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን በማቅረብ ይረዱን ነበር። ቡልቂ ከዚያ ከት/ቤታችን በእግር የስድስት ሰዓት መንገድ ያስኬዳል:: ለትምህርት ቤቱ የሚያስፈልጉንን አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ከዚያ ከቡልቂ እናመጣ ነበር:: በዚሁ ትምህርት ቤታችን 60 ልጆች የሚማሩ ሲሆን፣ ብዙዎቹ በ1972 ዓ.ም የአሥራ ሁለተኛ ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ በቅተዋል።

ያኔ በዚያ አካባቢ አምስት የተለያዩ ጠንቋዮች ነበሩ:: ሕዝቡም እያንዳንዳቸውን ባቡ እያሉ ይጠሯቸው ነበር (አባታችን እንደ ማለት ነው።) ይህም ማለት ከአምስቱም ጠንቋዮች ኃይለኛ የነበረው ባቡ ዳራ የሚባለው ጠንቋይ ነው:: እርሱ ክርስቲያን ሲሆን፣ የገጠሩ ሕዝብ አብዛኛው መለወጥ ጀመረ:: ግን አስቀድሜ ስለ ራሻ ለማ ልንገራችሁ።

ብዙውን ጊዜ ወደ ቤቱ እየሄድኩ በምንበኘው ጊዜ ብዙ እንነጋገር ነበር። ሁልጊዜ የምናገረውን ለመስማት ፈቃደኛ ከመሆኑም በላይ ምክሬንም ጥሩ ነው ብሎ ይቀበላል። እንዲያውም፣ «መሐሪ የጸሎት ቤት የት ነው የምንሠራው? በቅርብ ጊዜ በእውነት ከልቤ ካመንኩኝ በኋላ በእኔ መሬት ላይ የጸሎት ቤት እንሠራለን» ይለኝ ነበር:: ታዲያ ያ ባዶ ንግግር ነበር፤ ሁልጊዜ ስለ ውሳኔው በምጠይቀው ጊዜ ነገ እያለ ይመልሰኛል።

ሌሎች ጓደኞቹ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳስተምራቸው ፈለጉ። ብዙዎቹም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ያውቃሉ:: ስለዚህም እነርሱን ማስተማር ለእኔ መልካም ነበር:: ሌሎች በአካባቢው አምነው በመጠንከር የጸሎት ቤታቸውን ሠርተው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን መርጠዋል። ይህ ሰው ግን ዛሬ ነገ እያለ በማዘናጋት ቆይቷል።

## ድርብ ጋብቻዎች

በዚያን ጊዜ በአካባቢው «ቆይታ» የሚባል ባሕል ነበር። አንዲትን ልጃገረድ ለማግባት የሚፈልግ ወጣት ለልጅቷ ወላጆች የቅድሚያ ክፍያ ሦስት ሽልንግ (ማለትም አንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ይሰጥ ነበር። ይህን ካላገኙ የልጅቷ ወላጆች ልጃቸውን ለሌላ ወንድ ሊሰጡ ወይም ሊያጋቡ አይችሉም ማለት ነው። ልጅቷን ለማግባት በሚዘጋጅበት ጊዜ ለወላጆቿ አንድ መቶ ብር ጥሎሽ ይከፍላል:: ከመጀመሪያ ሚስቱ በኋላ ደርቦ የሚያገባቸው ሁለተኛና ሦስተኛ ሚስቶቹ ጋራ ተብለው ይጠራሉ::



ለእያንዳንዷ ሚስት የራሳቸውን መሬት ይሰጣቸዋል:: በዚያ ማሳ የሚያመርቱትን ምርት ለራሳቸው መጠቀም የሚችሉ ሲሆን፣ ባል ግን አብዛኛውን ድርሻ ይካፈላቸዋል:: በአንዳንድ አካባቢዎች ሁለተኛና ሦስተኛ ሚስቶች እንደ ባርያዎች ይቆጠራሉ።

ራሻ ለማ ደግሞ ሰፊ መሬትና ብዙ ገንዘብ ስለነበረው ብዙ ሚስቶችን ለማግባት ይፈልግ ነበር:: እርሱ በሕይወቱ በዚህ ሁኔታ የሚኖር መሆኑን ሁሉም የአካባቢው ሕዝብ ያውቃል:: ስለሆነም ሕይወቱ ተለውጦ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የነበረው ፍላጎት አጥጋቢ አልነበረም።

ከዚህ ሰው መልካም ነገር በመጠበቄ ሰዎች ይስቁብኝ ነበር። «ዛሬ ተነሥቶ ያምናል ብለህ ትገምታለህ?» እያሉም የቀልዱብኝ ነበር።

የእነርሱ ቀልድ ግን ምንም ተስፋ አላስቆረጠኝም። ነገር ግን ይህ ሰው አንድ ቀን ከሙሉ ልቡ እንደሚያምን ተስፋ በማድረግ እጸልይለት ነበር። እርሱ ካመነም በእርሱ አካባቢ ያሉት ሰዎች ሁሉም ሊያምኑ እንደሚችሉ ተስፋ አደርግ ነበር። በዚህን ጊዜ ጌታ በጣም በደረቅ ቦታ ያስቀመጠኝ መሰለኝ::

አንዳንድ ሰዎች ተነሥተው፣ «እኛን ተወን:: እኛ ለማመን አንፈልግም ስንል አይገባህም? ለምን ወደ ሌላ አካባቢ ሄደህ አትሰብክም? እኛ በፍጹም አናምንም» ይሉኝ ነበር::

እኔ ግን ተስፋ አልቆረጥኩም:: ነገር ግን በአካባቢው እየተዘዋወርኩ መስበኬንና ማስተማሬን ቀጠልኩኝ።

ሌላ ሻንካ ባጋ የሚባል ወንጌላዊ ነበርና የዚያን አካባቢ ሥራ (አገልግሎት) ለእርሱ አስረክቤ ወደ ሌላ አካባቢ ለመዛወር ተስማማሁ:: ከዚያ መዛወሬንም በብዙ መንገዶች ወደድኩኝ:: አካባቢው ለወንጌል የማይታዘዝ ቢሆንም፣ ጥቂት ክርስቲያኖች ተሰባስበው የጸሎት ቤት ሠርተው ስለነበር ሻንካ የእነርሱ እረኛና ወንጌላዊ ሆኖ እንደሚያገለግል ሳይ በጣም ደስ አለኝ:: እኔም ወደ ሌላ ቦታ ተዛውሬ ለማስተማር ተንቀሳቀስኩ።

በአጋጣሚ ሻንካ ተስፋ ቆርጦ ከዚያ ቦታ ከመሄዱ በፊት ለአጭር ጊዜ ብቻ ነበር የቆየው::

«ምን ይሻላል? ምንስ ማድረግ አለብኝ?» ብዬ ራሴን ጠየቅኩኝ:: በወቅቱ የምሠራው ጉዌዌሪ በሚባል ቦታ ቢሆንም፣ ወደ ባጋ አንዳንዴ እየሄድኩ ለመስበክ ወሰንኩ። ቤቴም ከዚያ አይርቅም ነበር።

አንድ ቀን ዳግመኛ ራሻ ለማን ለመጎብኘት ሄድኩኝ:: «አሁንም በክርስቶስ ለማመን አልተዘጋጀህም?» በማለት ደጋግሜ ጠየቅኩት።

«በቅርቡ፣ በቅርቡ» አለና መለሰልኝ።

## ያለማቋረጥ ለመርዳት የተዘጋጀ

በዚያን ጊዜ ባለቤቴ እጇን በድንገት በቢላዋ ቆረጠች:: ቁስሉ አመርቅዞባት ስለነበረ በከፍተኛ ትኩሳት ትሠቃይ ነበር። በጉዌዌሪ ደግሞ በጣም ለመገኘት የምፈልገው ስብሰባ ነበረብኝ:: ይሁን እንጂ ከዚያ ቀርቼ ባለቤቴን ማስታመም ስለሚገባኝ ወደ ስብሰባው ለመሄድ አልቻልኩም ነበርና በልቤ አዝኜ ነበር።

በሚቀጥለው ማግስትም በቤቴ ለመቆየት አልፈለግሁም ነበርና በስሜቴ ደስተኛ አልነበርኩም:: ስለዚህ መምረጥ ነበረብኝ:: ቡና አላፈላሁም ነበርና ኮቴን ለብሼ ወደ ደጅ ወጣሁ:: ወደ ሻንካ ቤት ሄጄ ልጎበኘውም ፈለግሁና ሄድኩኝ:: ባለቤቴ በቤት ባትኖርም ቡና መጠጣት አለብህ ብሎ ገፋፋኝ:: ከዚያም በኋላ ራሻ ለማን ሄጄ ለመጎብኘት ወሰንኩኝ።

የአጎቱ ልጅ ሞቶ በለቅሶ ላይ ስለነበረ ለመጎብኘት መልካም አጋጣሚ ሆነልኝ:: እቤት እንደሚሆን አውቅ ነበር:: በአካባቢያችን ደግሞ ቀብር ለየት ያለ ሥርዓት ነበረው።

ከራሻ ለማ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፣ «ዛሬስ እንዴት ነው በኢየሱስ ክርስቶስ አታምንም?» አልኩት::

«የማቴዎስ አባት» አለኝ::

«አቤት» አልኩት::

በቅርቡ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፣ ዛሬ ቀብር አለብኝ:: ዛሬ ቅዳሜ ነው አይደል? እሺ የዛሬ ሳምንት ቅዳሜ መጥተህ አስታውሰኸኝና እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ካንተ ጋር እሄዳለሁ» አለኝ:: ከአንደበቱ ይህን በመስማቴ ደስ አለኝ፣ ቃሉንም እንደሚጠብቅ ተማመንኩበት:: ወደ ቤት ሄጄ ይህንን የደስ ደስ ለሌሎቹ ለማብሰር ጊዜ አላጠፋሁም:: «በሚቀጥለው ሳምንት ራሻ ለማ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ስለሆነ በእርሱ መሬት የጸሎት ቤት እንሠራለን» አልኳቸው::

ሁሉም ሳቁብኝ::



«አባክህን ተው፣ እንደዚህ እያልክ ስትናገር ስንት ዓመት አለፈ:: የሚነግርህንስ ቃል እንዴት እውነት ነው ብለህ ታምናለህ?» አለችኝ ባለቤቴ።

እኔ ግን ተስፋ አልቆረጥኩም:: በቅንነት ግን ለእርሱ መጸለዩን ቀጠልኩኝ::

በቀጠሮአችን ቀን አልተገኘም:: ይህ ሁኔታው አሁንም አላስደነቀኝም፣ ተስፋም አላስቆረጠኝም:: እግዚአብሔር ልቡን ያነሳሳል የሚል ሙሉ እምነት ነበረኝ።

ከሦስት ሳምንት በኋላ ዳግመኛ ቤቱ የመሄድ አጋጣሚ አገኘሁ። ከቤቱ በደረስኩ ጊዜ በተረዳሁት ሁኔታ በጣም ተደነቅኩኝ:: ለተከታታይ ጉዳዮች በፍርድ ቤት እንደሚውልና የነበረውን ንብረቱን ማጣቱን አላወቅኩም ነበር:: የአባቱ አሽከሮችና ገባሮቹ ሁሉም ጥለውት ሄደዋል:: ቤቱም ባዶ ሆኖ ጭር ብሏል።

ወደ ቤቱ እንድገባ ጋበዘኝና ቡና ይፈላልህ አለኝ:: ነገር ግን በቤቱ ውስጥ የሚያግዘው ማንም አልነበረም:: በገዛ ቤቱ የራሱን ቡና ለመውቀጥ ሙቀጫና አነስተኛ ዘነዘና ተቀበልኩት። ይህ ሁሉ እውነት አልመስል አለኝ፣ ለማመን ያስቸግረኝ ነበር። ቡናውን ተጋግዘን ካፈላን በኋላ በየበርጩማችን ተቀምጠን መጠጣት ጀመርን:: የነገረኝ ታሪክ በጣም የሚያስደንቅ ነበር።

እርሱም ለብዙ ዓመታት ስለ ጌታ ኢየሱስ አዳኝነት ደጋግሜ እንደ መሰከርኩለትና ለማመን እምቢ ማለቱን አወሳ:: «አሁን እኔ ልዩ ነኝ:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከልቤ አምኜአለሁ:: እርሱን ለመከተል ማድረግ የሚገባኝን ሁሉ ለማድረግ ፍቃደኛ ነኝ:: አለኝ።

ሁለታችንም ረዥም ጊዜ ወስደን ብዙ ተወያየንና እኔም አሁን ምን ችግር እንዳለበት ጠየቅኩት::

ገንዘቡ ሁሉ እንደ ተወሰደበትና ዘመዶቹ ሁሉም ስለከዱት በድህነት ውስጥ ያለ መሆኑን ነገረኝ:: ታሪኩን ለማመን አስቸገረኝ:: እኔም ሰዎችን አሰባስቤ ልብስ የሚገዛበትን ገንዘብ ልናዋጣለት እንደምሞክር ነገርኩት:: ነገር ግን ወዲያው በትንሽ ነገር ሰይጣን አታለለው:: በሁኔታው በጣም ተስፋ ብንቆርጥም ከሙሉ ልቡ የተለወጠ በመሆኑ እንደሚመለስ ፍቃደኛነቱን አሳየን።

## የቀድሞ ሀብታም የዛሬ ድሃ ተረጂ

ወደ አካባቢው የክርስቲያኖች ስብሰባ እንዲመጣ ጋበዝኩት:: ሰዎች ሁሉ ሲያዩት በጣም ተደሰቱ:: በመካከላቸው ስለሠራው ሥራ

እግዚአብሔርን አመሰገኑት:: ክርስቲያኖች አዲስ ልብስ ሊ ገዛበት የሚችለውን ያህል ገንዘብ አዋጥተው ሰጡት:: ምእመናኑም የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንደሆነ አድርገው ለመቀበልም ተዘጋጅተዋል። ይህ ሰው ለረዥም ጊዜያቶች እንደሚያምን እየተናገረ መቆየቱ የትዝብት አሻራ ጥሎ እንዲያልፍ ቢያደርገውም ምእመናኑ ግን የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንደሆነ አድርገው በተዘጋጀ ልብ ተቀብለውታል።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ከተለያዩ አካባቢዎች ከተወጣጡ አሥራ ሰባት የቀረጥ ሰብሳቢዎች ጋር ስብሰባ ነበረን:: እርሱም ወደዚህ ስብሰባ መጥቶ ስለ ነበረ በጎፋ የነበሩት ክርስቲያኖች በደስታ ተቀበሉት:: በዚህ ሰው ልብ ውስጥ ታላቅ ሥራ የሠራውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

ራሻ ለማ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በኋላ እኔ ወደ መደበኛ ሥራዬ ወደ ሐማር ሄድኩኝ:: እዚያ እየሰበክሁ በነበርኩ ጊዜ አንድ አማኝ ያልሆነ ሰው በጣም ታምሞ መጣ::

«ምንድን ነው የምታደርግለት?» ብዬ አብሮት ያለውን ዘመዱን ጠየቅኩኝ::

ሰውየው በታፋው ላይ ከፍተኛ እብጠት ይታይበታል፣ በጣም እየተሠቃየ በመሆኑ የሕክምና ዕርዳታ እንደሚያስፈልገው ግልጽ ነበር::

ዘመዶቹና ወዳጆቹ ያደረጉለት እርዳታ ቢኖር ወደ ወጌሻ ማድረስ ብቻ ነበር:: ወጌሻ የተወሰነ በሽታ ሊያድን ቢችልም፣ የዚህ ሰው እብጠት በጣም ስላመረቀዘ ከወጌሻው አቅም በላይ ሆኗል። ዘመዶቹ ወደ ቡልቂ ክሊኒክ እንዲያደርሱት ካነሳሳኋአቸው በኋላ እኔም አብሬአቸው ሄድኩኝ:: እግዚአብሔር ደግ ነውና ሰውየው እዚያ ከበሽታው ተፈወሰ:: ይህ ሰው ከአንድ ዘመዱ ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ፣ ሌላም አንድ የአካባቢ ሹም አመነ::

ወዲያውም በቡልቂ የኤስ ኣይ ኤም ማቢያ በተከፈተው የመጽሐፍ ቅዱስ ትቤት ገባ:: በመጨረሻም በሐመሮ የጸሎት ቤትና በወረዳው የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተከፈተ:: እግዚአብሔር በዚያ ቦታ ስለሠራው ታላቅ ነገር ከመደሰቴም በላይ፣ እግዚአብሔርን በጣም አመሰገንኩኝ።



## *ወደ ምዕራፍ አሥራ ሰባት መግቢያ*

*አቶ መሐሪ የደረጃ ዕድገት ወይም ከፍ ከፍ መባል አይፈልጉም:: እርሳቸው እንደ ሌሎቹ ሰዎች ከመጀመሪያው ጀምረው በሕይወታቸው ዘመን ለማገልገል የወሰኑ ናቸው:: መልካም ዜና (ወንጌል) ለዓለም በጣም አስፈላጊ መልእክት ከሆነ ተገቢውንና ሦስት እጥፍ የሆነውን በጽኑ እምነት በየትኛውም ቦታ ቢሆን በሕይወቴ ሙሉ አስተላልፋለሁ ብለው ተነሥተዋል። የወንጌላዊ ሥራ (አገልግሎት) ከዓመት ወደ ዓመት ከዘመናት ወደ ዘመናት የማይለወጥና ተመሳሳይ ነው። በእያንዳንዱ ኅብረተሰብ ሁለት የተለየ ትርጉም ያላቸውና ሁልጊዜ ወንጌላውያን የሚጋፈጧቸው ቡድኖች (ሰዎች) ባሕላዊ ሃይማኖት የሚያወድሱና ከማኅበራዊ አኗኗር የተገለሉ ናቸው:: ወንጌላውያን ተዘዋውረው በሚሰብኩባቸው ቦታዎች ሁሉ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን የሚያባክኑት ከባህላዊ ሃይማኖተኞችና ልዩነትን ለመፍጠር ከሚተጉ ቡድኖች ጋር በመጋፈጥ ነው::*

*በእነዚህ ሁለት አካባቢዎች ወንጌል በቀጥታ ከባህል እምነት ጋር ሲጋጭ ይታያል:: በምንም ዓይነት በድርድር የሚፈታ አይሆንም::*

*ወንጌላውያንን ሳያቋርጡ እንዲሠሩ የሚያበረታታቸው ነገር ቢኖር በጎፋ ውስጥ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ነው። በ1961 ዓ.ም ወንጌላውያን በጎፋ የነበራቸውን የ25 ዓመት የአገልግሎት ጉዞ ወደ ኋላ መመልከት ችለው ነበር። ከኅብረተሰቡ ወደ እምነት ሕይወት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ይመለሱ ነበር። የወንጌላውያን የአገልግሎት ዘዴያቸው ወደፊት ሳያቋርጥ ይቀጥል ነበር:: በአንድ ቦታ ለረዥም ጊዜ ከቆዩ በኋላ ወንጌላዊ ከመሆን ይልቅ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይሆኑ ነበር።*

*በጎፋና በሰሜናዊ ምዕራብ አሪ ሃያ ዓመት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ አቶ መሐሪ ከዚያ ለመዛወር ማሰብ ጀመሩ:: በደቡባዊ አሪ ውስጥ ኤስ ኣይ ኤም አዲስ ሥራ ለመጀመር በሂደት ላይ ነበር:: አቶ መሐሪ በበና ሕዝብ መካከል ሄደው እንዲሠሩ ተጠየቁ:: ነገር ግን ወደዚያ ከመሄዳቸው በፊት ወደ ምዕራባዊ ኢትዮጵያ ሄዱ። በከፋ ክፍለ ሀገር አቶ መሐሪ ዋና መሠረት ሆነው ከብዙ ወንጌላውያን መካከል ሕይወታቸውን በታማኝነት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ያዋሉ ናቸው:: ከጥቂት ዓመታት በኋላ ለአካባቢው ወንጌላውያን ሥራውን ያስረክባሉ።*

# በሁሉም መንገድ መቃገል

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ከሐመር ከፋ ወደሚባል ቦታ ለስብከት ተዛወርኩኝ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራው በጣም ከባድ ነበር። የአካባቢው ኅብረተሰብ በሙሉ ኃይለኛ በሆኑ ጠንቋዮች ቁጥጥር ሥር ነበር:: በመጨረሻ ግን አንድ ጸሎት ቤትና እስከ አራተኛ ክፍል ማስተማሪያ የቀለም ት/ቤት ተከፍቷል።

በዚህ ቦታ በተለይም ኃይለኛ የሆነ ጠንቋይ የነበረ ሲሆን፣ ይህ ጠንቋይ ሰዎችን ለመጉዳት ልዩ ኃይል አለኝ ብሎ የሚያወራ ነበር። በአካባቢውም ዓይነ ስውራን የሆኑ ወይም አንድ ዓይን ያላቸውና እግሮቻቸው ሽባ የሆኑ የተወሰኑ ሰዎች ነበሩ ። ይህ ጠንቋይ እነዚህን ሰዎች የቀጣኋቸው እኔ ነኝ እያለ ስለሚያወራና ስለሚያስወራ ሰዎች እጅግ በጣም ደፈሩታል:: ሌሎች አራት ጠንቋዮች ደግሞ የእርሱ ተወካዮች እንደሆኑ ይናገሩ ነበር። በዚያ አካባቢ ብዙ ጫካ የነበረ ሲሆን፣ በብዙ ቦታዎች በጫካው ውስጥ የበቀሉትን ትላልቅ ዛፎች ጠንቋዮች የእኛ ናቸው ስለሚሉ ደፍሮ ዛፎቹን የሚቆርጥ ሰው አልነበረም:: ከዚህም የተነሣ ጠንቋዮቹ ሀብት ያካብታሉ፣ ይፈራሉም። ከብዙ ርቀት ወደ እነርሱ ከሚመጡት ሰዎች ገንዘብ፣ የጠር መሣሪያና ከብቶችን በገፍ ይሰበስቡም ነበር።

በዚያ አካባቢ የሸክላ ሠሪዎች (የፋጋዎች) ኅብረተሰብ ነበሩ። አንዳንዶቹም አነስተኛ የእርሻ መሬት ተፈቅዶላቸው የሚያርሱ ናቸው። ምናልባት የአናጢነት፣ የቀጥቃጭነት የሸክላ ሠሪነት ሙያ ብዙም ስላላዋጣቸው ወይም ለኑሮአቸው በቂ ባለመሆኑ የአካባቢው ሕዝብ አብዛኛውን ጊዜ ለም ያልሆነውን መሬት እንዲያርሱ ይሰጣቸውና ከዚያ አካባቢ እንዳይሄዱባቸው ያደርጉ ነበር።

አንድ ቀን በመንገድ ሳልፍ ከሸክላ ሠሪዎች ወገን የሆነ ሰው ከመንገዱ ዳር ሲያርስ አገኘሁት:: ሰላምታ ከሰጠሁት በኋላ በብዙ ቦታዎች ባሕል እንደነበረው ማረሻውን በቀኝ እጄ ተቀበልኩትና በግራ እጄ ጅራፍ በመያዝ በሬዎቹን እየነዳሁ ማረስ ጀመርኩ::

ወዲያው ወሬው እንደ በጋ እሳት ተዛመተ። የአካባቢው ሕዝብ ከአካባቢው ሊያወጣኝ ሞከረ።



በዚያን ጊዜ ባለቤቴ ሕፃን ልጅ ነበራት:: ላማችንም ወተት ስላልነበራት ለሕፃኑ ወተት ከጎረቤት እንገዛ ነበር:: ቃዲያ ወተት የሚሰጡን ሰዎች አንሸጥላችሁም አሉን:: ለሕጻኑ ወተት በጣም የሚያስፈልገው ቢሆንም በፍጹም እንደማይሸጡልን ነገሩን። በቡልቂ ወደሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮን ጣቢያ ሄጄ ከሚስዮናውያኑ የዱቄት ወተት መግዛት ነበረብኝ።

ወደ አካባቢው ገበያ ስንሄድና የፈለግነውን ዕቃ ለመግዛት ስንጠይቅ፣ ሰዎች አንሸጥላችሁም አይሉንም:: ነገር ግን ዋጋውን ስንጠይቃቸው እጥፍ አድርገው ይነግሩን ነበር:: ይህ ማለት በባሕላዊ መንገድ ለእኛ የፈለግነውን ዕቃ ላለመሸጥ የነበራቸው ዘዴ ነው። ምግብ ለመግዛት ስፈልግ ሰዎች ወደማያውቁኝ ወደ ሩቅ ገበያ እሄድ ነበር።

እንደ እውነቱ ከሆነ እኛ ወጥተን አልሄድንም እንጂ፣ እኛን ከአካባቢው አርቀው ሊያወጡን በብዙ ሞክረዋል:: ክርስቶስ ለሁሉም እንደ ሞተ፣ እኔም ከሌሎቹ ሰዎች (ፋጋ ከተባሉትም ጭምር) እንፈተናለን የሚል የግል መመሪያ ነበረኝ።

በዚሁ ሁኔታ ቀስ በቀስ አንድ ሰው ሲያምን ሌላም እየተጨመረ ይሄድ ነበር:: በተለይም የራሻ ለማ ወደ እምነት መምጣት በብዙ ሰዎች ላይ ጥሩ ግንዛቤ አስገኘ:: እኔም ለተወሰኑ ዓመታት በዚሁ አካባቢ እንደቆየሁ የጸሎት ቤት ተሠርቶ ምእመናኑም ሥራውን የሚያካሂዱ ሽማግሌዎችን ለመምረጥ ቻሉ። የአካባቢው ሕዝብ በክርስቲያኖች በኩል ብዙ ለመማር ከመቻሉም በላይ የሕክምና እርዳታም አግኝቷል።

## ክርስቲያኖች በብዙ አካባቢዎች

በዚያ አካባቢ ስኖር መሎ በሚባለው ሌላኛው ቦታ ሄጄ ወንጌልን መስበክ ጀመርኩኝ:: በዚያ አካባቢ አጋንንት የያዘው አንድ ሰው ነበር:: ሄጄ እንድጸልይለት ቤተሰቦቹ ጠየቁኝ:: ሌሊቱን ሙሉ ጸለይኩለት፤ በመጨረሻም ሰውየው ድኖ በማመን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ለመሆን በቃ። እንደገና ሌላ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ነበር። ያ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን የማይፈልግ ግትር ቢሆንም፣ ልጁ ግን አምኖ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ከማሎ ተነሥቼ አሌባ ወደሚባለው ሌላ ቦታ ሄድኩኝ:: በዚያ አካባቢ የነበሩ ሰዎች ለረዥም ጊዜ ለወንጌሉ የማይታዘዙ ነበሩ:: ቀስ በቀስ ግን አንድ ሰው ፍላጎቱ ቢኖረውም ሕይወቱን ለጌታ ለማስገዛት

ያልተዘጋጀ መሆኑን አስተዋልኩኝ:: በመጨረሻ ግን አመነና በእርሱ ምክንያት በዚያ አካባቢ ያሉት ሰዎችም በብዛት ክርስቲያኖች ሆኑ:: ከተወሰኑ ዓመታት በኋላም በርካታ ማኅበራት በዚያ ተመሥርተዋል። በዚያ ሕዝብ መካከል መሪዎች የሚሆኑ ሰዎች ተነሥተው ክርስቶስን እንዲቀበሉና ሥራውን እንዲረከቡ ማድረግ የሚገባኝን አድርጌአለሁ::

ከዚያም ሚስተር ዲክ ማክሊላን መልእክት ላከብኝና ባለቤቴንና ልጆቼን ትቼ ወደ ቡልቂ ተጓዝኩኝ:: ያስጠራኝ ምክንያትም ወደ ሌላ የኢትዮጵያ ግዛት ሄጄ እንድሰብክ ስለፈለገ ትኩረት እንድሰጥበት ሊያሳስበኝ ነበር።

«በዚያ በአንድ ቦታ ምን ያህል ጊዜ ትቆያለህ?» ብሎ ጠየቀኝ:: «በአካባቢያቸው እየሠሩ ያሉ ብዙ የጎፋ ወንጌላውያን አሉ:: ስለዚህ ምናልባት አንተ ወደ ሌላ ቦታ ብትሄድ መልካም ይሆናል» አለኝና ሚስተር ማክሊላን ወደ ሐመር ሄጄ ወንጌልን ለባና ሕዝብና ለፀማይ ሕዝብ እንድሰብክ ጠየቀኝ።

«ወደዚያ እንድሄድ ጌታ የፈቀደልኝ ቦታ ከሆነ፣ ከሙሉ ልቤ ሄጄ ለማገልገል ፍቃደኛ ነኝ» ብዬ መለስኩለት።

## በዲመካ አዲስ ጅማሬ

በዚያን ጊዜ ሚስተር ቻርሊ ቦንክና ቤተሰባቸው የሆኑት ሚስዮናውያን ዲመካ ሄደው ቤቶችን ለመሥራት በዝግጅት ላይ ስለነበሩ ሚስተር ማክሊላን ከእነርሱ ጋር ወደ ሐመር (ዲመካ) አብሬ እንድሄድ ሃሳብ አቀረበልኝ።

አስቀድሜ በወንጌላዊነት የተላክሁት በወላይታ ሽማግሌዎች መማክርት ስለሆነ ወደየትኛውም ስፍራ ከመንቀሳቀሴ በፊት የመማክርቱን ድጋፍ ማግኘት ይጠበቅብኛል:: በተጨማሪም በቡልቂ ሚስተር ቦንክን መገናኘት የማይቻል መሆኑን አውቅ ስለነበር ወደ ወላይታ ሶዶ ተጓዝኩኝ።

የሽማግሌዎቹን መማክርት ወደ ሐመር እንድሄድ ፈቃድ ስጠይቃቸው ፈቃደኛ ሆኑልኝ:: ሚስተር ቦንክ በአዲስ አበባ ነበሩና በሬዲዮ አነጋገርኳቸው:: እርሳቸውም የሚያስፈልጓቸውን ዕቃዎች እያሰባሰቡ በመሆናቸው መኪናቸው መቼ እንደሚንቀሳቀስ ገና እንደማያወቁ ነገሩኝ:: ስለዚህም በጎፋ ጥቂት ቆይቼ ወደ ሐመር ብጓዝ የተሻለ ነው አሉኝ።



እኔም ወደ ቡልቂ ተመለስኩኝ::

ሚስተር ማክሊላንም፣ «ሚስተርና ሚስስ አሌክስ ፌሎውስ በከፋ አብረህ ሄደህ የወንጌልን ሥራ እንድትሠራ ይፈልጋሉ፣ ወደዚያስ ብትሄድ ምን ይመስልሃል?» አለኝ::

«ያም የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ በእኔ በኩል ፈቃደኛ ነኝ» አልኩት::

በጎፋ ያሳለፍኩትን ጊዜ ሳሰላ ሃያ ሁለት ዓመት ሆኖኛል:: ይህም ማለት ከ1939 - 1961 ዓ.ም በዚያ በጎፋ አካባቢ ሠርቻለሁ ማለት ነው። እኔ ጎፋን ለቅቄ ስሄድ አንድ መቶ ስልሳ ቤተ ክርስቲያኖች ተመሥርተዋል:: አስቀድሜ እንደተናገርኩት፣ እኔ ከጥቂት ሰዎች ጋር ብቻ እገናኝና ትንሽ ቤተ ክርስቲያን እመሠርታለሁ:: ከወላይታና ከጎፋ የሆኑት ብዙ ወንጌላውያን በአካባቢው በስፋት ይሠራሉ። በሃያ ሁለት ዓመት ቆይታዬ በዚያ አካባቢ እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ ስመለከት በጣም ተደሰትኩኝ።

በ1941 ዓ.ም በርካታ ቁጥር ያላቸው ወንጌላውያን ከወላይታ ወደ ጎፋ ሄደው ሠርተዋል:: ሻንካ እና ላሌሶ በአሪ ጉይቤ ደፋርሻ ከሚባለውና በጣሊያን ወረራ ጊዜ አምኖ ከተጠመቀው ሰው ጋር ተደሳድለው ተቀምጠዋል። ጃራና እታንጌ በመጀመሪያ በዛንጋ ኖሩ:: ኢርጋዳና ዮሐንስ በቡኣ ነበሩ:: ሁላችንም አንድ ቀን አካባቢውን መልቀቃችን እንደማይቀር በማወቅ፣ ተባብረንና ተግባብተን በጋራ እንሠራ ነበር:: በ1943 ዓ.ም ሌላ የወንጌላውያን ቡድን ከወላይታ ወደ ጎፋ ሄደ:: አማንታ በአካባቢው በደረሰ ጊዜ እርሱና ወንድሜ ዳንኤል ካንቾ በሚባል ቦታ ያገለግሉ ነበር:: ቆየት ብሎ ደግሞ እነ ሊባባ፣ ዳና፣ ማዳልቾና ዳንጎ የሚባሉ ሰዎችን የያዘ ቡድን መጣ:: ከእነርሱ በኋላ ደግሞ ላማ፣ ባሳና ሾንቄ መጡ:: እነዚህን ስሞች የምጠቅሰው ከወላይታ ተልኬ በጎፋ የሠራሁት እኔ ብቻ አለመሆኔን እንድታውቁ ነው::

## *ወደ ምዕራፍ አሥራ ስምንት መግቢያ*

*ከ1938 ዓ.ም እስከ 1948 ዓ.ም ኤስ ኣይ ኤም ወንጌልን ለማስራጨት በከፋ ዋና ከተማ በነበረው በቦንጋ መሠረት ይጥል ነበር:: አስቀድመው የካቶሊክ ሚስዮናውያን ለአሥር ዓመት በአካባቢው ሠርተው ነበር:: ከ1948 እስከ 1958 ዓ.ም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በወቅቱ የበላይነት የሚሰማቸው የአማራ የገዢ መደብ አባሎች ኤስ ኣይ ኤምን ጠንክረው በመቃወም የውጪ አገር ሚስዮናውያንን ከቤታቸው እንዳይወጡና የቁም እሥር ያህል ያስጨንቋቸው ነበር:: ለአሥር ዓመታት ያህል የአገር ተወላጅ የሆኑ ወንጌላውያን እንኳን ለመሥራት ያልተቻላቸው ወቅት ነበር:: በከፋ ለመሥራት የሚሞክሩትን ወንጌላውያን እንደ ሚስዮናውያን ተቀጣሪ ሠራተኞች አድርገው በመቁጠር ከሚስዮኑ ግቢ እንዳይወጡ ያግዷቸው ነበር::*

*ከ1967 ዓ.ም አብዮታዊ ለውጥ ቀደም ብሎ አቶ መሐሪና በርካታ ቁጥር ያላቸው ወንጌላውያን በማይበገርና በማይረታ ፍላጎት ወንጌልን ለማስራጨት ከአሌክስ ፌሉስ ጋር በመሆን በከፋ መስበክ ጀመሩ:: በጐፋና በአሪ እንደሆነው የባሕላዊ ሃይማኖት ተከታዮች ልዩነት በመፍጠር ይፈታተኑአቸው ነበር:: በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ይደርስባቸው የነበረው ዛቻ እስከ 1968-1969 ዓ.ም ሳይቋረጥ ቀጥሎ ነበር:: የወንጌልን እውነት ለመግለጽ የፍርድ ቤት ክፍሎችንና የእሥር ቤት መጋዘኖችን ተጠቅመዋል::*

*ወንጌላውያኑ ከጐፋ የበለጠ በከፋ በብዙ መንገዶች ችግር ተጋፍጠዋል:: የከፋ ሰዎች ቋንቋቸውና ባህላቸው በአጠቃላይ የተለየ በመሆኑ ትንሽ ከተመለከቱና ካዳመጡ በኋላ ባህላዊ ገጽታቸውን ያንጸባርቃሉ:: ወንጌላውያኑ ከቤታቸው በጣም የራቁ ናቸው:: የወር ደመወዛቸውን እንኳን ለመቀበል ከርቀቱ የተነሣ በጣም ይቸገሩ ነበር::አዲስ መንፈሳዊ ኅብረተሰብ ለመፍጠር ከባዶ ቦታ ይነሣሉ:: ይህም ማለት በአዲስ አካባቢ ወንጌል ባልተሰበከበት ሀ ብለው ይጀምራሉ ማለት ነው::*

*ታዲያ በሁሉም ውጤታማዎች ነበሩ:: ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ተመሥርተዋል:: በምዕራብ ኢትዮጵያ የአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ ከዕለት ወደ ዕለት ያድግ ነበር::*



# ምዕራባዊ ኢትዮጵያ

## ምዕራፍ አሥራ ስምንት

በጋሞ ጐፋ ክፍለ ሀገር በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወርኩ ለሃያ ሁለት ዓመት ወንጌልን ከሰበክሁ በኋላ፣ በ1964 ዓ.ም የከፋ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ ወደነበረው ወደ ቦንጋ ሄድኩኝ:: እንደደረስኩም በቦንጋ በኤስ ኣይ ኤም ጣቢያ ለጥቂት ጊዜ ቆይታ ካደረግኩኝ በኋላ፣ ጥቂት ሰዓቶች ወደሚያስኬደው ይርጋለም ወደሚባል መንደር ሄድኩኝ:: እዚያም ለሁለት ወር ከቆየሁኝ በኋላ ቤታ ወደሚባለው ቦታ ሄድኩኝ::

ወደዚህ አካባቢ እኔ ከመድረሴ ቀደም ብሎ አቶ ኣካሶ የሚባል ሌላ ወንጌላዊ ይሰብክ ነበር:: ከአካባቢው ሀብታም ሰዎች መካከል አንዱ የሆነውና እንደ ብዙዎቹ የመሬት ከበርቴዎች የሆነው ሰው ሁለት ያደጉ ልጆች ነበሩት:: እነርሱ ክርስቲያኖች ስለሆኑ በአካባቢው እየተዘዋወርኩ በምሰብክበት · ጊዜ የማርፈው በእነርሱ ዘንድ ነበር:: አንደኛው ዘውዱ የሚባለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተለወጠ በመሆኑ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ የክርስቲያን ሕይወት ይኖር ነበር::

በጣም ሀብታም የሆነው አባቱ የሦስት ቀን መንገድ በሚያስኬድ ርቀት ባለችው ከተማ ይኖር የነበረ ሲሆን፣ ልጁ ዘውዱ ክርስቲያን ሆኗል የሚል ወሬ ደረሰው:: ወዲያውም ለልጁ /ለዘውዱ/፣ «ልጄ፣ ልጄ፣ ይህን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሉትን እንዴት አድርገህ በሕይወትህ ትቀበለዋለህ?« የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል» የሚለውን ተረት አታውቅም? እንዴት ለዚህ አዲስ ትምህርት ጆሮህን ትሰጣለህ?» ብሎ ጻፈለት::

የዘውዱ አባት መጻፍና ማንበብ ስለማይችል ደብዳቤውን ያጻፈው በአንድ ቄስ ነበር::

ዘውዱም መልሶ፣ «ወንድሜ አስፋውም አሁን አምኗል:: እናቴም በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለች:: ሁላችንም አስቀድመን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም አናውቅም ነበር:: አንተም በእርሱ ለምን አታምንም?» ብሎ መልሶ ጻፈለት::

ይህ ደብዳቤ እንደደረሰው አባትየው በጣመ ተቆጣና ተበሳጨ:: ለዚህ ጉዳይ ብቻ ሲል ሦስት ቀን ተጉዞ ወደ ቦንጋ መጣ:: በጣም እንደተቆጣም እኔን ለመገናኘት መጣ:: ሁልጊዜ ተገናኝተን ስንነጋገር

ወደ እኔ አፍጥጦ ይመለከተኝ ነበር፡፡ እኔም በልቤ እግዚአብሔር በመካከላችን ሰላማዊ የሆነ ግንዛቤ እንዲያመጣ እጸልይ ነበር፡፡

ነገር ግን ከእኔ ተለይቶ ሄደና ክስ መሠረተብኝ፡፡ ከዚያም ከመንግሥት ባለሥልጣኖች አንዱ ወስዶ አሠረኝ፡፡ እኔና ዘውዴ እንዲሁም አዶቶ የሚባል ሌላ ወንድም አብረን ታሠርን፡፡ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ካደረሱን በኋላ፣ ለአንድ ሌሊት ጠማችንን አሳደሩን፡፡ በዚያ ፖሊስ ጣቢያ ተይዘው ለሚቆዩት ከየዘመዶቻቸው ምግብ ይቀርብላቸው ነበር፡፡

## ለምርመራ መዘጋጀት

በሁለተኛው ቀን ወደ ቦንጋ ወሰዱን፡፡ ወደዚያ የተጓዝነው በሌሊት ነበርና ከወሰደን ፖሊስ ጋር በመንገድ ላይ የረዥም ጊዜ ውይይት ነበረን፡፡

«ከየት ነው የመጣኸው?» አለኝና ለማወቅ ፈለገ፡፡

እኔ የተወለድኩበት አካባቢ ቁጫ መሆኑንና ለወላይታ የሚቀርብ መሆኑን ነገርኩት፡፡

«ያንተ አካባቢ ወላይታ ከሆነ ታዲያ ወደ ከፋ ክፍለ ሀገር ለምን መጣህ?» አለኝ፡፡

እኔም ወንጌላዊ መሆኔንና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ መምጣቴን ነገርኩት፡፡

«እዚህ ወንጌላዊ ሆነህ እንድትሠራ ሕጋዊ ፈቃድ አለህ?» አለኝ፡፡

«አዎን፣ አለኝ» ብዬ አረጋገጥኩለት፡፡

«እዚህ እንድትሰብክ ፈቃድ የሰጠህ ማን ነው?» አለኝ፡፡

«በማርቆስ 16:15 ላይ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ብሎአል፡፡ ይህንን ትእዛዝ የኢትዮጵያ መንግሥት አልሰረዘውም፡፡ ስለዚህ በማንኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ተዘዋውሬ ለመስበክ ሙሉ ፈቃድ አለኝ» አልኩኝ፡፡

«ይህ ምናልባት ላንተ ጥሩ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በቦንጋ የሚገኙት ባለሥልጣኖች መልስህን አይቀበሉም፡፡ ሌላ የተሻለ መልስ ብታዘጋጅ ይሻላል፤ አለበለዚያ ግን ወደ ወህኒ ይወረውሩሃል» አለኝ፡፡



«ወደ ወህኒ ቢወረውሩኝ ለእኔ መልካም ነው ለምጠየቀው ጥያቄ የማኖረኝ መልስ ይኸው ነው፣ ሌላ መልስ ማዘጋጀት አልችልም» አልኩት፡፡

«ለመሆኑ ትጸማለህ?» አለኝ፡፡

«በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመኔ በፊት እጾም ነበር፡፡ አሁን ግን መጾም አያስፈልገኝም፣ ምክንያቱም ለኃጢአቴ ጌታ ይቅርታ አድርጐልኛል፣ ወደፊትም ሳያቋርጥ ይምረኛል» አልኩት፡፡

«ማርያምን ታመልካለህ?» አለኝ፡፡ እኔም፣ «ማርያምን አከብራታለሁ፣ ዳሩ ግን አላመልካትም» ስለው፣ «ለምን?» አለኝ፡፡

«ለእኔ ማርያም ለኃጢአቴ አልሞተችልኝም፡፡ የማርያም ልጅ ከማርያም ይበልጥብኛል፣ ስለዚህም ልጇን እንጂ እርስዋን አላመልክም» አልኩት፡፡

እነዚህን ጥያቄዎች ሁሉ ስለጠየቀኝ ደስ አለኝ፡፡ ወደ ቦንጋ ስንደርስም እነዚህን ጥያቄዎች በተደጋጋሚ እንደምጠየቅ አውቅ ነበር፡፡

«መላእክትንስ?» አለኝ፡፡ «እነርሱ የእግዚአብሔር ልዩ መልእክተኞች ስለሆኑ እንጸልይላቸዋለን» አለኝ፡፡

«ነገር ግን እነርሱ መልእክተኞች ብቻ ናቸው፡፡ ስለዚህ እነርሱን የላካቸውን ታላቁን እግዚአብሔር ካወቅን ለእነርሱ አምልኮት የምናቀርብበት ምክንያት የለም፡፡ እግዚአብሔርን በፍጹም የማናውቅ ብንሆን ኖሮ መካከለኛ አማላጅ ያስፈልገን ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን እናውቀዋለን፡፡ ይህም ማለት የመላእክት አማላጅነት አያስፈልገንም» አልኩት፡፡

እንደ ሌሎቹ ብዙዎች ሰዎች ይህ ፖሊስም መላእክት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የሚያማልዱ አድርጐ የሚገምት ነበር፡፡ ስለ መላእክት ተግባር በሰፊው ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን ውስጥ እያወሳን ተነጋገርን፡፡ ፖሊሱም በጣም ደስተኛ በመሆኑ ጠቃሚ ውይይት በጋራ ለማድረግ ችለናል፡፡

በቦንጋም ለአንድ ወር ሙሉ አቆዩን፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፍነው ስለ እምነታችን እየተጠየቅን ነበር፡፡ በተለይም ለባለሥልጣኖች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ብዙ ነገሮች የሚናገረውን ለማስረዳት መቻል መልካም አጋጣሚ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም እንደዚያ ዓይነት ሰፊ ውይይት በዝርዝር ተነጋግረን አናውቅም ነበር፡፡

ከቦንጋ እንሥተው ግንቦ ወደሚባል ቦታ ሊወስዱን ወሰኑ። እዚያም እንደደረስን ስለ ጾም፣ ስለ ማርያም ስለ መላእክትና ስለ ታቦት ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ተጠየቅን።

በተለይም እኔን ከየት እንደ መጣሁ፣ ማን እንደ ቀጠረኝ፣ ምንስ እሠራ እንደነበር ሁሉ ጠየቁኝ። በዚህ ቦታ የነበሩት ባለሥልጣኖች ጨካኞች በመሆናቸው በመጥፎ ስም ይጠሩኝ ነበር። በአካባቢውም ችግር ፈጣሪ ነው በማለትም ከሰሱኝ።

«ክፍለ ሀገሩ ሁሉ ክርስቲያን እንደሆነ አታውቅም እንዴ?» ብለው ደጋግመው ጠየቁኝ። «ይህ ክፍለ ሀገር ምንም ወንጌላዊ አያስፈልገውም እያልን ለምን ወንጌላዊ ነኝ ትላለህ?»

ችግር በመፍጠራችሁ ምናልባት የአምስት ወር እሥራት ይፈረድባችኋል ብለው ነገሩን። አለመፍራቴን ሲያውቁ በእግር ብረት ለአሥራ አንድ ቀን አሠሩኝ።

አንዳንድ ሰዎች ስለ ሁኔታችን ሰምተው ፖሊሱን ከሰሱት። የክሱን ማመልከቻ ወደ ቦንጋ ልከው ግልባጩን ደግሞ ወደ አዲስ አበባ ላኩ። እነዚያ ባለሥልጣኖች ለጥያቄ ሲጠሩ፣ እኔም እግር ብረቱ ተፈታልኝ። ቢሆንም በዚያ በግንቦ እሥር ቤት ተጨማሪ አንድ ወር አቆዩን።

## በእሥር ቤት መስበክ

የቀድሞ ባለሥልጣኖች በመቀየራቸው በምትካቸው በተተኩት አዳዲስ ባለሥልጣኖች ዳግመኛ ለመጠየቅ ተጠራሁ። ሆን ብለው አስቸጋሪ ጥያቄ በመጠየቅ ከእኛ ስሕተት ለማግኘት ይጥሩ ነበር። የኦርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን እንደ ተሳደብን አድርገው ለመክሰስ ጥቃቅን ምክንያቶችን ይፈልጉብንም ነበር።

በዚህ ቦታ በጣም መጥፎ አያያዝ ነበር የተያዝነው። መጥፎ ምግብ ያቀርቡልን ስለነበር ሆዳችን ሁልጊዜ እንደ ታመመ ነው። የምንጠጣውም የተበከለ ውኃ ነበር።

ከጥቂት ሳምንት በኋላ ብዙ ገጽ ያዘለ ጽሑፍ ያለበትን ማህደር አመጡልኝ።

«እነዚህ ሁሉ የተከሰስክበትን ጉዳዮች የያዙ ወረቀቶች ናቸው። ይህንን ክስ ፍርድ ቤት በቅርቡ ያየዋል። በደንብ አንብባቸውና መልስህን ለማዘጋጀት ትችላለህ» አሉኝ።



ወረቀቶቹንም ኤግዚቢት (ማስረጃ) ብለው ይጠሯቸዋል።

የተሰጡኝን ወረቀቶች ጨርሼ ለማንበብና የተከሰስኩባቸውን ነጥቦች አጣርቼ ለመረዳት ረዥም ጊዜ ወሰደብኝ። በሚገባ ካጠናሁኝ በኋላ ለአዛገቡ ለመመለስ ተዘጋጀሁ።

«በእያንዳንዱ ገጽ መፈረም አለብህ። ይህም ማለት ገጾቹን በሙሉ አንብበህ ተረድተህ ክሱም እውነት መሆኑን ተስማምተሃል ማለት ነው» ተባልኩ።

እኔም ለአዛገቡ በማንኛውም ገጽ ላይ እንደማልፈርም ነገርኩት።

«ሌላ የምትጨምረው ነገር አለህ?» አለኝና ጠየቀኝ።

«አንዳንድ ነጥቦች እውነት ናቸው፣ ሌላው /አብዛኛው/ ግን ውሸት ነው። ማርያምንና መላእክትን እንዲሁም የኦርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን ተሳድቤ አላውቅም። እነዚህ ነጥቦች ከእውነት የራቁ ናቸው።»

ለክሱ መልስ ለመስጠት በጥንቃቄ የጻፍኩትን የመቃወሚያ ጽሑፌን ከመጽሐፍ ቅዱስ እያጣቀስኩ በመጻፌ በተጨማሪም ከአዲስ ኪዳን የምሰብከውን እውነተኛ መልእክት በሰፊው በማስረዳት ጽፌ ለአዛገቡ ሰጠሁ። አዛገቡም ትሑት ነበርና የመልስ ጽሑፌን ተቀብሎ በማህደሬ ውስጥ ከተተው። ወረቀቱም ለፍርድ ቤቱ ዳኛ የሚቀርብ ነው።

አንድ ቀን በጠዋት ወደ ፍርድ ቤት ተጠራሁ። በዚያውኑ ዕለት ዳኛው ሲገቡም የደም ፍንጣቂ በልብሳቸው ላይ ይታይ ነበር።

«መሐሪ!» አሉና ተጣሩ።

«አቤት!» አልኳቸው

የተጠራሁትም የክስ ማህደሬ ቀርቦ ኖሮ ሲነበብ ልሰማ ነበር።

«የተከሰስክበትን ምክንያት ሰምተሃል። ምን ትላለህ?» አሉኝ ዳኛው።

## ለጊዜው በነፃ መለቀቅ

እኔም፣ «በክሱ ምክንያቶች አንዳንድ ነጥቦች እውነት ናቸው። ነገር ግን ብዙዎቹ ነጥቦች ከእውነት የራቁ ናቸው» ብዬ መለስኩኝ።

«ከታሠርክ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ?» አሉና ጠየቁኝ። «የታሠርክበት ጊዜ ይበቃል። አሁን ነፃ ሆነሃል። ወደ ቤትህ መሄድ ትችላለህ» ብለው

አስታወቁኝ:: ወዲያውኑ በታሠርኩ ጊዜ ወታደሮች የወሰዱትን ዕቃዎቼን በሙሉ እንዲመልሱልኝ አዘዟቸው::

አንዱ ባለሥልጣንም፣ «ይህ ሁሉ ችግር የመጣብህ ከስብከትህ የተነሣ ነው:: ስብከትህን አቁመህ ችግር እንዳይመጣብህ ማድረግ ብልህነት ነው» አሉኝ::

«ጌታ የጠራኝ እንድሰብክ ነው:: እርሱ እስካላስቆመኝ ድረስ እኔ ለማቆም አልችልም» አልኳቸው::

ከእሥር ቤት በነፃ የተለቀቅኩ መሆኔን የሚገልጽ ሕጋዊ ወረቀት ከፖሊስ ጣቢያው እንዲሰጠኝ ጠየቅኩኝ:: ሳይሰጡኝ ሊሰዱኝ ቢያስፈራሩኝም ሳልቀበል እንደማልሄድ ነገርኳቸው:: «እንግዲያውስ በዚያ አካባቢ ከእንግዲህ አልሰብክም ብለህ ፈርም:: ይህን ካደረግክ ብቻ ነው በነፃ የተለቀቅክበትን ሕጋዊ ወረቀት የምንሰጥህ» አሉኝ::

እኔ በፍጹም አልፈርምም አልኳቸው:: እነርሱም በታሰርኩበት ወቅት የወሰዱብኝን ንብረቴን ለመመለስ አልፈለጉም::

በመጨረሻም መብቴ ካልተከበረልኝና በእኔ ላይ የሚያሳዩት ባህሪያቸው እስካልተለወጠ እንደማልመለስ ተረዱ:: መጽሐፍ ቅዱሴንም መለሱልኝ:: ካሴቱንና ቴፔንም እንዲመልሱልኝ ጠየቅኳቸው:: ካሴቶቹን ከመለሱልኝ በኋላ ቴፕ መጥፋቱን ገለጹልኝ:: እስኪሰጠኝ ድረስ ከቢሮ እንደማልወጣ ነገርኳቸው:: በመጨረሻም ዕቃዬ በሙሉ ተመለሰልኝ:: በነፃ የተለቀቅኩበትም ሕጋዊ ወረቀት ተሰጠኝ::

በአላስፈላጊ ሁኔታ ስላዘገዩኝና ስላስቀየሙኝ ይቅርታ ጠየቁኝ::

«ማንም አላስቀየመኝም:: ወንጌላዊ እንደ መሆኔ ይህ የሥራዬ አካል ነው:: ባደረጋችሁብኝና በተናገራችሁኝ ሁሉ አልቀየማችሁም» አልኳቸው::

ለእነርሱ ግን መልሴ አጥጋቢ አልሆነላቸውም:: ምናልባት ቂም ይዞብን ሌላ ነገር ያመጣብናል ብለው ይሰጉ ነበር:: ስለዚህ ከፖሊስ ጣቢያው ከመሄዴ በፊት ይቅርታ እንዳደርግላቸው ይወተውቱኝ ነበር:: በእኔ ላይ ስለፈጠሩብኝ ችግር በጣም እናዝናለን እባክህ ይቅር በለን ይሉ ነበር:: ግን ልባቸውን እንዴት አውቃለሁ?

«እግዚአብሔር ይቅር ይበላችሁ» አልኳቸው::

እነርሱም፣ «አሜን፣ አሜን» አሉ::



ሁሉም ደስ ብሏቸው እጅ ለእጅ ተጨባብጠን ሄድኩኝ::

በወቅቱ ለሚያስፈልገን ሁሉ ወጪ እያደረግን ለሦስታችንም የተረፈን አምስት ሳንቲም ብቻ ነበር:: እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ እንጓዝ ነበርና ሦስታችንም በጣም ተራብን:: በመንገድ ላይ ገዝተን ለማኘክ ሸንኮራ አገዳ እንኳን ለማግኘት አልቻልንም:: በመጨረሻ ግን ወደ ቦንጋ ደረስንና ምግብ አገኘን::

እሥር ቤት አብሮኝ የነበረው ዘውዴ ጧት በማለዳ ወደ እኔ መጣ:: ሌሊቱን በአንድ ወዳጁ ቤት ነበር ያደረው:: መጥቶም፣ «መሐሪ» አለኝ:: እኔም፣ «አቤት» አልኩት::

# ሞት ዳግም ያንኳኳል

አባቴ በጠና እንደ ታመመ ወሬው እንደ ደረሰው ነገረኝ:: ምናልባት መልእክተኛው በግልጽ አልነገረኝም እንጂ ሞቶም ሊሆን ይችላል::

አባቴን ለማየት የሦስት ሰዓት መንገድ ከመጓዙ አስቀድሞ ለአባቴ አስፈላጊውን መድኃኒት ለመግዛት ገንዘብ ለመበደር እንዲሞክር ነገርኩት:: እኔም መሬቱን እያረስኩለት እንደምጠብቀው ገለጽኩለት::

አባቱን ለመጠየቅ ዕቅዶ ለመሄድ ተነሣ:: እኔም ጠዋት በማለዳ ተነሥቼ ማረሻና ቀምበር በመያዝ ሁለት በሬዎችን ጠምጄ ለማረስ ተዘጋጀሁ:: ወዲያው ከውጪ ጩኸት ተሰማኝ::

«ወየው፣ ወየው፣ ወየው» እያሉ የሚያለቅሱ ሰዎች ድምጽ ነበር::

ወደ ውጪ ስወጣ ብዙ ሰዎች ዘውዴን ከብበውታል:: እርሱም በሁለት እጆቹ ራሱን ይዞ ወዲያ ወዲህ እየተዘዋወረ፣ «ወየው አባቴ፣ ወየው አባቴ» እያለ ያለቅስ ነበር:: ምክንያቱም የአባቱ መሞት በዚያው ማለዳ ተነግሮት ኖሯል::

ታስታውሱ እንደሆነ ላለፉት ሁለት ወራት በእሥር ቤት እንድንሠቃይ ምክንያት የሆኑን እኚህ የሞቱት የዘውዴ አባት ናቸው:: ከዘመዶቹና ከወዳጆቹ ጋር ሆኖ ዘውዴ በአባቱ ቀብር ላይ ለመገኘት ጉዞ ጀመሩ::

ለአንድ ወር ሙሉ እዚያው ቆየ::

እኔም መሬቱን እያረስኩለት በነበረ ጊዜ ወንጌላዊ ኢካሶ ሊጉበኘኝ መጣ:: እርሱም በሌላው እሥር ቤት ለሁለት ወር ታሥሮ ነበር የወጣው:: ሁለታችንም በመገናኘታችን በጣም ደስ አለን::

እኔ በታሠርኩኝ ጊዜ ወዳጄን ኢካሶን፣ «አሁን አንተ ወደ ወላይታ መመለስ አለብህ:: በእሥር ቤት አምስት ዓመት ሊያቆዩን እየሞከሩ ናቸው:: አንተ ሄደህ ካልተናገርክ ሁላችንም የት እንዳለን የሚያውቅ አይኖርም» አልኩት::

ይሁን እንጂ ወደ ወላይታ ከመሄዱ በፊት እርሱም ለሁለት ወር ታሠረ::

በከፋ በነበርን ጊዜ ብዙ ነገሮችን ያከናወንን ይመስላል:: ከመፈታታችን በፊትም ጌታ በብዙ መንገዶች ስለባረከን እጅግ ተጽናንተን ነበር::

ከቀብር በኋላ የዘውዱ እናት አብረውት ሊኖሩ ይዟቸው መጣ:: እርሳቸውም ክርስቲያን ስለነበሩ ኅብረታችንን አጠናከሩት:: የዘውዱ ሚስት ግን በጠንቋይ መንፈስ የታሠረች ነበረች:: ጠንቋዮቹን ስዎች ቃልቻዎች ብለን እንጠራቸዋለን:: የዘውዱ ሚስት ለረዥም ዓመታት ወንጌልን ስትቃወም የኖረች ስትሆን፣ በመጨረሻ ግን በክርስቶስ አምና ከተቆጣጠራት የሰይጣን መንፈስ ነፃ ወጥታለች:: አንዳንድ ጐረቤቶችም ወደ ክርስትና እምነት መጡ:: ዘውዱና ሌሎች ሁለት ሰዎች ከተጠመቁ በኋላ በዚያ አካባቢ የጸሎት ቤት ተመሠረተ::

ከዚያም በኋላ እኔ ቦንጋ ወደሚገኘው የኤስ አይ ኤም ጣቢያ ሄድኩኝ:: ስማቸውን ዛሬ ለማላስታውሰው ሚስዮናዊ ለተወሰነ ጊዜ ወደ ወላይታ እንደምሄድ ነገርኳቸው:: በቦንጋ ከተማ በሚገኙት ክርስቲያኖች ላይ ተስፋ ቆርጬ ነበረ:: መታሠራችንን እያወቁ አንድ ጊዜ እንኳን መጥተው አልጠየቁንም:: ከእሥር በተፈታን ጊዜ በኪሳችን የተረፈን አምስት ሳንቲም ብቻ ነበርና አንዳች ዕርዳታ አላደረጉልንም::



# ወደ ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ መግቢያ

*አቶ መሐሪና የአገሩ ልጆች /ጓደኞቹ/ ከኤስ አይ ኤም ጋር ወደ ቆላ ወደ ደቡብ ባኮ በሄዱ ጊዜ በእርግጥም የአገሩ ተወላጆች የሆኑ ሚስዮናውያን ወንጌላውያን ሆነዋል:: በባሕል፣ በመልክዓ ምድር አቀማመጥና በቋንቋ ወደተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረዋል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን በዘላኖች መካከል አዳርሰዋል:: ይህ ተጨማሪና ከባድ ሥራ ሲሆን፣ ኤስ አይ ኤምን ተክተው የሚያከናውኑት ነበር:: የኤስ አይ ኤም አባሎች ለወንጌላውያን የገዙትን ምግብ በአየር እያቀረቡላቸው የመድኃኒት እርዳታም ያደርጉላቸው ነበር::*

*እግዚአብሔር በረዳቸው መጠን በማንኛውም ቦታ የምእመናንን ኅብረት ለመመሥረት ዕቅዳቸው ቢሆንም፣ ዳር ቆመው ለሚመለከቱ ግን የሚቻል አይመስልም ነበር:: ሁሉ ነገር ፈጣን ባይመስልም ጊዜው ግን ሁልጊዜ በጌታ እጅ ነው::*

*የብቀላ ግድያ በግድየለሽነት ሕይወትን ማጥፋት ለምሳሌ፣ የጴጥሮስ ሞት የመሳሰሉት ሁሉ፣ አስቀድመው የማያውቁትና ያጋጥመናል ብለውም ያልጠበቁት ክስተቶች ነበሩ:: እንደዚያ ዓይነት ጎጂ ባህል መቅረት ነበረበትና እነርሱም ከሥሩ ሊነቅሉት ችለዋል::*

*ባህላዊ ለውጦችን በማምጣት ረገድ ከአገሩ ወንጌላውያን የበለጠ የቆላው አካባቢ ክርስቲያኖች በጣም የጐላ ሚና ተጫውተዋል:: በአፋቸው ከሚናገሩት የበለጠ በሕይወታቸው የሚያሳዩት መልካም መመላለስ ምስክርነታቸውን በግልጽ ያሳይ ነበር::*

*አቶ መሐሪ በበና ሕዝብ መካከል ከሠሩ በኋላ ለአጭር ጊዜ በኦሞ ወንዝ ሸለቆ አካባቢም በሙርሲ ሕዝብ መካከልም ሠርተዋል:: ይህም ከበና ሕዝብ ለሚኖዊና ምዕራባዊ ክፍል ማለት ነው:: እርሳቸውና ሌሎቹ የአገሩ ተወላጅ የሆኑ ወንጌላውያን በቆላማው አለታማ ምድር መልካም ዘር ቢዘሩም ፍሬው እንደጠበቁት አልሆነላቸውም:: የወንጌላውያን ሥራ የኅብረት ሥራ ነው (ዮሐ 4:27-45)::*

# አራት ዓመት በሐመር

## ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

ወደ ወላይታ ከሄድኩኝ በኋላ ተመልሼ ወደ ጎፋ መጣሁ:: በከፋ ስለሆነው ነገር ሁሉ ለሚስተር ማክሊላን ነገርኳቸው:: በከፋ ያለውን የወንጌል ሥራ እግዚአብሔር እንደ ባረከ በሰሙ ጊዜ ማክሊላንና ሌሎች ክርስቲያኖች ሁሉም ደስ አላቸው::

ማክሊላን ወደ ሐመር ለመሄድ አመቺ ጊዜ መሆኑንም ሲነግሩኝ እኔም ያንን ስፍራ ሄጄ ለማየት ጊዜዬን እጠብቅ ነበር::

ለወንጌል አገልግሎት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሐመር ስንደርስ በአካባቢው ምንም ክርስቲያኖች አልነበሩም:: በዚያ በሐመር ሕዝብ መካከል ሄዶ ለመኖር የቀደሙን ወንጌላውያን አልነበሩም::[1] በ1972 ዓ.ም ሰባት ማኅበር ተመሥርቶ እያንዳንዳቸው የራሳቸው የጸሎት ቤት አላቸው:: በእርግጥ እያንዳንዱ ማኅበር አነስተኛ ቁጥር ነበረው:: ነገር ግን ክርስቲያኖቹ ከመካከላቸው የወጡ ሰዎች ወንጌላውያን እንዲሆኑላቸው ያበረታቱአቸው ነበር::

በቆላማው ምድር የሚኖሩ ዘላኖች አደገኞች እንደሆኑ ሰዎች ይነግሩኝ ነበር:: በየዓመቱም የማያቋርጥ ግጭት እየተፈጠረ ብዙ ሰዎች ይገደላሉ:: ሕይወት እንደዚህ ከሆነ አንድ ቀን በዚያ ሸለቆ ውስጥ እኔንም ሊገድሉኝ ይችላሉ እል ነበር::

ይህንን አሳብ በአእምሮዬ ይዤ ምናልባት በዚህ ቦታ በሐመር ከተገደልኩ ልጆቼ በሕይወታቸው መሥራት የሚገባቸውን ነገሮች በአንድ ደብተር ሙሉ ጽፌ አዘጋጀሁ::

በበና ሕዝብ መካከል ወንጌልን ለመስበክ ወደ ሐመር በሄድን ጊዜ በተናጠል አልሄድንም:: ምን ጊዜም መንገዳችን አስተማማኝ ባለመሆኑ ለደህንነታችንም ስንል ሁለት ሁለት እየሆንን በመዘዋወር እናገለግል ነበር:: ወደ ድመካ[2] በሄድኩኝም ጊዜ ከወላይታ ሁለት ወንጌላውያን ከአሪ ቤተ ክርስቲያንም ሁለት ወንጌላውያን ነበሩ::

የበና ሕዝብና የአሪ ሕዝብ ወሰንተኞች ቢሆኑም፣ በመካከላቸው እንደ ሌሎቹ ጉሳዎች የማያቋርጥና ገንፍሎ የሚወጣ ጠብ አልነበራቸውም:: ይሁን እንጂ ከእኛ ከወላይታ ከመጣን ይልቅ ለአሪ ወንጌላውያን በበና ሕዝብ መካከል እየተዘዋወሩ ለመስበክ ቀላል



አልሆነላቸውም:: እነዚያን ከአሪ የመጡትን ሁለት ወንጌላውያን ለመግደል ተከታታይ ሙከራ ያደርጉባቸው ነበር:: ሰላዮች ናቸው ብለው ስለሚጠረጥሯቸው በአፋጣኝ ወደመጡበት እንዲመለሱም ነግረዋቸዋል::

የአሪ ወንጌላውያንም ይህንን አሳባቸውን ተቀብለው ለማምለጥ ቢሞክሩ፣ በጫካ ውስጥ ጠብቀው በመንገድ እንደሚገድሏቸው ያውቁ ነበር:: ነገር ግን እዚሁ መቆየት የበለጠ የሚሻልበት ምክንያት አንድ አደጋ ለመጣል ቢፈልጉ እንኳን ከጫካ ይልቅ በመንደር ውስጥ መሆን የመከላከል ዕድል ስላለው ነው::

አንዳንድ የበና ጦረኞች ከአሪ ሕዝብ ጋር የረዥም ጊዜ ግንኙነት ነበራቸው:: ወንጌላውያኑ ሰላዮች ናቸው ብለው አያምኑም:: በአሪ ውስጥ ት/ቤቶች እንዲገነቡ አማኞች ያበረከቱትን አስተዋጽኦና ወደዚህ የመጡትም ወንጌልን ለሕዝቡ ለማስተማር ብቻ መሆኑን አሳምረው ያውቃሉ::

በአንድ አጋጣሚ ወንጌላውያኑ እንዳይጠቁ ለመከላከል ከአካባቢ ሰዎች አንድ ሰው በእህል ጉተራ ላይ ዘሎ ወጣ:: ያን ጊዜ ሌሎች ሰዎች ወንጌላውያኑን ለመግደል በሩቅ ሆነው ጠመንጃቸውን ደግነውባቸው ነበር:: እነዚህን ወንጌላውያን ለመግደል የአሪ ሕዝብ ሁሉ ቢስማማም አንድ ሰው ግን እንዲገደሉ አልተስማማም:: በኋላም የመንደሩን ሽማግሌዎች ሰብስቦ እነዚያ ወንጌላውያን ሰላዮች አለመሆናቸውን አስረድቶ አግባባቸው:: ይሁን እንጂ የመንደሩ ጦረኞች በጣም ተቆጡ፣ ተበሳጩም፣ በኋላም ልብሱን ገፍፈው በመውሰድ ቀጡት::

በዚያ በቆላማው አካባቢ መሥራት ለእኛ አዲስ የማንለምደው ሆነብን፣ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ለመማር የቻልንበትም ስፍራ ነው::

## ቤተ ክርስቲያንን እስቦ መትከል

ስዚያ በቆላ አካባቢ በአራት የተለያዩ ሕዝቦች መካከል አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናትን ለመመሥረት በነበረን አሳብ ወንጌልን መስበክ ጀመርን:: እነዚያም አራት ቦታዎች በሼዳ፣ በና፣ ፀማይና ሐመር ይባላሉ:: በመጨረሻም የውጪ ሚስዮናውያን ሲለቀቁ፣ እኛም «እዚህ ራሳችንን ችለን እንዴት ለመኖር እንችላለን? ምን እናድርግ? ለራሳችንና ለሚስቶቻችን ምግብ እንዴት ለማግኘት እንችላለን?» ብለን አሰብን::

ነገር ግን የውጪ ሚስዮናውያን እስከሚሄዱ ድረስ ለአራት ዓመት ሙሉ ለመሥራት ወሰንን፡፡ በእነዚያ ዓመታት ውስጥ በእግር እየተዘዋወርን ወንጌልን መስበክ በሚገባው ቦታ ሁሉ ሰብከናል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሚስተር ቻርሊ ቦንክ በላንድሮቨር ያደርሱን ነበር፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከአንዳንድ የስብከት ጣቢያ በአይሮኘላን ለመጓዝም ዕድል አግኝተናል፡፡ በቆላ የሚኖሩ ሰዎች ከእኛ በብዙ መንገዶች ይለያሉ፡፡ ቋንቋቸው፣ ልማዳቸውና ምግባቸው ሁሉ ከእኛ የተለየ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ምንም ቋንቋቸው ስለማይገባንና የምናደርገውን ስለማያውቁ ይቆጡ ነበር፡፡ በአስተርጓሚ በኩል እንነጋገርና ሁሉንም ስናስረዳቸው ተመልሰን ወዳጆች እንሆን ነበር፡፡ ምግባቸውን መብላትና ወተታቸውንም መጠጣት ተለማመድን፡፡ ቀስ በቀስም ለመግባባት ችለን ጥሩ ወዳጆች ሆንን፡፡

በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት እኔ በአካባቢው እየተዘዋወርኩ በምሰብክበት ጊዜ ባለቤቴና ልጆቼ በድመካ ኤስ አይ ኤም ግቢ ውስጥ ነበሩ፡፡ ብርሃኑ ኃይሌ የተባለው ወንጌላዊና ሁለቱ ከአሪ የመጡት ደግሞ ግርማ እና ጴጥሮስ ይባላሉ፡፡ ከአሪ የመጡት ወንጌላውያን በዚህ የኢትዮጵያ ክፍል ወንጌልን ለመስበክ ከእኔ ጋር የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያን ነበሩ፡፡ ለምናውቃቸው ሰዎች ሁሉ መንፈሳዊውን ግንዛቤ እናካፍላቸው ነበር፡፡

ስለ ሰዎቹ ሁኔታ ጥቂት ካወቅንና ቋንቋቸውንም ትንሽ መስማት ስንጀምር ወደ ሌላ መንደር እንሄዳለን፡፡ እኔ በሼዳ በሚባል ስፍራ እኖር ነበር፡፡ ከዚያ እየተነሣሁ ወደ ቅርብ አካባቢዎችም እየተዘዋወርኩ ወንጌልን መስበክና ማስተማር የዕለት ተዕለት ተግባሬ ነበር፡፡

ከአሪ የመጣው ግርማ ቡሪ ወደሚባል ስፍራ ሄደ፡፡ ለእርሱ መጠለያ የሚሆን አነስተኛ ቤት እዚያው ሠርተንለታል፡፡ በተጨማሪም ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ተሰብስበው የሚማሩበትን ትንሽ ጐጆ ሠርተን ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ግርማና እኔ አብረን ካገለገልን በኋላም ለየብቻችን በተለያዩ ቦታዎች ሰፍረናል፡፡ እርሱም በቡሪ ጥቂት ሰዎችን መሰብሰብ ጀመረ፡፡ በሻንቆ ደግሞ እኛ የተወሰኑ ሰዎችን እያበረታታን ተሰብስበው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩ እናደርግ ነበር፡፡ ሦስተኛው ቦታም ላላ ይባላል፡፡ በተጨማሪም በፀማይ ሕዝብ መካከል ሻላ የሚባል የገጠር መንደር አገኘን፡፡



በቆላማው መሬት ሰዎች ተበታትነው በተሠሩ ጐጆዎች ይኖሩ ነበር፡፡ በደጋማው መሬት እንደሚኖሩ ሰዎች የጋራ እንቅስቃሴ አይታይባቸውም፡፡ እዚህ ታዲያ ማዕከል የሆነ ቦታ አቋቁመን ሰዎች እየመጡ እንዲሰሙን እናበረታታቸው ነበር፡፡ ይህ ዘዴ እንግዲህ በደጋማው አካባቢ ከሚኖሩ ሰዎች የበለጠ ነው፡፡

ቀስ በቀስም ሥራችንን በአካባቢው በማስፋፋት አምስተኛ አድርገን የሠራነው ቦታ መሸጌ ይባላል፡፡ ስድስተኛውም ዴዌላ ሲሆን፣ ሰባተኛው ደግሞ አልዱባ ይባላል፡፡ ሖጨረሻ ላይ ሚስዮናውያኑ ከመሄዳቸው በፊት የመሠረትነው ቦታ ወሮ ይባላል፡፡ በድመካ ሥራችንን እንደጀመርን ሚስተርና ሚስ ሙሬይ ኦሬ የሚባሉ የውጪ አገር ሚስዮናውያን እዚያ የነበረውን የኤስ አይ ኤም ጣቢያን ለቅቀው ሄደዋል፡፡

በሐመር ፍሬያማ በሆንንባቸው ዓመታት ውስጥ ብዙ ነገሮች ተከናውነዋል፡፡ ከ1966 ዓ.ም[3] በኋላ በአገራችን ብዙ ለውጦች ተደርገዋል፡፡

በሐመር መኖርና መሥራት በጣም አደገኛ ነበር፡፡ እኛ እዚያ አገር ከመድረሳችን በፊት እንስማ የነበረው ሁሉ አላስፈራንም ነበር፡፡ እዚያ አገር ሞት ቅርብ ነው፣ መግደልም ቀላል ሲሆን፣ ከእሾሃማዎቹ ዛፎች የሚደርስብን ተከታታይ መቁሰል ማለቂያ አልነበረውም፡፡ አንዱ ሳይታሰብ በወፍራም ዱላ የአንዱን አናት ፍርክስ ሲያደርግ ወይም ሌላው ሳይታሰብ በጦር በስተጀርባ ወይም በስተጐን ግጥም አድርጐ ሲወጋ ያ ሰው አለቀለት ሞተ ማለት ነው፡፡ ሰዎች ስዓታቸውን ለመቀማት ተብሎ ይገደሉ ነበር፡፡ ምናልባት ጴጥሮስ የተገደለውም ለዚሁ ይሆናል፡፡

የበና ሰዎች ቀስ በቀስ ዘአራታችን ላይ ተነሡብን፡፡ እኛ እስከምናውቀው ድረስ ምንም አላስቀየምናቸውም፡፡ እንዲያውም ቋንቋቸውን እየተለማመድን ነው፡፡ ወደምንሰብክበት ቦታ በቡድን ስለሚመጡ ሥራችንም እያደገ የሚሄድ ይመስለናል፡፡ እያንዳንዳችን የምንሠራው በተለያዩ ቦታዎች ሲሆን፣ ጐረቤቶቻችንም ወዳጆቻችን ይመስሉናል፡፡

## ጴጥሮስ ተገደለ

ከዕለታት አንድ ቀን የጴጥሮስ ሚስት ታመመችና መድኃኒት አስፈለጋት:: ከእነርሱ መኖሪያ እስከ ሚስዮኑ ጣቢያ ድረስ የጥቂት ሰዓታት ጉዞ ይወስዳል:: ስለዚህ ጴጥሮስ ከቤቱ ማልዶ በመውጣት ከሰዓት በኋላ መድኃኒት ይዞ ስመመለስ ወሰነ:: ዲመካ ደርሶ መድኃኒት ቢገዛም ወደ ቤቱ ግን አልተመለሰም:: ከሰዓት በኋላ ወደ ማምሻው ሚስቱ መጨነቅ ጀመረች:: ወደ ድመካም መልእክተኛ ላከች:: ሌሎች ሰዎችም ተነሡና አብረን ፍለጋ ጀመርን:: ሚስተር ቦንክ ላንድሮቨራቸውን እየነዱ በሚታወቁ ቦታዎች መከታተል ጀመሩ:: ሌሊቱን ሁሉ ስንፈልገው አደርን፣ ግን አላገኘነውም:: በዚያን ጊዜ አብዛኞቻችን ስለ መሞቱ እርግጠኞች ነበርን::

በሁለተኛው ማግሥት ለባለሥልጣኖች አመለከትንና ባላምባራስ አድነው ጥቂት ወታደሮች ሰጡን:: ዳግመኛ ሬሳውን ፍለጋ ጀመርን:: በሰማይ አሞራ ሲያንዣብብ አየን፤ ተከታትለን ስንሄድ ሬሳውን አገኘ ንና በእሸዛማው መሬት ላይ ቀበርነው:: ጅቦች አውጥተው ሬሳውን እንዳይበሉት ትላልቅ ድንጋዬችን በመቃብሩ ላይ ከመርን:: ከቀብር በኋላ ፖሊስ ምርመራውን ጀመረ፣ ነገር ግን ምንም አልተገኘም::

የእጅ ሰዓቱንና ልብሱን ለመውሰድ ተብሎ በጦር የተገደለባት ታማሚ ሚስቱ እንዴት እንደሆነች ለመናገር በጣም ይከብዳል:: ሚስቱ ባኮ ወደሚገኙት ቤተሰቦቿ ስትመለስ የእርሱን ቦታ የሚተካልን ሰው አልነበረምና ለጊዜውም ቢሆን ስብከቱ ተስተጓጉሎ ወይም ቆመ:: በኋላ ግን ከወላይታና ከአሪ በርካታ ወንጌላውያን ሄደው መስበክና ማስተማር ቀጠሉ::

ልክ በዚያን ጊዜ ልጆቼን ለመንከባከብ ለአጭር ጊዜ ወደ ወላይታ ተመለስኩኝ::

የወላይታ ሽማግሌዎች መማክርት ጠርተውኝ፣ «መሐሪ ለረዥም ዓመታት ከአካባቢህ ርቀህ በመሄድ ስትሰብክ ኖረሃል:: አሁን አንተ እያረጀህ ነው፣ አሁን እርሻህን እያረስክ ከቤተሰብህ ጋር የምትሆንበት ጊዜ ነው:: ከእንግዲህ ወደዚያ አደገኛ ቦታ ወጣቶች ይሂዱ ብለው መከሩኝ::»

እኔም መልሼ፣ «እርሻዬን እያረስኩ እንድቀመጥ እግዚአብሔር አላሳሰበኝም:: እንዴት ጥሩ ምክር ሰጣችሁኝ?» ካልኳቸው በኋላ፣



«ሕይወቴ እስካለች ድረስ ስብከቴን ስመቀጠል እፈልጋለሁ:: አሁን ወደ ሐመር መመለስ አለብኝ» አልኳቸው::

እነርሱም እንድሄድ ፈቀዱልኝ:: ጴጥሮስ ይሰብክ በነበረበት ቦታ ሄጄ ስመሥራት ወሰንኩኝ:: ጴጥሮስን ማን እንደ ገደለው እስካሁን አልታወቀም:: ሁሉም ሰው ለእኛ ወዳጅ መስሎ ነበር የሚቀርበን:: ስለዚህ እኔ እዚያ ሄጄ እንድሠራ ስወስን ለብቻዬ ሄጄ ለብቻዬ እየኖርኩ የምሰብክ መሆኔን ባውቅም ምንም ፍርሃት አላደረብኝም ነበር:: እዚያ እንድሄድ የፈለገኝ እግዚአብሔር ስለሆነ ከሚደርስብኝም ክፉ ነገር ሁሉ እርሱ እንደሚታደገኝ ሙሉ እምነት ነበረኝ::

## በበና የመጀመሪያው አማኝ

ወዳሰብኩት ቦታ ደርሼ ብዙ ቀናት ሳልቆይ ጋሪሾ ከሚባል የአካባቢው ነዋሪ ጋር አስተዋወቁኝ:: ያን ጊዜ በቆላው ሕዝብ አካባቢ ሰውን ገድሎ መዘረፍ የተለመደ ነበርና ይህ ያስተዋወቁኝ ሰውም በመግደል ወንጀል ታሥሮ የነበረ ሲሆን፣ ለአሥራ አምስት ዓመት ከተፈረደበት በኋላ አሥራ ሁለት ዓመት ታሥሮ ተፈትቷል:: በጨንቻ የእሥር ቤት ቆይታው የአማርኛ ቋንቋ ከመማሩም በላይ ወንጌል ተመስክሮለት በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ነበር::

ያን ጊዜ በእዚያ ቦታ የነበሩት የውጪ አገር ሚስዮናውያን የነበሩት ሚስተር ቻርሊ ቦንክና ባለቤታቸው ለዕረፍት ወደ አገራቸው በመሄዳቸው በምትካቸውም ማልከምና ጂን ሃንተር የሚባሉ ባልና ሚስት መጥተው ነበር:: ሚስተር ሃንተር ጋሪሾ የእኔ አስተርጓሚና መንገድ መሪ እንዲሆነኝ እና ቋንቋቸውንም እንዲያስማምደኝ ሁኔታውን ስለአመቻቹልኝ ወዲያው ሁለታችንም ጓደኞች ሆንን፣ እንደ ዳዊትና ዮናታን በፍቅር ተጐዳኘን::

ሚስተር ሃንተር በአቅራቢያው መንደር አጠገብ የአይሮኘላን መነሻና ማረፊያ ነበራቸው:: ይህም ማለት በአይሮኘላን ምግብ ይቀርብልን ነበር:: ለሕክምና አገልግሎትም ነርሶች ይጠቀሙበታል:: እኛም ለስብከት ረዥም ርቀት በመሄድና በመምጣት ብዙ ተጠቅመንበታል:: አይሮኘላኑ የዓለም አቀፍ ሚስዮናውያን ድርጅት ንብረት የነበረ አይሮኘ ላን ሲሆን በብዙ መንገድ ረድቶናል::

እኛም በመንደሩ ውስጥ ሁለት ቤቶች መሥራት ጀመርን:: አንዱ ቤት ለእኔና ለቤተሰቤ ሲሆን፣ አንዱ ቤት ደግሞ ለጋሪሾና ቤተሰቡ

የሚሆን ማለት ነው። ከሦስት ወር በኋላ ሁለቱንም ቤቶች ሠርተን ስንጨርስ፣ በዚያ ገለልተኛ ስፍራ ለመኖር ልጆቼ በጣም ተቸገሩብኝ። ልጆቼ በየጊዜው ይታመሙብኝ ስለነበር ባለቤቴ በቅርብ ሕክምና ልታገኝላቸው ወደምትችልበት የሚስዮኑ ጣቢያ ሄዳ ለመቀመጥ ተገደደች። ምክንያቱም እዚያ ሲቆዩ ወዲያው ይሻላቸው ነበር።

በቆላማው ምድር የሚኖሩ ሰዎች ከአካባቢያቸው ውጪ የሚመጡትን ሰዎች ጠላት ናቸው የሚል ግምት ነበራቸው። ምክንያቱም በተለያዩ ጐሳዎች መካከል የማያቋርጥ ግጭት ይከሠት ስለነበር፣ ወንጌላውያን ለዚያ ግጭት መንሥኤ የሆኑ ሰላዮች ናቸው ብለውም ይገምታሉ። አቶ ጋሪሾንም ከዳተኛ አድርገው ገምተውታል።

እርሱንም፣ «ለዚህ ሰው ቋንቋችንን ለምን ታስተምራለህ? ምሥጢራችንን ሁሉ እንዲሰማ ነው? ለምንስ አካባቢያችንን ታሳየዋለህ? ለምንስ ትከላከልለታለህ? እርሱ እኮ ጠላታችን ነው ምናልባት አንድ ቀን ይገደላል» አሉት።

አቶ ጋሪሾም ከእኔ እንደማይለይና ከእኔ ጋር እንደሚኖር ነገራቸው። «እርሱን ከገደላችሁት እኔንም ትገድሉኛላችሁ። ሁለታችንም በአንድ ጊዜ እንሞታለን» ካላቸው በኋላ፣ እኔም ሲገድሉኝ እንደሚፈልጉኝ ማወቄን ሲረዳ፣ «እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ አይዞህ፣ እነርሱም አይገድሉህም» ብሎ አረጋገጠልኝ።

ከዚያ በኋላ ሰዎቹ በግልጽ ይፈታተኑኝ ጀመር። ከአንድ ጊዜ በላይ በእነርሱና በጐረቤቶቻቸው መካከል ውጊያ እንደሚኖር ሲሰሙ፣ «በዚህን ጊዜ እንግዳ ሰው በመካከላችን እንዲኖር አንፈልግም። አንተም ልትገደል ትችላለህ። ይህ ችግር እስኪያልፍ ድረስ ከዚህ ብትሄድ ይሻላል» ብለው መከሩኝ።

## የብቀላ ግድያ

አካባቢያችን በረሃማና ቁጥቋጦ የበዛበት ስለሆነ ራሳችንን እንዴት መከላከል እንችላለን ? አብዛኞቹ ሰዎች በየመንደራቸው ከራሳቸው ላይ ቀይ ጭቃ ተቀባብተው ለውጊያ የተዘጋጁ ጦረኞች መሆናቸውን እየገለጹ ነው። እኛም ምን እንደምናደርግ አናውቅም ነበር። ወዲያው አሥራ አምስት ሰዎች ጠመንጃዎቻቸውን ተሸክመው እየተጣደፉ በመራመድ ያልፉ ነበር። በዳሌዎቻቸው ላይ እራፊ ጨርቅ አስረዋል። በራሳቸውም ላይ ቀይ ጭቃ ተቀብተዋል። ከመካከላቸው አንዱ ባትሪ



ነገር ይዟል። ይህም ሲፈነዳ ከፍተኛ ጭስ የሚወጣው ነው። እንደዚያ ዓይነት ነገሮችን የሚጠቀሙት ብዙውን ጊዜ ማር ለመቁረጥ ሲፈልጉ ንቦችን በጭስ ለማፈን ነው።

ባለቤቴንም፣ «ልጆቹን በፍጥነት ቤት ውስጥ አስገቢያቸውና በሩን ዝጊ» አልኳት።

ወዲያውም የጠመንጃ ተኩስና ጩኸት ሰማን። ባለቤቴ ከነልጆቿ ቤት መግባታቸውን ካረጋገጥኩኝ በኋላ ሁኔታውን ለማጣራት ወደ ጩኸቱ አቅራቢያ ሄድኩኝ። የሄድኩትም ዛጐል የሚባለውን ከጋሞ ጐፋ ያመጣነውን ታዳጊ ልጅ ይዤ ነበር። ይህ ልጅ እኔ ለአገልግሎት በምሄድበት ጊዜ ባለቤቴን የሚረዳት ነው።

ወዲያውም ሰዎች መጮህ ጀመሩ። ሰላይ ጠላት ወደ አካባቢያቸው እንደ መጣና የብቀላ ግድያ መፈጸም እንደሚገባቸው ያወሩ ነበር። ቀደም ብለው ያለፉትን አሥራ አምስት ታጣቂ ጦረኞችን ገድለው ገዳዮቹም ወደ ራሳቸው ክልል ፈጥነው በመሮጥ አምልጠዋል። በቆላማው ምድር የሚኖሩ ሰዎች የሩጫቸው ፍጥነት በጣም ያስደንቃል። በእሾሃማ ዛፎች መካከል እያፈተለኩ በጨረቃ ብርሃንና በፀሐይ ወጋገን ወደ ወገኖቻቸው በሰላም እስኪደርሱ ድረስ ሮጡ።

ወደ ተኩሱ ቦታ በደረስን ጊዜ አንድ የማውቀው ዋርቤ የሚባል ታዳጊ ወጣት ወድቋል። ከደረቱ ላይ በጥይት ተመትቷል። ጥይቱ ቀኝ ጐኑን በስቶ የገባ ሲሆን በሰውነቱ ውስጥ እንዳለ ነበር። ደሙ በቁስሉ በኩል እየጐረፈ በአቧራ ላይ ተደፍቷል። አይንቀሳቀስም።

እንድናነሳው ሰዎቹን ለማግባባት ስሞክር፣ «አባት፣ ይተዉ፣ አይንኩት» አሉኝ። የባላምባራስ አድነው ወንድም ደግሞ እርሱ እንደሆነ እየሞተ ነው ከነካኸው አንተም ትሞታለህ አለኝ።

ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ ኢላቤኒ እና ሌቤኒ የተባሉ ሁለት የሟች ወንድሞች በሰፈር ውስጥ ነበሩ። በዚህ በቆላ አካባቢ አንድ ሰው በጥይት ቢመታ ምንም የሚደረግለት እርዳታ ባለመኖሩ እስኪሞት ድረስ ዝም ብለው እያዩ ከመርዳት ይልቅ ሰውየው ሲሠቃይ ማየትን ይመርጣሉ።

ይህ ለእኔ አዲስ በመሆኑ ምንም አልተረዳሁም ነበር። ኪሴን ዳበስ ሳደርግ በአካባቢው ያሠራኋቸውን ት/ቤት ቁልፍ አገኘሁ። ሬሳውን ወደ ት/ቤት ወስደው እንዲያሳርፉ ነገርኳቸው።

ገና አልሞተም ነበርና በወለሉ ላይ አመቻችቼ አጋደምኩት:: ደሙ እንዲቆም ለማድረግ ቀና እያደረግኩት ውኃ እንዲጠጣ ሰጠሁት::

«ምናልባት ገዳዮቹ ርቀው አልሄዱም ይሆናል:: ይህ የብቀላ ግድያ ነው:: ይህን ልጅ ስትረዳው ሲያዩ ተመልሰው መጥተው አንተንም ሊገድሉህ ይችላሉ» አሉና ነገሩኝ::

ሊያስፈራሩኝ እየሞከሩ መሆናቸው ገብቶኛል:: ገዳዮቹ በጣም ርቀው መሄዳቸውን እኔም እነርሱም እናውቃለን::

«አይቻልም አልኳቸው:: እዚህ ቆሜ ይህ ልጅ እየተሠቃየ ሲሞት አላይም:: የምችለውን ዕርዳታ አድርጌለት ሕይወቱን ለማዳን መሞከር አለብኝ::»

«እርሱ እኮ አሁንም እንደ ሞተ ሰው ነው ብለው ሊያግባቡኝ ሞከሩ:: ምንም ልናደርግለት አንችልም አንድ ቀን የእኛ ጠረኞች ደግሞ ሄደው ይበቀሉአቸዋል:: በዚህ ጉዳይ ውስጥ አንተ እንድትሳተፍ አንፈልግም:: አንተ እዚህ አገር እንግዳ ስለሆንክ እንዲገድሉህ አንፈልግም:: አሁን ተወው አሉኝ::»

በዚህን ጊዜ ባለቤቴና ልጆቼ ወዳለንበት መጡ:: ሁሉም ፈርተው እያለቀሱ ነበር:: «ምን ለማድረግ እንደሚቻል ግራ የሚገባ ነገር ነው:: በዚህ አገሩ በብጥብጥ ውስጥ ባለበት መቆየት አለብን ወይስ ለተወሰነ ጊዜ ከዚህ መሄድ አለብን?» ተባባልን::

በዚያን ወቅት ጋሪሾ በአካባቢው አልነበረም:: ነገር ግን ከጨንቻ ያገባት ሚስቱና ልጆቹ በዚያ መንደር ውስጥ ይኖሩ ነበሩ:: ለተወሰነ ጊዜ መንደሩን ለቅቀን ለመሄድ ወሰንን:: መሸከም የምንችለውን ቁሳቁስ ሰበሰብንና ለሦስት ሰዓት ያህል ተጉዘን በሌላ መንደር ሌሊቱን አሳለፍን::

ወሬው ከሰፈር ወደ ሰፈር እየተዛመተ ሲመጣ ጠረኞቹ ሊገድሉህ እየመጡ ናቸው ተባልኩ:: ጠዋት ሲነጋ መቶ የሚያህሉ ሰዎች መሣሪያዎቻቸውን አንግበው ከሰፈሩ በሰላም እስክንወጣ ድረስ ሊሸኙን ከበስተውጪ ተከልክሉዋል::

እኔም ለሚስተር ሃንተር ወደ ዲመካ ደብዳቤ ላክሁኝ:: እርሳቸውም በዲመካ ሁለት ነርሶች ስላሉ የቆሰለውን ወጣት ሊረዱት ይችላሉ:: ነገር ግን ወደዚያ ሊመጡ አይችሉም አሉኝ:: ሌላው ወጣት እንዲሁ ከብቶቹን እያገደ በነበረበት ጊዜ በቆላ አካባቢ በተለያዩ ጐሳዎች መካከል



በተፈጠረው ግጭት ለሞት ተዳርጓል:: በዚህ ሁሉ የሕይወትን ባሕርይና ውጣ ውረድ በግልጽ ለማየት በቅተናል::

«ይህም ወንጌላዊነት ይሆን?» ብዬ ራሴን ጠየቅኩኝ::

ጋሪሾ ወደ ቤተሰቡ ተመልሶ ሲመጣ የተፈጸመውን ሁኔታ በመግለጽ ሁለት ሰዎችን ወደ ኬይ ከተማ በመላክ ለፖሊስ አስታወቅን:: ተመሳሳይ አቤቱታ ከየአቅጣጫው ለዓመታት ሲሰሙ የኖሩ በመሆናቸው በከተማው ጥቂት ወታደሮች ብቻ ስለነበሩ የየመንደሩን ግጭቶች ለማብረድ አልቻሉም::

ሰዎች ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ አካባቢውን ለቅቀን እንድንሄድ ይገፋፉን ነበር:: ምናልባት በመንደሩ ሰላም እስኪሰፍን ድረስ ወር ያህል ሊቆይ ይችላል:: ስለዚህ እስከዚያ ድረስ ግን አካባቢው በማያባራ ጦርነት ውስጥ ይሆናል:: እኛ እዚያ መንደር ብንቆይ የምናመጣው አንዳች ፋይዳ አይኖርም::

ይሁን እንጂ እኔ ወዲያው ወጥቼ ለመሄድ አልፈለግኩም:: ነገር ግን ባለቤቴ ወደ ወላይታ ተመልሳ እዚያ ት/ቤት ያስገባናቸውን ትላልቆቹን ልጆቻችንን ለማየት ትፈልጋለች:: ሚስተር ማልከም ሃንተርና ባለቤታቸው ለዕረፍት የሄዱ ሲሆን፣ ሚስተር ባርክ ፋህንስቶክ በባኮ ከሚሠሩበት ተጉዘው ሊጐበኙን መጡ:: እርሳቸውም የሙርሲ ሕዝብ ወንጌልን ለመስማት ይፈልጋሉ አሉኝ:: እዚያ ሄጄ በመካከላቸው እንድኖርና ወንጌልን እንድሰብክ አበረታቱኝ::

«እኔም ከዚህ ስፍራ አሁን ወጥተን ብንሄድ ይህ ሕዝብና በወላይታ ያሉ ሰዎች ፈርቼ እንደ ሸሸሁ ይገምታሉ:: ሌላ ማንም ወደዚህ ሊመጣ የሚፈልግ አይኖርም:: ሕዝቡን ከድተን የሄድንም ያስመስልብናል:: ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ እዚሁ መቆየቱ አደገኛ ቢሆንም እንኳን፣ ዝም ብዬ ልቆይና ሌላ ቦታ ሄደን እንድንሰብክ ተጠርተናል በእኛ ምትክም ሌላ ወንጌላዊ ይመጣላችኋል ብለን እንነግራቸዋለን:: ይህን ማድረግ ለሁሉም መልካም ነው» ብዬ መለስኩላቸው::

ሚስተር ባርክ ፋህንስቶክ በመልሴ በጣም ተደሰቱ፣ እኛም ስለዚህ ወደ መንደሩ ተመልሰን ለተወሰኑ ወራት ለመቀመጥ ሄድን::

## በሙርሲ ሕዝብ መካከል

ከግድያው ጊዜያት አያሌ ወራቶች ካለፉ በኋላ ወደ ባኮ ሄደን ሚስተር ባርክ ፋህንስቶክን ለመጐብኘትና በሙርሲ ሕዝብ መካከል ለስድስት ወር ያህል ለመሥራት ሄድን::

የሙርሲ ሕዝቦች በኦሞ ወንዝ ዳርቻ አካባቢ የሚኖሩ ናቸው:: የሣር ግጦሽ ወዳለበት ከብቶቻቸውን ከቦታ ወደ ቦታ እያዘዋወሩ የሚኖሩ ዘላኖች ሲሆኑ፣ ወንዶች ሙሉ በሙሉ የከብቶቻቸውን ደምና ወተት እየጠጡ የሚኖሩ ናቸው:: ከበሬዎቻቸውና ከወይፈኖቻቸው የደም ሥር ወጋ አድርገው ደሙን በመቅዳት ከወተት ጋር አቀላቅለው በፀሐይ ላይ ያቆዩታል፣ ከዚያም ግጥም አድርገው ይጠጡታል::

እኛ በዚህ ሁኔታ እየተመገቡ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመኖር አልፈለግንም ነበር::

አብዛኛውን ጊዜ ሰዎቹ በአነስተኛ የእርሻ መሬት በኦሞ ወንዝ ዳር በቆሎ ያመርታሉ:: አንዳንዴ የኦሞ ወንዝ ሙላትና ድንገተኛ ጐርፍ ሲመጣ የእርሻ ለብላቸውን እንዳለ ያወድምባቸውና ያለምግብ ያስቀራቸዋል:: ወቅቱን የጠበቀ ዝናብ ስለማያገኙ ዝናብን ተስፋ አድርገው አይጠብቁም ነበር:: ዘላኖች በመሆናቸውም የዝናብን ውኃ አያጠራቅሙም፣ እህልንም አያስቀምጡም:: በሙርሲ ሕዝብ መካከል ለስድስት ወር ሳንቆይ የምግብ ችግር አጋጠመን::

በሐመር በእኔ ቦታ ጌታሁን ደላ የሚባል ወንጌላዊ ተተካ::

በሙርሲ ሕዝብ መካከል ሃይላውሃ በሚባል የገጠር ከተማ የፖሊስ ጣቢያ ባለበት ወደዚህ ከተማ ለሰዎች ከጅንካ ከተማ የምግብ እህል የሚያመላልሱት የፖሊስ መኪናዎች ናቸው:: ለእኛም በአካባቢው ለሚገኘው የአይሮፕላን ማረፊያ በጊዜው ኤም. ኤ. ኤፍ ከሚባለውና ከኤስ ኣይ ኤም ጋር በቅርበትና በኅብረት ከሚሠራው ድርጅት ምግብ ይመጣልን ነበር:: ስለዚህ ከአካባቢው ሕዝብ ምግብ አንገዛም ነበር:: በሕይወታችን ዘመን ሁሉ መገበያየት የለመድነው ዓይነት ገበያ በዚህ ቦታ አይታይም:: የምንፈልገውን ምግብ ከውጪ እያስመጣን እንጠቀም ነበር::

በሙርሲ ሕዝብ መካከል እኔ፣ ገብረሥላሴ ማሪዛ እና እሥራኤል አንጄሎ ሆነን ሦስታችንም እንሠራ ነበር:: በዚህን ጊዜ ባለቤቴ ወላይታ ነበረች:: ሁለቱ ወንጌላውያን ከሚስቶቻቸው ጋር ነበሩና አምስታችን ምግብ ለማግኘት እንቸገር ነበር::

እዚያ እሠራ በነበርኩ ጊዜ በአሜባ ተቅማጥ ክፉኛ ታመምኩኝ:: ምንም ዓይነት መድኃኒት ለማግኘት ባለመቻሌ ልሞት ቀረብኩኝ:: እግዚአብሔር ማረኝና ወዲያው አገገምኩኝ:: ይሁን እንጂ ለረዥም ጊዜ አቅም ነስቶኝ ሰነበትኩኝ::



ወደ መጨረሻው አካባቢ የኤም.ኤ.ኤፍ አይሮፕላን በድንገት መምጣቱን ሲያቆም፣ የምግብ ማግኛ መንገድ ሙሉ በሙሉ ተቋረጠብን:: አዋቂ ሰዎች አምስት ስንሆን ምን እንደምናደርግ ግራ ገባን:: ከደጋማው ምድር ምግብ ገዝተን ወደ ሸለቋማ አካባቢ ልናመጣ የምንችልበት ምንም መንገድ አልነበረም:: በመጨረሻ ግን ለሚስተር ፋህንስቶክ ሚስተር ማክሲላን በሬድዮ በመገናኘት ችግራችንን እንዲያስረዱልን መልእክት ለመላክ ቻልን:: ከዚያ ሚስተር ማክሲላንና ሌሎች ክርስቲያኖች የአራትና የአምስት ቀናት ጉዞ ከጉፋ ተጉዘው ምግብ አመጡልን:: እነርሱ በደረሱልን ጊዜ ያለንን ምግብ አሟጥጠን ጨርሰን ስለነበር እንዴት እንደምንኖር ግራ ገብቶን ነበር::

ከዚያም ያልጠበቅነው ወሬ ወደ እኛ ቀድሞ ደረሰ:: ይኸውም የውጪ አገር ሚስዮናውያን ከዚያ አካባቢ እንዲወጡ የሚል ነበር:: ሚስተር ሃንተርም ወደ ሐመር ተመልሼ ብሠራ የሚሻል እንደሆነም ነገሩኝ::

«መልካም ወደ ሐመር ሄጄ ብሠራ ይሻላል ነው የሚሉኝ? ግን ለምን ወደ ሐመር እሄዳለሁ? በዚህ በሙርሲ ሕዝብ መካከል ሆኜ መሥራት እፈልጋለሁ:: ብዙ ጊዜ ስላልኖርን ሕዝቡ እዚህ በደንብ አያውቀንም» ብዬ ተከራከርኳቸው::

እዚህ በሙርሲ ሕዝብ መካከል መቆየታችሁ ባይከፋም ከውጪ ምንም ዓይነት ግንኙነት አይኖራችሁም:: በተለይም ምግብ ሊያቀብላችሁ የሚችል ሰው ሲኖር አይችልም ስለዚህ ልትቆዩ አትችሉም አሉኝ::

በሐመር በበና ሕዝብ መካከል እግዚአብሔር አበርትቶን ስለነበር ወደዚያ ለመሄድ ደስተኛ ነኝ:: ይሁን እንጂ በሙርሲ ሕዝብ መካከል ደግሞ ጥቂት ብንቆይ አይከፋም ነበር::

## ማስታወሻ

1. ዶንና ክርስቲና ግሬይ ያንን አካባቢ ከዓመታት በፊት ጐብኝተው ነበር::

2. የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮን ጣቢያ በነበረበት አጠገብ አነስተኛ ከተማ በነበረበት የመንግሥት ት/ቤት ነበር::

3. ባልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ የተነሣ ሚስዮናውያኑ ዲመካን ለቅቀው በአስቸኳይ የወጡት በ1969 ዓ.ም ነበር::

## *ወደ ምዕራፍ ሃያ መግቢያ*

*አቶ መሐሪና አብረዋቸው የሚሠሩ ወንጌላውያን አዳዲስ ክርስቲያኖችን የሚያበረታቱና የሚመክሯቸው እነርሱ ናቸው:: ለእያንዳንዱ ሰው በቅርቡ ብዙ መንፈሳዊ ለውጥ እንደሚያመጡም ያውቁ ነበር:: ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ደግሞ አነስተኛ ለውጥ ሰብዙ ጊዜ እንደሚሠራጭና መንፈሳዊ ዕድገትን እንደሚያገኙ ይታመን ነበር:: ከአካባቢው ውጪ /ርቀው/ የመጡ እንደመሆናቸው ባህላዊ ስሜታቸውና ልምዳቸው ውስን ነበር:: ባህላዊ አስተያየት ምን እንደሆነ በትክክል አያውቁም::*

*የሰዎች ሕይወት ሲለወጥ ማየት ለወንጌላውያኑ ከፍተኛ ደስታን ይሰጣል:: መንፈሳዊ ውጊያም ባህላዊ በሆነ መንገድ ካልሆነ በስተቀር ፊት ለፊት በመጋፈጥ የሚያሸንፉት እንዳልሆነ ያውቁ ነበር:: የሥራው የበላይ ተመልካቾች ቢሆኑም፣ አንዳንድ ጊዜ ግን የቀጥታ ተሳትፎ ያደርጉ ነበር::*

*በበና ምድር ወንጌላውያኑ የሚፎካከሯቸውና የሚታገሏቸው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የአማራው የመሬት ከበርቴዎች አልነበሩም:: የማንኛውም ፍጥጫ ዋና ክፍል ማመቻመች እንደሆነ ያውቁ ነበር:: መንፈሳዊውን ዕድገት ለማምጣት አስፈላጊውን ጊዜና ቦታ በአስፈላጊው ደረጃ ይመርጡ ነበር:: ያለመደራደር ካሰ ሁከት ይኖራል:: በፍጹም ሥነ ምግባርና በባሕል መካከል ሚዛናዊ የሆነ አስተያየትን ማግኘት ነበረባቸው::*

*አዳዲስ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ሲለወጡ ባህላዊ ለውጥንም ያሳዩ ነበር፤ ለምሳሌ፣ ሞትን መፍራት፣ የማያምኑት በአስደናቂ ሁኔታ ሰሙታን የሚኖራቸው አዘኔታ ካመኑ በኋላ ይለወጥ ነበር:: ለመለወጥ ፍቃደኛ አለመሆናቸው ከፍርሃት የተነሣ ነበር:: የሚያስፈራቸውም ለዘመናት አብሮአቸው የቆየውንና የሚያስታውሱትን ጉጂ ባህል መተው ወይም ማቋረጥ ነበር::*

*ለወንጌላውያንና ለክርስቲያኖች እያንዳንዱ ተግዳሮት ለወንጌል ድልን ሰጥቷቸዋል:: ይህም ማለት እግዚአብሔር ለኃጢአት ይቅርታና ለሕይወት መለወጥ ያለውን ዕቅድ የሚገልጸውን ቃሉን እንዲያሰራጩ ቀላል ሆኖላቸዋል ማለት ነው::*



# በሐመር ውስጥ የነበረው ምላሽ

## ምዕራፍ ሃያ

በሐመር በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑት ሰዎች መካከል አንዱ ጉምዛሮ የሚባለው ወጣት ነው:: በክርስቶስ ካመነ በኋላ የባሕርዩ መለወጥ እየጨመረ መሄዱ በግልጽ ያስታውቅ ነበር:: በዚያ የሚኖር ኅብረተሰብ የዚህ ወጣት መለወጥ የማኅበራዊ ኑሮአችን ፀር ከመሆኑም በላይ ለኅብረተሰባችን መጥፎ ዕድል የሚያመጣ ነው ይሉ ነበር::

አንድ ቀን፣ «አንተ ከእነዚህ ከውጪ ከመጡት ሰዎች ጋር ተዳብለሃል:: ወይ ከእኛ ውጣና ከእነርሱ ጋር ሂድ፣ ወይንም ከእኛው ጋር እኛን መስለህ ከዘር ሐረጋችን ተያይዞ የመጣውን ባህላችንን ጠብቅ:: በሌላ መንገድ የውጪዎቹን ሰዎች ባህል መስለህ እዚህ መኖር አትችልም» ብለው አሰሩት::

ጉምዛሮ መልሶ፣ «ይህ የተወለድኩበት አገሬ ነው:: የትም ቦታ ልሄድ አልችልም:: የእናንተን ያረጀ ባህል መተዌ ምንም መጥፎ ዕድል አያመጣባችሁም:: እኔም በዚህ ኅብረተሰብ መካከል አደገኛ ሰው አይደለሁም:: ስለዚህ እኔን የምታባርሩበት አንዳች ምክንያት የላችሁም» አላቸው::

ባለቤቱም ጠንካራ ክርስቲያን ነበረች:: በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመኗ በፊት በእያንዳንዱ እግሯ ዘጠኝ ጥቅል ብረቶችና በክንዷና በአንገቷም እንዲሁ ብረቶች ነበሯት:: ፀጉሯም ቀይ ጭቃ የተመረገበት ነበር:: ይህቺ ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመነችው ሚስተር ቦንክ በድመካ በነበሩ ጊዜ ነበር:: ያን ጊዜ በክንዶቿ አስራቸው የነበሩትን ብረቶችና በእግሮቿም የታሠሩትን ብረቶች ቆርጠን እንድናወጣላት ጠይቃናለች:: በፀጉሯም የተቀባችውን ቀይ ጭቃ ታጠበች፣ መላ አካላቷንም ታጥባ ንጹሕ ሆነች::

ይህን በማድረጓ ሰዎች በጣም ተቆጡ:: እርሷም፣ «ይህ አሮጌ ባህላችን ሰላምና ደስታ አላመጣልንም:: እነዚህን ባሕላዊ ድርጊቶች በመፈጸማችን ልባችን ዕረፍት አላገኘም:: አባቶቻችን ካስተማሩን ባህል ይልቅ የተሻለ የሕይወት መንገድ አለ» አለቻቸው::

እነዚህ ባልና ሚስት ልጆቻቸውን ድመካ ወደሚገኘው የሚስዮኑ ግቢ ትምህርት ቤት አስገብተዋቸዋል:: ለዚህም የአካባቢው ሕዝብ በጣም ተናደውባቸዋል::

## ማነጣጠር

ጉምዛሮን ከአካባቢው ለማስወጣት የወጣት ጦረኞች ቡድን መጥተው አምባጓሮ በመፍጠር ደበደቡት:: ሁኔታውን ለማስረዳትና ለመማለድ ወደ አካባቢው አለቃ /መሪ/ ሄድኩኝ:: መሪውም አሳቤን በሙሉ ከሰሙ በኋላ ሌሎች ደግሞ የሚሉትን መስማት እንዳለባቸውና ከዚያ በፊት ግን አሳባቸውን እንደማይሰጡኝ ነገሩኝ:: የክስ መጥሪያ የሚጽፍላቸው ጸሐፊ ስለነበራቸው አጽፈው ወደ አካባቢው ሰዎች እንድወስድ ሰጡኝ:: እኔም ወስጄ ስሰጣቸው የጥሪውን ወረቀት ቀድደው በአየር ላይ በተኑት:: ቀርበው መወያየትን እንጂ የጥሪ ወረቀትን አይፈልጉም:: በእነርሱ አስተሳሰብ ሹሙ በአንድ ወገን ቆሞ ብያኔ የመስጠት መብት የለውም ባዮች ናቸው::

ተመልሼም ያደረጉትን ሁሉ ለመንደሩ ሹም ለግራዝማች አድነው ነገርኩኝ:: ምንም የመጨነቅ ስሜት አልታየባቸውም:: ምናልባትም ጥሪውን የጻፉላቸው እኔን ለማስደሰት ብቻ ይመስላል እንጂ ምንም ፋይዳ አላመጡልኝም::

«ረቡዕ ዕለት መጥቼ አነጋግራቸዋለሁ» ብለው ሸኙኝ::

በእርግጥም ረቡዕ ጠዋት ደረሰና መጥተው አብረውአቸው ቡና ከጠጡ በኋላ ሁሉም በርጩማዎቻቸውን አውጥተው በግራር ዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጡ:: ጊዜው ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ቢሆንም፣ ፀሐዩ በጣም ሞቃት ነበር::

ሁሉም ቡናቸውን ፉት እያሉ በሚጫወቱበት ሰዓት የመንደሩ አለቃ ግራዝማች አድነው ጣልቃ በመግባት፣ «ያ ሰው ወደ እኔ መጥቶ ጉምዛሮ መደብደቡን ነገረኝ» ሲሉአቸው በመካከላቸውም ፀጥታ ሰፈነ::

«እንደምታውቁት በባሕላችን አንድ ሰው ያለምክንያት አይደበደብም:: ከደበደቡት ሰዎች ጋርም ጠብ እንደሌለውና በሰላም ለመኖር የሚፈልግ ነው:: ይህ ሰውና እነዚህ ሰዎች ምን እንዳደረጓችሁ ንገሩኝ:: ምናልባት አካባቢያችንን እንዲለቁ እንጠይቃቸዋለን:: ማን ነው ከመካከላችሁ የሚናገር?» ሲሉ ሁሉም ዝም አሉ::



በመጨረሻም አንድ በዕድሜ የገፉ ሰውዬ ትንባሆ በማኘክና ጉሮሮአቸውን በማጥራት ለመናገር ተነሡ::

«ልታነጋግረን በመምጣትህ እናመሰግንሃለን:: በእውነቱ እኛ ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ነን:: በሰላምም ለመኖር እንሻለን:: ነገር ግን አሁን ራሳችንን ነው የተከላከልነው፣ ይህ ሰው ለምን እንደ ተደበደበ አምስት ምክንያቶች ልስጥህ:: በእርግጥ በግሌ በእርሱ ላይ ጥላቻ ባይኖረኝም፣ የምናገረው ግን በእነዚህ በደበደቡት ሰዎች ስም ነው::

*አንደኛ፣* የውጪ አገር ዜጎች መጥተው በድመካ ቤቶችን ገንብተዋል:: እነርሱም ስለ እግዚአብሔር አዲስ ነገር ማስተማር ጀምረዋል:: አኗኗራቸውም በጣም የተለየ ሲሆን፣ ይህ ሰው ደግሞ ትምህርታቸውን ተቀብሎአል:: እንደ እነርሱም መልበስ ጀምሮአል:: የውጪ አገር ዜጎች አሁን የት አሉ? ሁሉም ወደመጡበት ተመልሰው ሄደዋል:: ይህ ሰው ደግሞ የእነርሱ ሆኗል:: ስለዚህ ከእነርሱ ጋር መሄድ አለበት፤ ከእንግዲህ ወዲህ እኛን መስሎ አይኖርም::

*ሁለተኛ፣* ከሰዎች ጋር እንዳንጣላና እንዳንገድላቸውም የእግዚአብሔር መጽሐፍ ያስተምረናል እያለ ይናገራል:: ሰዎችን ካልገደልን ቤታችንን እንዴት መጠበቅ እንችላለን? ቤተሰባችን ሲጠቃ፣ ከብቶቻችንን ሰንዘረፍ፣ አካባቢያችን ሲወረር እንዴት ዝም ማለት እንችላለን?

«ይህ ሰው ባሕላችንን የሚያውቅ ሰው ነው:: እኛ የተወሰኑ እባቦችን እንኳን እንደማንገድል ያውቃል:: እርሱ ግን መገደል የሌለባቸውን እባቦች በዱላው እየገደለ መጥፎ ነገር እንዲመጣብን ይፈልጋል::

*«ሦስተኛ፣* ለጠንቋዮች ለየት ያለ ቦታ እንደተሰጣቸውም ያውቃል:: ጠንቋዮች ደግሞ መልካሙንና ክፉውን ቀን ለይተው የሚያሳውቁንና በየትኛው ቀን ጠላቶቻችንን ብናጠቃ እንደምናሸንፋቸውም የሚነግሩን ናቸው:: የተወሰነ የመሬት ክልል የእነርሱ እንደሆነም እያወቀ፣ ግን እርሱ ምን አደረገ መሰለህ? የጠንቋዮቹን መሬት ሄዶ በድፍረት እያረሰ በቆሎ በመዝራት፣ ሣር በማጨድና ዛፍ በመቁረጥ ከፍተኛ በደል ፈጽሞብናል::

«በባህሉ መሠረት ጠንቋዩ እህል መዝራት የሚገባን መቼ እንደሆነ እስኪነግረን እንደምንጠብቅ ያውቃል:: እርሱ ግን አይጠይቅም፣

እኛንም አይጠብቅም:: ነገር ግን በራሱ ፈቃድ ሄዶ በማረስ የመጀመሪያው ዝናብ እንደዘነበ ዘርቷል::

«የእርሱ ሰብል ከእኛው ቀድሞ ይደርሳል፣ በባሕላችን እሸት ሲደርስ መጀመሪያ ለጠንቋዩ እንደምንሰጥና ትክክለኛውን የዝናብ ወቅት ከጥበቡ እንደሚነግረን ያውቃል:: ይህ ሰው ግን ይህን አያደርግም:: እንዲያውም ጠንቋዮች ዝናብ ማምጣት አይችሉም ማለት ጀምሯል:: የመጀመሪያውን በቆሎ ለጠንቋዩ ከማቅረብ ይልቅ ለራሱ ቆርጦ በራሱ እሳት ጠብሶ መብላት ጀምሯል::

«አራተኛ፣ ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ባሕላችንን አይከተልም:: ይህን አለመከተል ደግሞ በኅብረተሰባችን ላይ መጥፎ ዕድል የሚያመጣ ነው::

«አምስተኛውን ምክንያት ደግሞ ልጨምር:: በሙታን መቃብር ላይ ማር ማፍሰስ ባሕላችን ነው:: ይህ ሰው ግን የሞቱት ሰዎች ሊባርኩን ወይም ሊረግሙን የሚያስችል ሥልጣን የላቸውም:: በመቃብራቸው ላይ እያፈሰስን የምንመገበውን ማር የምናባክንበት ምክንያት የለም ይላል:: ይህ ደግሞ ባሕላችንን የሚጻረርና ጠንቋዮቹም በዚህ ድርጊቱ ከተቆጡ በእኛ ላይ መጥፎ ዕድል ሊያመጡብን ይችላሉ» ብለው በስፋት ካስረዱ በኋላ ተቀመጡ::

የመንደሩ አለቃም መልስ ከመስጠቱ በፊት ማሰብ ጀመረ፤ በሁሉም መካከል ፀጥታ ሰፈነ::

«እነዚህ የእናንተ ባሕሎች ናቸው:: ልትታዘዟቸውም ነጻነት አላችሁ:: ሕጉን ግን ለመግታት ነጻነት የላችሁም:: እነዚህ ባሕሎቻችንን ማንም ሰው እንዲቀበል የሚያስገድድ መመሪያ ከአዲስ አበባ ከመንግሥት ተቀብላችኋል? የምትወስዱት ወይም የወሰዳችሁት እርምጃ ከመንግሥት ሕግና መመሪያ ውጪ ከሆነ ሁላችሁም ታሥራችሁ ትቀጣላችሁ::» ሰዎቹም ረዘም ያለ ጊዜ ወስደው በጉዳዩ ላይ መከሩበት::

«አንዳንዶቹ በእርግጥ የተፈጸመ ነገር የለም» አሉ::

አንዳንዶቹ ደግሞ፣ «አሁን ካልሆነም የሚከሠት ነገር ሊኖር ይችላል» በማለት ተከራከሩ::



# በድርድር የተገኘ ሰላም

ከረዥርም ውይይት በኋላም ለመደራደር ወሰኑ:: ወደ እሥር ቤት ከመግባት ይልቅ ከጠላት ጋር መስማማት ይመረጣልና፣ «ወጣቶቻችን ከመመሪያችን ውጪ እየተጓዙ ናቸው» በማለት ሽማግሌዎች ተናገሩ:: «የደረሰውም ጥቃት ሳይሆን አለመረዳትና አለመግባባት ነው:: ወጣቶቹም ሊጠይቁት ሲሄዱ በጣም የተቆጣው እርሱ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ጠብ የጀመረውም እርሱ ነው» በማለት ተናገሩ::

ግራዝማች አድነውም ወደ እኔ ዞረው፣ «አሁን ምን እንዲያደርጉ ትፈልጋላችሁ?» አሉኝ::

በምን ጉዳይ ላይ መደራደር እንደሚፈልጉ አንወቅና ወደ መስማማት ልንደርስና በሰላምም አብረን ለመኖር ዝግጁዎች እንሆናለን::

በመጀመሪያ ጉምዛሮ አስቀድሞ የተቆጣ መሆኑን ይመን:: ያ ከሆነ ደግሞ ያጠቁት ሰዎች ከእንግዲህ ፊት አይነሱትም:: ለደረሰውም ችግር እርሱም መወቀስ ይገባዋል::

ሽማግሌዎቹም ደብዳቢዎቹ የዘረፉትን አምስት ፍየሎች መመለስ አለባቸው:: አንድ ወይም ሁለት ፍየሎችም ተበልተው ይሆናል:: በአምባጓሮው ወቅት የቀደዱበት ልብሶቹን ለመተካት መስማማት አለባቸው:: እርሱ ግን የባሕልና የልምድ ተገዥ መሆን ይጠበቅበታል አሉ::

«በዚህ ሁሉ ባይስማማም እንኳን፣ የአንድ ሰው ተነጥሎ ከእኛ ባሕል ውጪ መሆኑ ብዙም መጥፎ ዕድል ሊያመጣብን አይችልም::»

ወንጌላውያን በዚህ ብቻ መለየት ካለባቸው የእያንዳንዱ ግጭቶች ተከታታይ ውጤት የጠረኞችን ዓላማ የሚገታ ሊሆን ስለሚችል የወንጌልን መልእክት በግልጽ ለማስተላለፍ አመቺ ይሆናል ብዬ ገመትኩኝ::

አሮጌው ባሕል መተውና መናቅ ያለበት በጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ የሚወሰድ እርምጃ መሆን የለበትም:: አንዳንድ አስተዋይ የሆኑ የኅብረተሰቡ አካሎች ክርስቲያን ባይሆኑም ጎጂ ባሕልን ለማስቀረት መጣር ይገባቸዋል::

## አካለ መጠን መድረስን ማረጋገጥ

ወዳጄ ጋሪሾ ከጨንቻ ወደ በና ምድር በተመለሰ ጊዜ ከጋሞ አካባቢ ሚስት ይዞ መጣ:: ያገባትም በጎሳው ባሕል መሠረት አልነበረም:: በላሞች ጀርባ እየዘለሉ የማጋባት ባሕል አልጠፋም ነበር:: በአካባቢው ኅብረተሰብ ዓይን ጋብቻው የተሟላ አይደለምና ዋጋ አይኖረውም::

የጎሳ ሰዎችም ጋሪሾ አስፈላጊውን የበናን የጋብቻ ባህል እንዲያሟላ ለማስገደድ ይሞክሩ ነበር::

በላሞች ጀርባ የመዝለል ባሕል የኅብረተሰቡን ጀግንነት ለመጠበቅ ነው ተብሎ ይታመናል:: ይህም ማለት አንድ ወጣት እነዚህን ሥርዓቶች ካላሟላ ልጅነቱን አልጨረሰም፣ ለማግባትም የተገባ ሊሆን አይችልም:: ሥርዓቱም የአስፈላጊ ነገር ችሎታ የመለካት ባሕርይን ያሳያል:: በፈተናው አለማለፍ የሚያሳፍር አይሆንም:: ዋናው ነገር የቤተሰቡ መንፈስ ለጋብቻ ጊዜው አመቺ አይደለም ብሎ መናገሩን እንደሆነ ያምናሉ::

ለሥነ ሥርዓቱም ስንት ከብቶች እንደሚጠቀሙ የሚወስኑት የኅብረተሰቡ ልዩ ሹመት ያላቸው ሽማግሌዎች ናቸው:: እንስሳቱም በየጎናቸው ሆነው በመሥመር እንዲቆሙ ይደረጋል:: የሁሉም ጀርባ ተስተካክሎ በተርታ ይቆማሉ:: ወጣቱም ከአንዱ ከብት ወደ ሌላው ከብት ጀርባ እየዘለለ ያልፋል:: አንድ እንስሳ ከተንቀሳቀሰበት መሥመሩን አዛብቶበት በዘዴ ለማለፍ ካልቻለ መጥፎ ምልክት ስለሆነ ጋብቻው መታለፍ ይኖርበታል::

ጋሪሾ ግን አግብቶ ነው የመጣው:: ጋብቻውም ዕድለ ቢስ እንዳያደርገው በከብቶች ጀርባ የመዝለሉ ነገር አልዋጥ ብሎታል:: በአንድ በኩል ደግሞ የአካባቢው ሽማግሌዎች የጋሪሾ ልጅ እንደማይገድል የቤተሰቡ መንፈስ ምልክት አልሰጠም ከጠንቋዩ አላገኙም ወይንም መጥፎ ዕድል የሚያመጣባቸውን ነገር አላዩም:: ይሁን እንጂ ከጋሪሾ ሚስቱን ወስደው ለአንድ ዓመት ሙሉ ሸሽገው አቆይተዋታል::

ከብቶቹንም አርደው ሲበሉ እርሱ ግን እጁን አልሰጣቸውም:: በመጨረሻም የወሰዱበትን ሁሉ ለመመለስ ተስማሙ:: ሚስቱም ለጋሪሾ ተመለሰችለት:: በኅብረተሰቡም መካከል በሰላም እንዲኖር ተፈቀደለት:: የተሟላ ሥነ ሥርዓት (በባሕላቸው መሠረት) ባይከናወንም ጋብቻቸው መጥፎ ዕድል እንደማያመጣባቸው ታምኖበት ጸደቀላቸው::



*ይህ ምዕራፍ በ1966 ዓ.ም የተጀመረውን አብዮታዊ ንቅናቄ የኋላ ታሪኩን ለማሳየት የተጨመረ ሲሆን፣ ለውጡ በጣም ጥልቅ ቢሆንም የአቶ መሐሪንና የጓደኞቻቸውን መንፈሳዊ አገልግሎት አላስተጓጎለባቸውም::*
*ብራዬን ፋርገር*

# ሥር ነቀል ለውጥ

## ምዕራፍ ሃያ አንድ

ዘመናዊው የአማራ ገዢ መደብ (መንግሥት) የአገዛዝ ዘመኑ በወርሃ መስከረም 1967 ዓ.ም ጠዋት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከቤተ መንግሥታቸው ወደ እሥር ቤት ሲወሰዱ አከተመ:: ለውጡ የተጀመረው ንጉሡ በዙፋናቸው ላይ እንደ ነበሩ ከአያሌ ወራት አስቀድሞ ቢሆንም፣ የንጉሡ ከሥልጣናቸው መውረድ ለአገሬው ሕዝብ በይፋ ሲነገር እያንዳንዱ ዜጋ የተጀመረው ለውጥ ወደ ኋላ እንደማይመለስ ያውቅ ነበር:: ነገሮች ዳግም ላይመለሱ ተለወጡ:: ጉዞው ጠመዝማዛ ሳይሆን በቀጥታ ወደ ግራ እንደ መታጠፍ ዓይነት ነበር::

ሥር ነቀል ለውጡ ከመነሻው ለእንደ አቶ መሐሪ ዓይነት ሰዎች ጥሩ ይመስል ነበር:: አብዛኛው የአገሬውም ሕዝብ ሁለት ክንዶቹን ዘርግቶ ነበር የተቀበለው:: በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከዚህ ቀደም ሕዝቡ ያላየውን ነጻነት እንደሚያጎናጽፈውም ቃል ተገባለት:: ሕዝቡ ግን የንጉሡን ከሥልጣን መውረድ በጭብጨባ አልተቀበለውም:: የወታደራዊውንም አገዛዝ እንዲሁ በደስታ አልተቀበለውም:: ነገር ግን የሕዝቡ ደስታ ሊፈጸም የሚችልበትን እየጠበቀውም ያለው ነገር ለዘመናት ሲረግጠው የኖረው የአማራው የገዢ መደብ ከሥሩ ተመንግሎ ሲወድቅ ማየት ነበር::

በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዓመት ለውጡ እንደ ደራሽ ወንዝ በመላ አገሪቱ ተሰራጨ:: የመጀመሪያዎቹ ተጠቂዎችም የአማራው የመሬት ከበርቴዎች ሲሆኑ፣ በብዙ ምክንያቶች ፊት ለፊት ለመታየት ያልቻሉ የመሬት ከበርቴዎች ሌሎችን እየሾሙ ቀረጥ ለመሰብሰብ ይሞክሩ ነበር:: በኋላም ጥቃቱ ለአገሪቱ ዕድገት መሰናክል ወደሆኑት ዞረ:: ጠንቋዮችና ተከታዮቻቸው ሁሉ ሳይቀሩ የቅጣቱ ሰለባ ሆኑ:: ይህ

እንቅስቃሴ መልካም መስሎአቸው ክርስቲያኖቹም በእንደዚያ ዓይነት እርምጃ ደስተኞች ሆኑ:: ምክንያቱም እስከዚያ ነጥብ ድረስ የለውጡ ደጋፊዎች ሲሆኑ፣ የለውጡ አራማጆችም በክርስቲያኖቹ ላይ ያደረሱት ጥቃት አልነበረም::

በ1968 ዓ.ም የለውጡ ፍልስፍና ሲታወጅ በቀጥታ ሃይማኖትን የሚጻረር ሆነ:: ይህም የሆነው ለውጡ የአፍሪካ ኅብረተሰብአዊነት ከሚለው ደረጃ እየተሸጋገረ የማኦና የማርክሲዝምን ፍልስፍና የሚያራምድ ነው ተባለ:: ተራው ሕዝብ የፍልስፍናውን መርህ አልተረዳም ነበር:: በ1967 እና በ1968 ዓ.ም ይወራ የነበረው ሁሉ ፀረ ሃይማኖት ቢሆንም፣ አብዛኛው ሕዝብ አልገባውም ነበር::

ፍልስፍናው ሃይማኖትን የሚያጠቃና በቁሳዊ ነገሮች ላይ ትኩረት የሚሰጥ ነበር:: ያ በውሸት ለማሳመን የሚደረገው ቅስቀሳ ከተራው ሕዝብ ራስ ላይ የወጣ ሲሆን፣ ማንም ያስተዋለ ግን አልነበረም:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ሃይማኖት ከጽንሰ አሳብ የበለጠ የኅብረተሰብ አካል ነው ማለት ይቻላል:: በመጨረሻም የለውጡ አራማጆች የቤተ ክርስቲያንን እንቅስቃሴ በመፍራት ማኅበራዊ ጥቆማ እየተካሄደ ታዋቂ የሃይማኖት መሪዎችን ሰብስበው ማሠር ጀመሩ:: በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ላይም አነጣጠሩ፣ ምክንያቱም ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ከእስልምና ሃይማኖት ይልቅ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጥቂቶች ስለነበሩ ይመስላል:: የፀረ ሃይማኖትን እንቅስቃሴ በተግባር ላይ የሚያውሉት የአካባቢው ተመራጮችና ባለሥልጣኖች ነበሩ:: የፈለጉትን ዓይነት እርምጃ ቢወስዱ ክርስቲያኖቹ ለመከላከል አቅምና ለሚ አልነበራቸውም:: ከማዕከላዊው መንግሥት ይተላለፍ የነበረውን መመሪያ በዝምታ መቀበል እንጂ አቤቱታ ማቅረብ ውጤት አልነበረውም::

ቀጥሎም መሬትን ከግል ንብረትነት ወደ መንግሥት ይዞታነት የሚያሸጋግር አዋጅ ወጣ:: ይህም የወንጌላውያንን ሥራ የሚያስተጓጉል ሆነ፣ ምክንያቱም በብዙ አካባቢዎች ሹሞች የነበሩት ነዋሪውን ሕዝብ መሬት የራስህ አይደለም በማለት የተሳሳተ መረጃ ስለሚያሰራጩ ነበር:: ከቤታቸውና ከመንደራቸው ርቀው የሚያገለግሉ ወንጌላውያን ምን ያድርጉ? ሁለት ምርጫ ብቻ ነበራቸው:- ይኸውም ለተወሰነ ጊዜ ሥራቸውን አቁመው በመሬታቸው ላይ መቆየት፣ ወይም መሬቱን ራሳቸው ትተው ቤተሰቦቻቸውን በመሬቱ ማኖር



ሲሆን፣ መሬቱን ማስረከብ ግን አማራጭ አይሆንም:: አንዳንድ ወንጌላውያን ለተወሰነ ጊዜ ሥራቸውን በማቆም በመሬታቸው ላይ ቆይተውም ነበር::

የለውጡ አራማጆች በወቅቱ የሚያደርጉት ቅስቀሳም አጠራጣሪ አይታ ነበረው:: ወንጌላውያንን በተመለከተ ግን ከማንም ጋር መታገልና መርከክር የሚያዋጣ አልነበረም:: ከለውጡ ወገኖች በኩል አንድ ዕድገትን ለማግኘት ሌላውን አሳልፎ መስጠት የተለመደ በመሆኑ፣ አንድ ሰው የቅርብ ጓደኛውን ካጋለጠ የበለጠ ዕድገትን ያገኝ ነበር:: ወንጌላውያን ደግሞ የመምራት ብቃት ስለነበራቸውና የሚሰብኩት መልእክትና በማኅበራዊ ሕይወታቸው ተቀባይነት ስለነበራቸው የመጀመሪያዎቹ የካድሬዎቹ ዒላማዎች ነበሩ::

በመጨረሻም የፀረ ሃይማኖት ቅስቀሳው ሁሉም ሰው እስኪገረም ድረስ በወላይታ አጠቃላይ ቤተ ክርስቲያናት እንዲዘጉ አደረገ:: በወላይታ በዚያን ጊዜ 735 ቤተ ክርስቲያናት በዚያ ስደት ውስጥ በእምነታቸው ጸንተው በመቆም የሚከራባቸው መልካም ምሳሌዎች ለመሆን ችለዋል:: ከመንፈሳዊ ዕይታና ከአቅም አንጻር ተቃዋሚዎች ሁሉንም ቤተ ክርስቲያኖችን ሊዘጉ የሚችሉ አይመስልም ነበር:: ነገር ግን የወጠኑት ዕቅዳቸው ተሳካና ቤተ ክርስቲያናት ተዘጉ:: ብዙ የጸሎት ቤቶችም ፈረሱ፣ የክርስቲያኖች ሠርግና ቀብር የሕግ ከለላ አጥቶ ተወገዘ:: በክርስቲያኖች ቀብር ላይ የተገኙትም ለእሥር የተዳረጉበት ጊዜ ነበር:: ሁሉም ቤተ ክርስቲያናት በተዘጉ ጊዜ በተለያዩ ስፍራዎች ለአገልግሎት የተበተኑት ወንጌላውያን ምንም ገንዘብ ማግኛ መንገድ አልነበራቸውም:: የወላይታ ቤተ ክርስቲያናት ኅብረትም ገንዘብ አግኝቶ ለመርዳት ያልቻለበት ወቅት ነበር:: መሪዎችም ባዶ እጃቸውን ነበሩ:: በሌላው የአገሪቱ ክልሎች የሚገኙ የወላይታ ወንጌላውያንም እየለበኩ ደመወዛቸውን ለማግኘት አልቻሉም ነበር::

በመላው አገሪቱ ውስጥ የሃይማኖት ነጻነት ሲነፈግ ሌላም ነጻነት አልነበረም:: ሕዝቡ በመገናኛ ብዙሃን ብሶቱን ለመግለጽ አልቻለም ነበር:: ይሁን እንጂ በግድየለሽነት ተቃውሞውን ሳያሰማ አልቀረም:: መምህራኖች በየሰዓታቸውና በየክፍላቸው ቢገኙም፣ ተማሪዎች ምንም አይማሩም:: ገበሬዎች ለቤተሰቦቻቸው የሚበቃውን እህል ብቻ ለማምረት ይቻሉ እንጂ ከገበያ የሚፈልጉትን ለመግዛት የሚያስችል የገንዘብ ምንጭ አልነበራቸውም:: የማኅበራዊው ምጣኔ ሥርዓቱ

ተንኮታኩቶ ወደቀ:: ይህች አገር የሶቪዬት ኅብረትን መርሆ መከተል እንጂ የነበራትን የኢኮኖሚ ምንጭ በአግባቡ ስመጠቀም አልቻለችም ነበር::

በአዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ ውስጥ ክልከላዎችን በመጣስ የሚያስከትለውን ውጤት በደስታ ለመቀበል የተዘጋጁ ሰዎች አይታጡም ነበር:: በ1972 ዓ.ም አካባቢ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያኖችን መክፈት ጀመሩ፣ መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውንም ከየደበቁበት አወጡ፣ መዘመርና መጸለይም ጀመሩ:: የፀረ ሃይማኖት መመሪያዎች ቀስ በቀስ ላላ ማለት ጀመሩ፣ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዛመተ የወንጌል ሥራው እንቅስቃሴም ወደ ቀድሞ ቦታው ለመመለስ በቃ:: የማዕከላዊው መንግሥት ባለሥልጣኖችም የፍልስፍናቸውን ከንቱነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተረዱት መጡ::

ለሕዝቡ ተነፍጎ የነበረው ነጻነት በመጠኑም ቢሆን መለቀቅ ተጀመረ:: የግል የንግድ ድርጅቶች እንዲከፈቱ መበረታታት ጀመሩ:: የሃይማኖትና የመሰብሰብ ነጻነት ተፈቀደ:: ነገር ግን ለመንግሥቱ ሥልጣን ጊዜው አለፈበት::

በግንቦት 1983 ዓ.ም ያ አገዛዝ ተወግዶ አዲስ ዘመን ታየ:: ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም አስቀድመው ያላገኙትን ነጻነት በደስታ መቋደስ ጀመሩ::



# የምዕራፍ ሃያ ሁለት መግቢያ

*መስከረም 1967 ዓ.ም ለእንደ አቶ መሐሪ ዓይነቶቹ ወንጌላውያን አዲስ የገሃድ ዓለምን ወይም የቁስ አካል ምርምርን ያንጸባረቀ ነበር:: ይሄ ፍልስፍና ምን እንደሆነ የተረዱት ነገር አልነበረም:: ብዙ የለውጡ አራማጆች የነበሩት ራሳቸው እንኳን ስለ አዲሱ ፍልስፍና ጠለቅ ብለው የሚያውቁት ነገር አልነበራቸውም:: ወዲያው ግን ሁሉም የተረዳው ነገር ቢኖር ፍልስፍናው ሌላው አሰፈሪ መንገድ መሆኑን ነው:: አዲሱ ጠላት የበለጠ ጨካኝ፣ ጮሌና ቆራጥም የሃይማኖት ጠላትም ነበር:: ዓላማውም ቤተ ክርስቲያናትን መዝጋት፣ ወንጌላውያንን ከቦታ ወደ ቦታ እንዳይዘዋወሩ የሚያደናቅፍ ነበር::*

*ወንጌላውያኑ የፍልስፍናውን ውስብስብነትም ሆነ በእግዚአብሔር መኖር ያለማመን ቅስቀሳ ፈጥነው አልተገነዘቡትም ነበር:: አብዛኛዎቹ ወንጌላውያን የመጣው ማዕበል እስኪያልፍ የተሻለው አማራጭ ወደየቤታቸው ተመልሰው ማሳለፍ እንደሆነ ወሰኑ:: የመጣው ይምጣ ብለው በነበሩበት ቦታ ለመቆየት የወሰኑት ደግሞ ሁለት ነገሮችን ለማድረግ ችለዋል:: በመደራደር ባሉበት ቆይተው መልካሙን ዜና (ወንጌልን) ለመስበክ በተቻላቸው መጠን ረዘም ላለ ጊዜ ቆይተው ወንጌልን ለመስበክ ነበር:: ሁለቱን ወይንም አንዱን ዘዴ ተጠቅመው ለስኬታማ ውጤት ለመብቃት ደግሞ በተለያዩ ነገሮች መተማመን ነበረባቸው:: ከ1966 ዓ.ም እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የተጠበቁ ነገሮች የታዩበት ዓመታት አልነበሩም:: በኃይል መተማመን ብቻ የታየበት ነበር::*

*እውነት ለመናገር ሁሉ ነገር እንደ አቶ መሐሪ ዓይነቶቹ ወንጌላውያን የወንጌልን ጠንካራ መሠረት በየቦታው ለመጣል ችለዋል::*

*እነዚያ ወንጌላውያን በግንቦት 1983 ዓ.ም ታላቅ ለውጥ መጥቶ ወታደራዊውን አገዛዝ እስኪያስወግድ ድረስ ሥራቸውን በትጋት ተወጥተዋል:: ወደ ኋላቸውም ተመልሰው ምን ትምህርት እንደ ተማሩ ያስተውሉም ነበር::*

*በአብዮታዊው ለውጥ ወቅት ጌታ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አሟልቶ እየሰጣቸው ያሳለፉ መሆናቸውን ደጋግመው አረጋግጠዋል:: በእርግጥ የደረሰባቸው ስደትና ተስፋ ማጣት የሚረሳ አልነበረም::*

# አዲስ ዘመን

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

በእርግጥ የውጪ አገር ሚስዮናውያን ድመካን[1] ትተው ወጡ ማለት እኛም ለቅቀን ወጣን ማለት አይደለም። በመጀመሪያ ጌታ እኔን ለወንጌላዊነት ሲጠራኝ በጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገር ምንም የውጪ አገር ሚስዮናውያን አልነበሩም። በ1970 ዓ.ም የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናውያን ጋሞ ጎፋን ለቅቀው ሲወጡ ብዙ የተለያዩ ነገሮች ቢኖሩም፣ ሥራው ግን ቀጠለ እንጂ አልቆመም።

ሚስተር ሙሪ ኡሬና ባለቤታቸው ሄደው ብዙ ሳይቆዩ ዳግመኛ ታመምኩኝና የፖሊስ መኪና አግኝቼ ከድመካ ወደ ጂንካ ለመግባት ቻልኩኝ። ከጂንካ ወደ ሶዶ በአይሮፕላን እንድሄድ ገንዘብ ተሰጥቶኝ የነበረ ቢሆንም፣ የአይሮፕላኑ መቀመጫዎች ተይበዋል ስለተባልኩ ለመጠቀም አልቻልኩኝም። ስለዚህ አራት ቀን ሙሉ በአሪ በኩል በእግር በመጓዝ ወደ ጎፋ በመድረስ በቅሎ ለመከራየት ቻልኩኝ። ከዚያም ወደ ትውልድ ቦታዬ ቁጫ ተጉዤ በመጨረሻም ወደ ሶዶ ደረስኩኝ። ወደ ሶዶ በደረስኩኝ ጊዜ በሆስፒታሉ ውስጥ ሚስዮናዊ ዶ/ር ነበሩና አስፈላጊውን ምርመራ ካደረጉልኝ በኋላ የታዘዘልኝን መድኃኒት ገዛሁኝ።

አሁንም የወላይታ ሽማግሌዎች መማክርት ቦርድ ወደ ትውልድ ቦታዬ ሄጄ ዕረፍት እንዳደርግ (ጡረታ እንድወጣ) ትእዛዝ ሰጡኝ። «አሁንስ እያረጀህ ነው። ለብዙ ጊዜም በተደጋጋሚ ስትታመም ቆይተሃል። አሁን የጡረታ መውጫህ ነው። ወደ ደቡባዊ ጋሞ ጎፋም ሌሎች ወጣቶችን እንልካለን» ብለው ነገሩኝ።

«ጌታ እንድሄድ አዝዞኛል፣ እንድመለስ ግን ገና አልነገረኝም። ስለዚህ እንዴት ወደ ትውልድ አገሬ ሄጄ ጡረታ እወጣለሁ?» አልኳቸው። በኋላም ወደ ደቡባዊ ጋሞ ጎፋ እንድመለስ ፈቀዱልኝ። ባለቤቴና ልጆቼ ለተወሰኑ ወራቶች እዚያው በወላይታ እንዲቆዩ ወሰንን። በአብዮታዊው ለውጥ በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ብዙ ነገሮች በመለወጣቸው ምን እንደምንጠብቅ አናውቅም ነበር። በቁጫ የነበረንን አነስተኛ የእርሻ መሬታችንን በእኛው ይዞታ ሥር እንዳለ ቢቀጥል አስፈላጊ እንደሆነ አመንን።



# አዲስ ዓይነት ምርመራ

ስድስት ሆነን በአንድነት እንሄድ ነበር። ወደ መጀመሪያው ትልቁ ከተማ እንደ ደረስን ለጥያቄ ብለው አቆዩን። ዘጠኝ ቀን ሙሉ እዚያ ሰነበትን። ወንጌልን መስበክ ከጀመርኩኝ ወዲህ ለጥያቄ እየተባልኩ ስቀርብ ለእኔ አሥራ ሁለተኛ ጊዜዬ ነበር። በዘጠነኛው ቀን ማምሻው ላይ ከመካከላችን አንዱ፣ «በጉዞአችን ጅምር ላይ እንዲህ ዓይነት ነገር ካጋጠመን መጨረሻችንስ ምን ይሆን?» ሲል ሁሉም ወደ ወላይታ ለመመለስ ወሰኑ። ከዚያ በኋላ እኔ ወደ ሁለተኛው ትልቁ ከተማ የሚወስደኝን መኪና አገኘሁ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ስምንት ቀን ሙሉ ተጉዤ ወደ ድመካ ደረስኩኝ። ድመካ እንደ ደረስኩኝ ብዙ ነገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተለውጠው አገኘሁኝ። ሥራችን ሁሉ አንድ በአንድ እየተመረመረ ቆይቷል።

እኔ ድመካ ገብቼ ብዙም ሳልቆይ ሌሎች ሁለት ወንጌላውያን በአውራጃው እየተዘዋወሩ ይሠሩ የነበሩት የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለመግዛት መጥተው አገኘሁአቸውና በሕዳር ወር ውስጥ ሠላሳ ሰዎች እንዳጠመቁ በነገሩኝ ጊዜ በጣም ደስ አለኝ።[2] በተጨማሪም ከበና ጎሳዎች መካከል ደባቆ የሚባለው ሰው ለመጠመቅ እንደተዘጋጀም ነገሩኝ። በአሪ ጎሳ መካከልም ሃያ ሰዎች በተጠመቁበት የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ላይ መገኘታቸውንም ሰማሁ። በሌላው ወረዳ ውስጥ ደግሞ ተከፍቶ የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት እንደ ተዘጋና ምእመናኑም በየቤታቸው ሆነው መጸለይ መጀመራቸውን አስረዱኝ።

አሁን የት እንደሚሄዱ ጠየቅኳቸው።

እነርሱም፣ በቆላማው ምድር በስተደቡብ የሚገኙትን ምእመናን ለመጎብኘት እንደሚሄዱም ሲነግሩኝ፣ ሁላችንም በኅብረት ከጸለይን በኋላ ሁለቱም መንገዳቸው ቀጠሉ።

ከሄዱበትም ወዲያው አልተመለሱም፣ ነገር ግን የአዲሱ መንግሥት አስተዳደር ሁላችንንም ለማየት እንደሚፈልግ ገልጾ እንድንቀርብ መልእክት ላኩብን።

ጊዜ ሳያጠፉም አስተዳዳሪው፣ «ይሄ የትውልድ አገራችሁ ነው? ካልሆነ ደግሞ፣ በዚህ አካባቢ ምን ትሠራላችሁ?» ብለው ጠየቁን።

እኛም ወንጌላውያን መሆናችንን ከገለጽንላቸው በኋላ ዋናው ዓላማችንም ወንጌልን ለመስማት ለሚፈልጉት ሁሉም አካባቢ እየተዘዋወርን መስበክ ነው አልናቸው፡፡

«መልካም ነው፣ ጥሩ ነው፣ ደመወዛችሁንስ ከማን ነው የምታገኙት?» አሉና ለማወቅ ጓግተው ጠየቁን፡፡

«እኛ ሁላችንም በወላይታ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን[3] አባሎች ነን፡፡ ደመወዛችንንም ከቤተ ክርስቲያን እንቀበላለን» አልናቸው፡፡

«ደህና፡፡ ስመሆኑ እዚህ ለምን ያህል ጊዜ ቆይታችኋል?» ብለው ጠየቁን፡፡

እኔም መልሼ፣ «እኔ እዚህ ከመጣሁ አራት ዓመት ሆኖኛል፡፡ ሚስተር ቦንክ በድመካ ቤቶችን ለመሥራት መጥተው ከተመለሱ በኋላ ነበር የመጣሁት፡፡ ሌሎቹ የመጡት ግን በቅርቡ ነው» ብዬ መለስኩኝ፡፡

«አንተ የሚስዮኑ ተወካይ ነህ? እዚህ ንብረቶቻቸውን እንድትጠብቅላቸው ልከውሃል?» አሉኝ፡፡

እኔም፣ «በእርግጥ ሚስዮናውያኑ ወዳጆቼ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከሚስዮኑ ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም» አልኳቸው፡፡

«እሺ፣ ገንዘባቸውንና ምግባቸውን እየተሸከሙ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ከሚዘዋወሩት አንዱ ነህ?» አሉና ጠየቁኝ፡፡

እንደገመትኩት ከሆነ እኚህ ሰው ከጓደኞቼ ከአንዱ ጋር በቅርቡ ወደ ሶዶ በመሄድ የወንጌላውያንን ደመወዝ ስላመጣው ሰው እያሰቡ ነበር፡፡ «እኔ ለሚስዮናውኑ ገንዘብ ተሸክሜላቸውም አላውቅም» ብዬ መሰስኩላቸው፡፡ በመልሶቼም የረኩ መሰሉ፡፡

በመጨረሻም የመሬት ግብር እንደምንከፍል ወይም እንደማንከፍል ወይም አነስተኛ መሬት እዚህም እዚያም በመዘዋወር እያረስን ያለግብር እንደምንጠቀም ለማወቅ ጓግተው ጠየቁን፡፡ እኛም እንደ ማንኛውም የአገሬው ተወላጅ ገበሬ ለምናርሰው መሬት ግብር እንደምንከፍል አረጋገጥንላቸው፡፡ እንግዲያውስ ወደየቤታችሁ ተመለሱ፤ አስፈላጊ ከሆነም ሌላ ጊዜ እናነጋግራችኋለሁ ብለው አሰናበቱን፡፡



## ከለውጡ አራማጅ ባለሥልጣኖች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ከጥቂት ቀናት በኋላ አስተዳዳሪው ይፋዊ ያልሆነ ጉብኝት ለማድረግ እንዲችሉና እንኳን ደህና መጡ ለማለት ጥሪ አደረግኩላቸው፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ነገሮች በመልካም ሁኔታ ይከናወኑ ነበር፡፡ በኋላ ግን ወደ ክርክር ውስጥ ገባን፡፡ እንደ እናንተ ዓይነት ሰዎች የኅብረተሰቡ ሸክሞችና አስጊዎች ናቸው ማለት ጀመሩ፡፡ የምናስተምረው የእግዚአብሔር ቃል የኅብረተሰቡን ማኅበራዊና የምጣኔ ሀብት ዕድገት የሚገታ እንደሆነም ነገሩን፡፡ እውነት እንነጋገር ካልን ክሱ የሰበብ ፍለጋ ነው፤ ስለ ለውጡ ከማንም ቀድመን የሚገባውን ተሳትፎ የምናደርግ እኛ ነበርን፡፡

ነገር ግን አስተዳዳሪው በአካባቢው ስለሠራነው ት/ቤቶችና ክሊኒኮች የሚነገረውን ታሪክ ምንም ሊሰሙ አልፈለጉም፡፡ ወደ እርሳቸው መጥቼ ስለጎበኘሁአቸው ካመሰገኑኝ በኋላ ብዙ ሥራ አለብኝ ብለው አሰናበቱኝ፡፡

በማግሥቱ ደግሞ ለሌላ ስብሰባ ተጠራን፤ በዚህን ጊዜ አስተዳዳሪው ከሌሎች ሰዎች ጋር ነበሩ፡፡

«እሺ እናንተ የክርስቶስ አማኞች ናችሁ አይደለም? ሁላችሁም በአካባቢው ችግር የምትፈጥሩ መሆናችሁን ሰምተናል፣ በየሄዳችሁበት ሁሉ ችግር ትፈጥራላችሁ» አሉን፡፡ ከመካከላቸውም አንዱ ወጣት ተነሥቶ እኛን በቅርብ እንደሚከታተለንና በሐሰት የችግር መንሥኤዎች መሆናችንን ለባለሥልጣኖቹ አስረዳቸው፡፡

እኛም ላለፉት አምስት ዓመታት በዚህ አካባቢ ወንጌልን እየተዘዋወርን ስንሰብክ ቆይተናል፡፡ ሁለት ማኅበር ተመሥርቶም ሁለት ጸሎት ቤቶች ተሠርተዋል፡፡

«እንደ እውነቱ ከሆነ የኋላ ኋላ ሁለቱም አካባቢዎች ከእኛ ሥራ ጋር ያልተያያዙ ችግሮች ነበሩ፡፡ በማንኛውም ቦታ ችግሮች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ይታወቃል» አልናቸው፡፡

እንዲሁም ደግሞ እኛ ወንጌላውያን እንደ መሆናችን ተግባራችንም መልካሙን ዜና ( ወንጌልን ) መስማት ለሚፈልጉት ሁሉ ማብሰር ነው፡፡ ስለ ስብከት በምናወሳበት ጊዜ የአካባቢው ሕዝብ ይሰበሰብና የተለያዩ ክሶችን ያቀርብብናል አልናቸው፡፡

ከመካከላቸውም አንዱ ተነሥቶ፣ «በአገራችን ሁለት ዓይነት ሃይማኖቶች አሉ፣ ይኸውም ክርስትናና እስልምና ናቸው:: እናንተ ግን አዲስ ሃይማኖት አምጥታችሁ መከፋፈልና ችግር አምጥታችሁብናል» አለ::

ይህንን ዓይነት ክስ ለአያሌ ጊዜያቶች ስንሰማ የቆየን ስለሆነ መልስ ለመስጠት ችግር አይኖርብንም::

«እኛ ክርስቲያኖችና ወንጌላውያን ነን:: በመላው ዓለም ውስጥ ያሉት ክርስቲያኖች ያላቸው አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ካስተማርናቸው ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለውን አስተምረን ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አምጡና አሳዩን» አልናቸው::

አስተዳዳሪውም እቋርጠው፣ «ሌላ ሃይማኖት ሲያመጡና ሲለማመዱ ሰምታችኋል? ወይም አይታችኋል?» አሉና ከሳሾቻችንን ጠየቋቸው::

ሁሉም ለጥቂት ጊዜ ዝም ካሉ በኋላ ሌላ ክስ አቀረቡ::

«እነዚህ ሰዎች ምን ጥሩ ነገር ይሠራሉ? ለእኛስ ምን አድርገውልና? ( በልባችን በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሌሎች ሰዎችስ ለምን ተመሳሳይ ጥያቄ አልቀረበላቸውም ብለን እንታዘባቸው ነበር::) እነዚህ ሰዎች በዚህ አካባቢ ሆነው እንዲሰብኩ ለምን እንፈቅድላቸዋለን?» በዚህ ርእስ ላይ ሞቅ ያለ ውይይት አካሄድን:: እኛ በአካባቢው ለረዥም ጊዜ የቆየን ባንሆንም የሕክምና፣ የት/ቤቶችና የእርሻ ሥራ ጥቅሞችን (በኤስ ኣይ ኤም) በኩል እንዳሠራንላቸው ሕዝቡ የሚያውቀው ነው:: ከረዥም ውይይት በኋላ ሚስዮኑና ወንጌላውያኑ ቁሳዊ ጥቅሞችን ለአካባቢው ኅብረተሰብ እንዳመጡ ተማምነን ተሰማሙ::

ከጓደኞቻችን አንዱም የአካባቢው የገበሬ ማኅበር ለቢሮነት ያሠራነውን ጸሎት ቤታችንን ለመውሰድ ዕቅድ እንዳለውም ነገረን:: እዚያው ቃለ መጠይቅ እየተደረገልን በነበርንበት ቦታ ከወንጌላውያኖች አንዱ ቶማስ የሚባለው የተባለውን ጸሎት ቤት በውስጡ እየኖረ እንዲጠብቅ አደረግን:: ምክንያቱም ባዶ የተዘጋ ቤት አግኝተን ወሰድን እንዳይሉ የፈጠርነው ዘዴ ነበር:: በመጨረሻም ቤቱን ተረክበን ለፈለግነው ተግባር አዋልነው::



## ቤታችንን ለመውሰድ መፎካከር

በዕለተ ዓርብ ቶማስ መጥቶ የገበሬ ማኅበር ሥራ አስፈጻሚ አባላት ጸሎት ቤታችንን በእርግጠኝነት ወስደው የራሳቸው ጽ/ቤት ለማድረግ አቅደዋል አለና ነገረን:: የዓርብን ምሽት ሁላችንም ተሰብስበን በጉዳዩ ላይ ጸለይንበት:: ምን ማድረግ እንደምንችል ግን አልገባንም ነበር::

ስለ ቤቱ አስቀድሞ የነበረን አሳብ የወንጌላውያን ስብሰባ በሚኖረን ጊዜ በየቅዳሚው ሌሊት እንሰበሰብበታለን፣ በነጋታው እሑድ ደግሞ ከምእመናኑ ጋር ተሰብስበን አምልኮታችንን እንፈጽማለን የሚል ነበር:: እንደ ዕቅዳችን ቅዳሜ ማምሻውን ወደ ጸሎት ቤታችን ስንደርስ፣ የገበሬ ማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ አባላትም እዚያ ደርሰው ከእኛ ጸሎት ቤት ባልራቀ ቦታ ድንኳናቸውን ዘረጉ:: በጸሎት ቤታችን ውስጥ እንደነበርን ጸሎታችንንና ስብከታችንን ቀጠልን:: ሰዎቹም በቁጣ ተነሡብን:: በነጋታውም ይህንን ቤት ዳግመኛ ልትጠቀሙ አትችሉም አሉን::

ከድር የሚባለው ሰውዬ ቀርቦ፣ «ትእዛዝ እየሰጠናችሁ ነው:: በዚህ ቦታ ዳግመኛ አትሰብኩም» አለ::

እኔም መልሼ፣ «እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ አለ:: እግዚአብሔርን በቤት ውስጥ ብናመልከው ወይም ከቤት ውጪም ብናመልከው የሚያመጣብን ልዩነት አይኖርም:: አምልኮታችን በእጅ በተሠራ ሕንፃ የሚወሰን አይደለም:: ምናልባት ስብከታችንን ተጠራጥራችኋል መሰለኝ» አልኩት::

«ምን ማለትህ ነው?» አለና ጠየቀኝ::

እኔም፣ «እኛ ስለ ማንም ስለ ምንም አንሰብክም:: ነገር ግን ክርስቶስን ብቻ እንሰብካለን:: ሰዎች በእርሱ አምነው እንዲድኑም እንነግራለን:: በስብከታችን ውስጥ ሌሎች ሰዎች ስለሚሠሩት ሥራ ጣልቃ አንገባም:: ይህን ጸሎት ቤት ለመውሰድ ከፈለጋችሁ እኛ አናግዳችሁም:: እንዲሁም የቤቱን መወሰድ እግዚአብሔርን እንዳናመልክና የወንጌል ስብከታችንን እንድናቆም የሚያደርገን አይደለም::» በዚህን ጊዜ ከድር በግልጽ ተቆጥቶ አንዳች መልስ ሳይሰጥ ከእኛ ተለይቶ ወደ መጣበት ተመለሰ::

ከዚያም በኋላ ቶማስን ለማነጋገር ሄድኩኝ:: ሌላ ችግር እንደነበረም ነገረኝ:: እኛም ቶማስ ተመልሶ በመሄድ ስለ ጉዳዩ ከካድሬው ጋር

እንዲነጋገር ወሰንን።አላስፈላጊ የሆነ ችግር እንዲፈጠር አልፈለግንም። ይህ ካድሬ አስቀድሞ የአካባቢው ሹም ነበርና ማንነታችንን ያውቃል።

ለረዥም ጊዜ ከተወያዩ በኋላ ወደ ግራዝማች አድነው ሄዱ። ግራዝማች አድነው በአካባቢው በሥልጣን የቆዩ ናቸው።

«እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ካለ፣ በሌላ ቦታ ቤት ለምን አትሠሩም? በአላችሁበት ቦታ ሁሉ እግዚአብሔር ይሰማችኋል። በዚህ እኛ የጽሕፈት ቤት ለማድረግ በመረጥነው ቤት ላይ ብቻ ለምን ታተኩራላችሁ?» አሉን።

እኔም፣ «ጅብ ከላይ እየጠጣ ከታች ዝቅ ብላ የምትጠጣውን አህያ ውኃውን ለምን ታደፈርሽብኛለሽ? » ያላትና «አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ» የሚባለው ተረት ታወሰኝ።

ከረዥም ውይይት በኋላ ካድሬው ለቶማስ፣ «ቤታችሁን ጠዋት ጠዋት ተጠቀሙበት፣ እኛ ደግሞ ለጉዳያችን ከሰዓት በኋላ እንጠቀምበታለን።»

ግራዝማችም ራሳቸውን ከፍና ዝቅ በማድረግ መስማማታቸውን ገለጹ። እኛም ምርጫ አልነበረንምና ተስማማን።

*ማስታወሻ*

1. በደቡባዊ ጋሞ ጎፋ በትንሹ ከተማ አጠገብ የኤስ ኣይ ኤም ጣቢያ ይገኛል።

2. በበና አካባቢ ግን አይደለም።

3. ይህ ሃይማኖታዊ ድርጅት በ1924 ዓ.ም የተወለደ ቢሆንም፣ እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ በዚህ ስም ሳይታወቅ ቆይቷል።



*በ1988 ዓ.ም ወንጌላዊ መሐሪ ወጣት ወንጌላውያንን ወደ በና ምድር በመውሰድ እዚያ ለሚገኘው አገልግሎት አስተዋወቋቸው። ይህ ምዕራፍ የታሪኩ መጨረሻ አይደለም።ይህን ምዕራፍ የምጨምርበት ምክንያት እግዚአብሔር ለአዲሱ ትውልድ አዳዲስ ወንጌላውያንን በማስነሣት ድምጻቸቸውን ከፍ በማድረግና በመንቀሳቀስ ወንጌልን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማዳረስ እንዲችሉ ያደረጋቸው መሆኑን ለመግለጽ ነው።*

*ብራዬን ፋርገር*

# የድኅረ አብዮት ስኬት

## ምዕራፍ ሃያ ሦስት

የመንግሥት አገዛዝ በግንቦት ወር በ1983 ዓ.ም ሲወድቅ፣ በኢትዮጵያ አዲስ ዘመን መፈንጠቅ ጀመረ። በሃይማኖት በኩል ታይቶ የማይታወቅ ልምዶች ታይተዋል። ለአንዳንድ ሰዎች የማይዋጥ ሲሆን፣ ለሌሎች ግን ተጽዕኖው ችግር አልፈጠረባቸውምና ጥሩ ለውጥ ነበር።

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥት መንፈሳዊ ያልሆነ መሆኑን ገልጾ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ሌላው ሃይማኖት የራሷን እምነት ይዛ መራመድ ጀመረች። ለ1500 ዓመታት መንግሥት የማንም ጎሣ ይሁን ኦርቶዶክስን ይደግፍ ነበር።

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ግን በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሃይማኖትና ለመሰብሰብ ያልተገደበ ነጻነት ተሰጠ። ሰዎች በየቤታቸው እየተሰበሰቡ በነጻነት ማምለክ ጀመሩ። ቤት ተከራይተው ወይም መሬት ገዝተው ጸሎት ቤት መገንባት ችለዋል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ባልተጠበቀ ሁኔታ እየሰፋ ያለውን ቤተ ክርስቲያን ማንም ለማፍረስ አይችልም።

በየቋንቋ መጠቀም በይፋ ተፈቀደና በብዙ መንገድ በየክልሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መሥራት ተቻለ። ብዙ ሰዎችም ይህንኑ አመስግነው ተቀበሉት። አስቀድሞ ያልነበራቸውን የጎሣ ዕውቅና እንዳስገኘላቸው ነበር የተሰማቸው። በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በየአካባቢው የአፍ መፍቻ ቋንቋ በግዴታ መስጠት ተጀመረ። በአማርኛ ቋንቋ ላይ መደገፋቸው እየቀረ ሄደ። በየከተማው

የወንጌል ስርጭቱ እየፈነዳ ተስፋፋ:: በንጉሣዊ አገዛዝና በማርክሳዊ አገዛዝ ዘመን በየከተማዎች ወንጌልን ለማዳረስ በጣም አስቸጋሪ ነበር:: ምክንያቱም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተቃውሞ ትፈጥር ስለነበረ ነው:: ማንኛውም ሰው በነጻነት የፈለገውን ሃይማኖት መከተል እንደሚችል፣ በፈለገውም ቦታ የመስበክና የማስተማር እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን የመመሥረት ነጻነት እንዳለው ማዕከላዊው መንግሥት አውጇል::

በዚያ አጋጣሚ የክርስቲያንን ሃይማኖት የማይከተሉ የይሖዋ ምስክሮችና ሞርሞን የሚባሉ ሃይማኖቶችም ነጻነታቸውን ተጎናጽፈዋል::

በብዙ የገጠር አካባቢዎች የየማኅበራቱ ንብረቶች በተዘረፉባቸው ቦታዎች ሁሉ የጸሎት ቤቶችን መልሶ ለመገንባት ጊዜ ይወስድ ነበር:: መልሶ የመገንባቱ ሂደት በጥሩ ሁኔታ ይካሄድ ነበር:: በብዙ የገጠር አካባቢዎች ክርስቲያኖቹ ንብረታቸውን ያፈረሱባቸውንና የዘረፉአቸውን ለመክሰስ ያደረጉት ጥረት አልነበረም:: በተለያዩ ምክንያቶች ከእምነታቸው ያፈገፈጉና ወድቀው የነበሩት ክርስቲያኖች ንስሐ እየገቡ ወደየማኅበሮቻቸው ተመለሱ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ከእምነታቸው የወደቁትን ሰዎች በጊዜው በነበረው ግፊት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ያለፈውን ትተው አብረው ወደፊት መራመድ ጀመሩ::

በተጨማሪም በገጠር ያሉ አማኞች የአገር አቀፍ (ብሔራዊ) የቤተ ክርስቲያን ድርጅት ጥቅም እየገባቸው መጣ:: በንጉሡ አገዛዝ ዘመን የገጠር ቤተ ክርስቲያን ጨቅላና ደካማ ስለነበረች ብዙ መንፈሳዊ ዕድገት አልነበራትም:: በማርክሲስት መንግሥት አገዛዝም ብሔራዊ ማኅበራት ምንም ሊረዷቸው አልቻሉም:: የብሔራዊ ማኅበሩ ስኬት በአዲስ አበባ በአነስተኛ ንብረቱ ላይ ባለበት መቆየት ነበረበት:: ነገር ግን የአገር አቀፍ ማኅበር ከማዕከላዊው ቢሮ ጋር የወንጌልን ስርጭት በማስተባበር መንፈሳዊ ትምህርትን ለማዳረስ ማፋጠናቸው ግልጽ ነበር:: የአዲሱ መንግሥት ዕቅድ የክልሉን መንግሥት በማበረታታት በአንድ ልብ በመነሣት አማኞች የሚፈልጉትን ሁሉ በማድረግ ሕዝቡን በወንጌል ለማድረስ በሚያደርጉት ጥረት ሁሉ እንዲተባበሩ ነው::

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ወንጌልን በመላው ሀገሪቱ ለማስፋፋት ገንቢ ልምዶችን ከማካበቷም በላይ፣ የሠለጠኑ ወንጌላውያንን በተገቢው ቦታ በማሰለፍ ሕዝብ በሚበዛባቸው የከተማ አካባቢዎች በቆላማው ዘላን ሕዝብ አካባቢ ሁሉ ሳይቀር ወንጌልን እንደሚገባ አዳርሳለች::

ለእንደ አቶ መሐሪ ዓይነት ወንጌላውያን ለአሥርት ዓመታት ሥራው ተስፋ አስቆራጭ ነበር:: በእርግጥ ይህ የሚሆነው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም አገሮች ጭምር ነው:: የወንጌላዊ መሐሪን ታሪክ በዚህ ጽሑፍ የመግለጽ ዓላማው ሰዎች ሁሉ በራሳቸው መንገድ የእግዚአብሔርን ኃይል ለመግለጽ እንዲችሉ ለማሳወቅና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መልካሙን ዜና (ወንጌልን) በፍጹም ሰምተው ለማያውቁት ሰዎች ለማዳረስ ወንዱም ሴቱም ራሳቸውን በመስጠት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲነሣሱ ለማድረግ ነው::



<u>ኢትዮጵያዊው ወንጌላዊ</u> የሚለው መጽሐፍ ስለ አንድ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን የሚያወሳ መጽሐፍ ነው። የእነዚህ ወንጌላውያን እምነታቸው፣ መሰጠታቸው፣ ድፍረታቸውና የዓላማ ጽናታቸው ልዩ ያደርጋቸዋል። ልናስታውሳቸውም ይገባናል። መጽሐፉ ከእነዚህ ወንጌላውያን መካከል የአንዱ ግለ ታሪክ ነው። ባለታሪኩ በተደጋጋሚ እንዲህ ይላሉ፣ «በእኔ ውስጥ እግዚአብሔር ስለሠራው ነገር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። እባካችሁን ይህንን አትርሱ - እኔ እግዚአብሔር ወንጌልን ለማስራጨት ከተጠቀመባቸው አንድ የተለየ ትውልድ ወንጌላውያን መካከል አንዱ ነኝ።»

ብራያንና ዶሪስ ፋርገር ከኤስ ኣይ ኤም ኢትዮጵያ ጋር በሚስዮናዊነት ከ1950 - 1977 ዓ.ም ድረስ አገልግለዋል። ከወንጌላዊ መሐሪ ጮራሞ ጋር ባያገለግሉም፣ ከባልንጀሮቻቸው ጋር ግን በደቡብ ኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች አገልግለዋል። ይህ መጽሐፍ ለእነዚህ ጀግኖች የአገልግሎት አጋሮቻቸው መታሰቢያነት የተበረከተ ነው። «እኛ እናደንቃቸዋለን። እነርሱ ለእኛ የማያቋርጥ መጽናኛችን ነበሩ።»